አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

# አዲስ ልሳን

ቅጽ 32 ቁጥር 3540 | ቅዳሜ መስከረም 17 ቀን 2018 ዓ.ም | ዋጋው 10.00 ብር




# "በያዝነው አዲስ ዓመት በጋራ ሰርተን መልማትን ምርጫችን እናድርግ"

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ


3

ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ ማቲያስ የ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓልን አስመልክቶ በመስቀል አደባባይ መልዕክት ሲያስተላልፉ

## የቱሪዝሙ ንጋት ነፀብራቅ

11



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዕድገት ከፍተኛ አቅም እንደሚፈጥር የሚጠበቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ

## የአደባባይ በዓላት በብርሃናማዋ ከተማ

6



ፎቶ ከፋይል

የመስቀል ደመራ በዓል ከፊል ገጽታ

## የመስቀል ዘገባ ትውስታዎች በውጭ መገናኛ ብዙኃን

18



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

የውጭ ሀገራት ዜጎችን ጭምር ቀልብ የሚስበው የመስቀል ደመራ በዓል

# "በትጋት እየቆፈርን፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና እናወጣዋለን"

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)



**በሳህሉ ብርሃኑ**

በመደመር ደመራ እየተመራን፣ በትጋት እየቆፈርን፣ የኢትዮጵያን ብልጽግና እናወጣዋለን ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት፣ በመደመር ደመራ እየተመራን፣ በትጋት እየቆፈርን፣

ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# "አዲስ አበባ ለበዓሎቻችን ድምቀት፣ ለቱሪስቶች ደግሞ መስህብን እየጨመረች ትገኛለች"

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ

**በሳህሉ ብርሃኑ**

አዲስ አበባ ለበዓሎቻችን ድምቀት፣ ለቱሪስቶች ደግሞ መስህብን እየጨመረች ትገኛለች ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተናገሩ

ከንቲባ አዳነች አቤቤ በትናንትናው ዕለት የመስቀል ደመራ በዓል በመስቀል አደባባይ በተከበረበት

ወደ ገጽ 4 ዞሯል

**አድራሻ** +251 111 112 218 +251 111 267 266 www.amn.gov.et 5 kilo infront of St. Mary Church Addis Ababa Ethiopia

# ርዕሰ አንቀፅ



## ለቱሪዝሙ ዘርፍ የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ወደ ሃብት መቀየር ያስፈልጋል!

ቱሪዝም በዓለም ኢኮኖሚ ውስጥ ቀላል የማይባልን ድርሻ እየያዘ መጥቷል። ካምበርላንድ ቫሊ ገጸ ድር እ.ኤ.አ በ2024 Importance of Tourism to Local Economies በሚል ርዕስ ለንባብ ያበቃው ጥናታዊ ጽሑፍ ቱሪዝም በበርካታ ሀገራት የሀገር ውስጥ ጥቅል ምርት ዕድገት ከፍተኛውን ድርሻ እየያዘ መምጣቱን ያስረዳል።

በተመሳሳይ ስታቲስታ ገፀ ድር Global tourism industry - statistics & facts በሚል ርዕስ ያወጣው መረጃ ቱሪዝም በ2024 ብቻ 10 ነጥብ 9 ትሪሊዮን ዶላር በዓለም ጥቅል የሀገር ውስጥ ምርት ዕድገት ላይ አስተዋፅኦ አድርጓል። ይህም 10 በመቶውን የዓለም ኢኮኖሚ ድርሻ ይይዛል ማለት ነው፡፡ ዕድገቱ በዚሁ ቀጥሎ እ.ኤ.አ በ2034 ቱሪዝም ለዓለም ኢኮኖሚ 14 ትሪሊዮን ዶላር ድርሻ የሚያበረክት ዘርፍ እንደሚሆን ትንተናዊ ትንበያ ተቀምጧል፡፡

ኢትዮጵያ የአያሌ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤት ብትሆንም ከዘርፉ እያገኘች የቆየችው ገቢ የሚመጥናት አልነበረም፡፡ ለበርካታ ዓመታት የዘርፉን ትሩፋት ሳትቋደስ ቀርታለች፡፡ በተለይ መስህቦች አካባቢ ላይ የሚስተዋሉ የመሠረተ ልማት ውስንነቶች፣ የአስጎብኚዎች እውቀትና ክህሎት ክፍተት እንዲሁም በቂ የማስታወቂያ ስራዎችን አለመስራት የመሳሰሉ ክፍተቶች ሀገሪቷ በበቂ ደረጃ እምቅ ሀብቷን እንዳትጠቀም አድርገዋል፡፡

አዲስ አበባም ለቱሪዝም ምቹ የሆነች ከተማነቷን በተለያዩ ምክንያቶች ተጠቅማለች ብሎ ለመናገር አያስደፍርም፡፡ የሆነው ሆኖ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የሀገራችን የኢኮኖሚ እይታ መስተካከሉ ቱሪዝም ትኩረት እየተሰጠውና እየለማ፣ የጎብኚዎችም ቁጥር እየጨመረ እንዲመጣ አስችሏል፡፡ በዚሁ የእይታ ለውጥ አቧራ ለብሰው የቆዩ ፀጋዎች አሁን ወደ ተጨባጭ ሀብትነት ተቀይረዋል፡፡ በተለይ ገበታ ለሸገር፣ ገበታ ለሀገር፣ ገበታ ለተውልድ እና ከተሞችን የማስዋብ ስራዎች የቱሪዝሙን ዘርፍ በተጨባጭ አሳድገውታል።

ኢትዮጵያ በጥቂት ዓመታት ውስጥ የሰራቻቸው እንደ ጎርጎራ ኢኮ ቱሪዝም፣ ቤኑና መንደር፣ ወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም፣ ሐላላ ኬላ ሪዞርት፣ ጨበራ ጩርጩራ ብሔራዊ ፓርክ የመሳሰሉ መስህቦች የቱሪዝም ዘርፉ ላይ ጉልህ ልዩነት አምጥተዋል፡፡ በአዲስ አበባ ከተማ የተከናወኑት ዘርፈ ብዙ የልማት ስራዎችም የቱሪዝም ዕድገቱን የሚያፋጥኑ ናቸው። በተለይ እንጦጦ ፓርክ፣ አንድነት ፓርክ፣ ወዳጅነት አደባባይ፣ ሳይንስ ሙዚየም፣ የዓድዋ ድል መታሰቢያ፣ አዲስ ዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን ማዕከል፣ ግዙፍ ፕላዛዎችና የተሽከርካሪ ማቆያ ልማቶች ከተማዋ ከቱሪስቶች መሸጋገሪያነት ወደ መዳረሻነት እንድትለወጥ ምክንያት በመሆን ላይ ናቸው፡፡

የኮሪደር እና የወንዝ ዳርቻ ልማቶችም የአዲስ አበባን መልክ በእጅጉ አሻሽለዋል፡፡ ፒያሳ፣ አራት ኪሎ፣ ከመገናኛ እስከ አያት እና ከፒያሳ እስከ መስቀል አደባባይ፣ ሲ.ኤም.ሲ፣ መገናኛ፣ ጉርድ ሾላ፣ ካዛንቺስ፣ ከአራት ኪሎ እስከ እንጦጦ እና ሌሎች የኮሪደር ልማቱ የጎበኛቸው ስፍራዎች ለቱሪዝም ምቹ ሁኔታን ፈጥረዋል፡፡

እነዚህ ከተማዋን የማስዋብ፣ የማፅዳትና ምቹ የማድረግ ተግባራት የበርካታ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ተቋማት መናገሻ፣ የዲፕሎማቲክ ማህበረሰብ መናኸሪያ ለሆነችው አዲስ አበባ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ ለአብነትም የተለያዩ ጉባኤዎች ማከናወኛ አድርጓታል፡፡ መዲናዋ በተጠናቀቀው በጀት ዓመት ብቻ 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ያህል ጎብኚዎች የተሳተፉበትን 150 ዓለም አቀፍ ኩነቶችን አስተናግዳለች። በዚህም 143 ቢሊዮን ብር ያህል ሀብት ወደ ከተማዋ ኢኮኖሚ ገቢ ሆኗል።

ለቱሪዝሙ ዘርፍ የተፈጠረውን ይህን ምቹ ሁኔታ ወደ ሃብት መቀየር ያስፈልጋል፡፡ ሆኖም ዘርፉ ካለው ባህሪ አንፃር ተሳታፊ የሚሆኑ ባለ ድርሻ አካላት በርካታ እንደመሆናቸው ከዘርፉ ከሚገኘው ሀብት አሟጥጦ ለመጠቀም አገልጋይነትን ማስቀደምና የሀገርና ከተማችንን ስም ማስተዋወቅ ላይ መስራት ይገባል፡፡

# የእኔ እይታ

ይህ ገፅ ዜጎች በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳባቸውን በነፃነት የሚያንፀባርቁበት ሲሆን ይህም የጋዜጣዋን የዝግጅት ክፍል አቋም አይገልፅም።

## ከበዓላቱ ልንወርሳቸው የሚገቡ እሴቶች፡- አንድነት እና ሕብረት

**በሐብታሙ ደበሌ**

አዲስ ዓመት፣ መስቀል ደመራ፣ ኢሬቻ እና ሌሎች መሰል በዓላት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከበሩበት እና የሚከበሩበት ወር ነው፤ መስከረም። በዓላቱ ኃይማኖታዊ እና ባህላዊ ትርጉም ተሰጥቷቸው በተለያየ ሁነቶች የሚከወኑ ናቸው፡፡ የክረምት ዝናብ አብቅቶ፣ ጥቁር ደመና የጋረደው ሰማይ ጠርቶ፣ ወንዞች ጎድለው፣ ምንጮች ኩልል ብለው፣ ምድር በልምላሜ እና በአበቦች ተውባ ... ተስፋና ብርሃን ከፍ ብሎ የሚታይበት ወቅት በመሆኑ፤ የመስከረም እና የበዓላቱ መገናኘት ልዩ ስሜትን ይፈጥራል፡፡

በእነዚህ በዓላት የሕዝብ አንድነት እና ሕብረት ጎልቶ ይታያል፡፡ በተለይ መስቀል ደመራ እና ኢሬቻ በዓላት በአደባባይ የሚከወኑ እንደመሆናቸው መጠን፤ የሕዝብ አንድነት እና ሕብረት በገሃድ ይገለጥባቸዋል፡፡ በአንድነት ገዝፎ መቆምን፣ በመተባበር መጠንከርን፣ በመሰባሰብ አቅም መፍጠርን፣ በመደመር ማሸነፍን በእነዚህ በዓላት ተምሳሌትነት እንገነዘባለን፡፡ ንፅህናን፣ ፍቅርን፣ ይቅር ባይነትን፣ ከፈጣሪ ጋር መቀራረብ እንዲሁ የበዓላቱ ልዩ መገለጫ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

ከእንጨት የሚሠራው ደመራ፣ ችቦ የሚዘጋጅበት አኳኋን፣ ምዕመኑና ሕዝቡ በደመራው የሚሰባሰብበት ስርዓት፣ የዝማሬ እና የሥርዓት ዕምነቱ ክዋኔ አጠቃላይ ገፅታ የሚያሳየውም ሆነ የሚገልጠው የአንድነትንና ሕብረትን አቅም ነው፡፡ በወርሃ መስከረም በድምቀት የሚከበሩት የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ በዓላት ለሀገር እና ሕዝብ የሚያስገኙት ፋይዳ ሠፊና ጥልቅ መሆኑ ይታወቃል። እሱን ተረድቶ በአግባቡ መጠቀም በባህልና ቱሪዝም ዘርፍ ኃላፊነት ያለባቸው አካላት ዋነኛ ተግባር ሊሆን ይገባል። እንደ ሕዝብ ግን በእነዚህ በዓላት አማካኝነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ይዘው ያሸጋገሩልንን ውድ እሴቶች መጠበቅ፣ የሕይወት መመሪያ አድርጎ መጠቀም ይገባል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ በዓላት አጉልተው ከሚያንፀባርቋቸው እሴቶች መካከል ዋነኞቹ የአንድነትን እና የሕብረትን ኃያልነት ነው።

ለኢትዮጵያ እና ለኢትዮጵያዊያን ደግሞ አንድነት እና ሕብረት ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት ጉንጭ ማልፋት ነው የሚሆነው፡፡ ሌላውን ትተን በቅርቡ የተመረቀውን "የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን" ማንሳት፤ ኢትዮጵያዊ በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን በሀገር ጉዳይ በአንድነት ለመቆም የማያቅማማ መሆኑን ያሳያል፡፡ ወደኋላ መለስ ካልንም፤ "የዓድዋ ድል" የአንድነትና የሕብረት ውጤት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በማይዳሰስ ሃብትነት በዩኔስኮ የተመዘገቡ የመስቀል ደመራ እና የአባገዳ ስርዓት (የስርዓቱ አንዱ አካል የሆነው ኢሬቻ) በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚከበሩ ቢሆንም፤ በአዲስ አበባ ግን ያላቸው ድምቀት የተለየ ነው፡፡ በዘንድሮው ዓመት ደግሞ ልዩ ገፅታ እና ድባብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ምክንያቱም በማያቋርጥ ልማት ውስጥ እያለፈች ያለችው አዲስ አበባ፤ በጊዜ ምህዋር ውስጥ መዋቧ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህ ሁኔታ በበዓላቱ ሁነት ለመሳተፍ ከተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች እንዲሁም ከሌሎች የዓለም ሀገራት የሚመጡ እንግዶች ብዙ ናቸው፡፡ እነዚህን እንግዶች በፍቅር ተቀብሎ፣ በወጉ አስተናግዶ፣ አዲስ አበባን እንዲናፍቋት አድርጎ መሸኘት ከነዋሪው ይጠበቃል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መሠረተ ልማቶቿ ተጠብቀው፣ ሠላምና ፀጥታዋ ተረጋግጦ በዓላቱ በተሳካ መልኩ እንዲካሄዱ ማድረግም ከሁሉም ይጠበቃል፡፡ ለዚህ ደግሞ የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ ያስተማሩንን ድንቅ የአንድነትና የሕብረት እሴቶች መረዳት እና መጠቀም ይኖርብናል እላለሁ፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ
ADDIS MEDIA NETWORK

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየተዘጋጀች

ዘወትር ቅዳሜ ወደ አንባቢያን
የምትደርሰው ይህች ጋዜጣ

ግንቦት 1985 ዓ.ም
ተመሰረተች

**አድራሻ**
አምስት ኪሎ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ፊት ለፊት
በሚገኘው ማህበረ ቅዱሳን ህንፃ ጎን
ስልክ ቁጥር 0111-574923
ፖ.ሣ.ቁ 27080 code 1000
ፋክስ - 559368
addislisan1985@gmail.com

**የገበያ አገልግሎት እና የማስታወቂያ ዝግጅት ዳይሬክቶሬት**
ስልክ 0111 - 112218

**አታሚ**
ሜልባ ፕሪንቲንግ ፐብሊሺንግ ኤንድ ፓኬጂንግ ሼር ካምፓኒ

**ግራፊክስ ዲዛይን**
ዳንኤል ተስፋይ

**ሌይአውትና ዲዛይን**
ፍልሰታ አየለ

**የእርምት ባለሙያ**
ቸርነት ዋለልኝ
ገነት መላኩ

**የዕለቱ አዘጋጆች**
ለይላ መሀመድ
አብርሃም ገብሬ
ሸዋርካብሽ ቦጋለ
ፋንታነሽ ተፈራ
ሄለን ጥላሁን
ይግለጡ ጓዴ

**ዋና አዘጋጅ**
ምህረቱ ፈቃደ
Mehretu@gmail.com
አድራሻ ለሚ ኩራ ክ/ከተማ
ወረዳ 3 የቤት ቁጥር 34/55

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሰውነት ኃ/ጊዮርጊስ
መለስ ተሰጋ

**ከፍተኛ አርታኢያን**
ደረጀ ታደሰ
ጊዜው አማረ
ስንታየሁ ምትኩ
ሳህሉ ብርሃኑ

# “በያዝነው አዲስ ዓመት በጋራ ሰርተን መልማትን ምርጫችን እናድርግ”

**ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ**

**በመለሰ ተሰጋ**

በያዝነው አዲስ ዓመት እርስ በእርሳችን ከመጠፋፋት ይልቅ በጋራ ሰርተን በጋራ የምንለማበትን ምርጫችን እናድርገው ሲሉ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ተናገሩ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ-ክርስቲያን ፓትርያርክ ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ማቲያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለሃይማኖት ይህንን ያሉት የመስቀል ደመራ በዓልን አስመልክቶ ባስተላለፉት መልዕክታቸው ነው፡፡

አቡነ ማቲያስ በመልዕክታቸው፣ “የመስቀሉ መልዕክት የሰው ልጅን ሁሉ በሰላም፣ በሕይወት፣ በእኩልነት፣ በአንድነት ማኖር መሆኑን ከልብ ተገንዝበን በያዝነው አዲስ ዓመት እርስ በእርሳችን ከመጠፋፋት ይልቅ፣ በጋራ ሰርተን በጋራ የምንለማበትን ምርጫችን እናድርገው” ሲሉ አሳስበዋል፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ፓትርያርክ ብፁዕ አቡነ ማቲያስ የ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓልን አስመልክቶ በመስቀል አደባባይ መልዕክት ሲያስተላልፉ

እግዚአብሔር ሁለመናው እንከን የለሽ ፍፁም አምላክ መሆኑን የጠቀሱት፣ አቡነ ማቲያስ፣ በዚህም ጥፋትን የማይወድ አምላክ ነው ብለዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ሕግ ላይ ድፍረትን የተሞላ ስህተት ወይም ጥፋት በመፈፀሙ እግዚአብሔርን ማስቆጣቱን አውስተዋል፡፡

“ከዚህ አንፃርም ሰው በተግባሩ ደካማ ሆኖ ተገኘ፡፡ እግዚአብሔርም ሰውን በጥፋቱ ቀጣው፡፡ የቅጣቱም አይነት ሞት ነበር፡፡ በሰው ላይ የተላለፈው የሞት ቅጣትም በምድርም በሰማይም ተፈፃሚ ሆነ፡፡ ይህም ማለት ሰው በምድራዊውም ሆነ በሰማያዊ ኑሮው ከእግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ሁሉ ከሆነው ተለየ ማለት ነው፡፡ ይህም ቅጣት ለሰው ልጅ እጅግ መራራ ቅጣት ነበር” ብለዋል፡፡

በዳኛነቱ ፈራጅና ቀጭ የሆነው እግዚአብሔር በአባትነቱም መሐሪና ይቅር ባይ በመሆኑም በሀጢአት ደክሞ የወደቀውን የሰው ልጅ በቤዛዊ ሞቱ የሚያድነው መሆኑን ተስፋ ሰጠው። በዚህ ዓለምም ተገለጠ፡፡ ሰው የሚድንበትን ወንጌል ካስተማረ በኋላም በመስቀል ላይ ቤዛነትን ተቀብሎ ቅጣታችን እንዲነሳ አደረገልን ያሉት ቅዱስ ፓትርያርኩ ለዚህም፣ “ሁሉም በአዳም እንደሚሞቱ ሁሉም በክርስቶስ ይድናሉ” የሚለውንም የመፅሐፍ ቅዱስ ቃል በዋቢነት ጠቅሰዋል፡፡

ምንም እንኳን በመስቀል ላይ በተፈፀመው የጌታችን ቤዛዊ ሞት ምክንያት ነባሩ ቅጣታችን ቢነሳም በገቢር አበሳችን ምክንያት ዛሬም ከስህተት ለመፅዳት አልቻልንም ያሉት አቡነ ማቲያስ፣ በመሆኑም ዛሬም ከእውነት ጋ መጋጨታችን ስለቀጠለ በየጊዜው በምንፈፅመው ገቢር አበሳ እግዚአብሔርን ማስቆጣታችን አልቀረም፡፡ የመዳናችን ምልክትና ምስክር የሆነው እፀ መስቀል በሰዎች እንዲቀበር መደረጉም ገቢር አበሳችን መቀጠሉን የሚያመላክት ምስክር ነው ብለዋል፡፡

> **ሀገራችን ልትሰራቸው በዕቅድ የያዘቻቸው ታላላቅ የልማት ሥራዎች በፍጥነትና በጥራት ተሰርተው ለህዝብ ጥቅም እንዲውሉ ሁላችንም መረባረብ ይኖርብናል**

መስቀሉን መደበቅ ሆነም መሰወር ከሰው አቅም በላይ በመሆኑ በእግዚአብሔር ኃይል አመልካችነት መስቀሉ ከተቀበረበት ጉድጓድ ሊወጣ ችሏል፡፡ መስቀሉም እስከ ዛሬ ድረስ የእውነት መስካሪና የመዳን ምልክት ሆኖ ቀጥሏል ብለዋል ቅዱስ ፓትርያርኩ፡፡

የመስቀሉ አበይት መልዕክቶች ሰው ሊያምንባቸው፣ ሊቀበላቸውና ሊኖርባቸው በውጤቱም በስጋውም ሆነ በነፍሱ ሊድንባቸው እንደተሰጡ ጠቅሰው፣ ይሁን እንጂ እኛ ሰዎች በአንድ ጆሯችን ሰምተን በሌላኛው ከመጣል ባለፈ ያመጣነው ለውጥ እንደሌለ ተግባራችን እራሱ ምስክር ነውም ብለዋል፡፡

አክለውም፣ ዛሬም ሕገ እግዚአብሔር በድፍረት ይጣሳል፡፡ የዚህም ውጤት ዓለማችንን በመኖርና ባለመኖር ውስጥ እየከተታት ይገኛል፡፡ እኛስ በዚህ ሁሉ አልደከምንምን? የሚታደገን መስቀላዊ ኃይልስ አያስፈልገንም? ለሰላማችን መጠበቅና ለደህንነታችን ዋስትናስ ከመስቀሉ ቃልና ኃይል የበለጠ ሌላ አለን? ሲሉ የጠየቁት ቅዱስ ፓትርያርኩ በንፁህ አዕምሯችን በደንብ ካስተዋልነው ከመስቀሉ ቃል የበለጠ ለሰው ልጆች ሰላምንና አንድነትን የሚሰጥ ሌላ ኃይል በዓለማችን ውስጥ እንደማይገኝ ተናግረዋል፡፡

ፍፁምና ዘላቂ ሰላምን የምንሻ ከሆነ በመስቀሉ ቃል እንመራ፡፡ የመስቀሉ ቃል ማለት ይቅርታንና እርቅን፣ እኩልነትን እና አንድነትን፣ ፍትሕን እና ርትዕን ማረጋገጥ ማለት እንደሆነ በውል እንገንዘብ፤ በዚህ ሕይወት መኖር ከጀመርንም ድክመታችን በመስቀሉ ተወገደ ማለት ነው ሲሉ አባታዊ ምክራቸውን ገልፀዋል፡፡

የዘንድሮውን የመስቀል በዓል ልዩ የሚያደርገው እግዚአብሔር የሰጠንን ልዩ የውሃ ፀጋችንን ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም በአንድነት ተባብረን ባካሄድነው ጥረት የሕዳሴ ግድባችንን አጠናቅቀን ባስመረቅንበት ማግስት እየተከበረ ያለ በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

ይህ ክስተት ለሀገራችን ዳግም ልደትን ያበሰረ ስኬት ነው ብንል ማጋነን አይሆንም ያሉት ቅዱስ ፓትርያርክ አቡነ ማቲያስ፣ በዚህም እግዚአብሔር አምላካችንን ማመስገን ይገባናል፡፡ በስራው ላይ ታሪካዊ አሻራቸውን ላሳረፉ ሁሉ ምስጋና እንደሚገባቸውም ተናግረዋል፡፡

በቀጣይም ሀገራችን ልትሰራቸው በዕቅድ የያዘቻቸው ታላላቅ የልማት ሥራዎች በፍጥነትና በጥራት ተሰርተው ለህዝብ ጥቅም እንዲውሉ ሁላችንም መረባረብ ይኖርብናል በማለትም አባታዊ ጥሪም አቅርበዋል፡፡

ቅዱስ ፓትርያርኩ በመልዕክታቸው ታላላቅና ዘመን ተሻጋሪ እንዲሁም ችግር አስወጋጅ የሆኑ ሥራዎች እውን ሊሆኑ የሚችሉት ህዝቡ በአንድነትና በህብረት ተነስቶ ወደ ትግበራ ሲገባ እንደሆነ ከታላቁ ሕዳሴ ግድባችን ተምረናል ያሉ ሲሆን፣ በሕዳሴው ግድብ የታየው ትብብርና ተነሳሽነት አሁንም ተጠናክሮ መቀጠል አለበትም ብለዋል፡፡

መንግስትም ከዚህም ከዚያም የሚታዩ አለመግባባቶችን በእርቅ እና በይቅርታ በማለፍ እኩልነትን፣ ፍትህን እና ርትዕን በማረጋገጥ እንዲሁም ለሰላም መስፈን ረዥም ጉዞ በመሄድ ህዝቡን ወደ አንድነት የማምጣት ኃላፊነቱን እንዲወጣም ጥሪ ያቀረቡ ሲሆን፣ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ለመስቀል ደመራ በዓል ስላደረጉት ድጋፍም ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

ብፁዕ አቡነ ሳውሮስ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ፅህፈት ቤት ዋና ስራ አስኪያጅ፣ የደቡብ ምዕራብ ሸዋ እና ሸገር ከተማ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ባስተላለፉት የመስቀል ደመራ በዓል መልዕክት፣ በዓሉ መንፈሳዊ በዓል ስለሆነ ሁላችንም ከስጋዊ ተግባራት በመራቅ መንፈሳዊ ስራዎችን በመፈፀም ልናከብር ይገባል ብለዋል፡፡

መስቀል የሰው ልጆች ከእግዚአብሔር ጋር የታረቅንበት፣ ሰላም፣ ፍቅር እና አንድነት የተገኘበት፣ ጥል የተሸነፈበት፣ እርቅ የታወጀበት በዓል ነው ያሉት አቡነ ሳውሮስ፣ ይህን ታላቅ በዓል ስናከብር ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች የሰጠውን የማዳን ፀጋ እና በረከት በማሰብ ይሁን ሲሉ መክረዋል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀሉ ሰማይና ምድርን አንድ አድርጎ እንዳስታረቀው ሁሉ እኛም ከስሁት ተግባራት በመራቅ መንፈሳዊ አንድነታችንን አጠንክረን ቤተ ክርስቲያናችንን እና ሀገራችንን ልናገለግል ይገባል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

መስቀል የአንድነት በዓል በመሆኑ ለሀገር አንድነትና ለሰላም የማይተካ ሚና የሚያረጋግጥ በዓል ነው፡፡ በዓሉ በሰላም ተጀምሮ እንዲጠናቀቅ ድጋፍ ላደረጉልን ምስጋና እናቀርባለንም ብለዋል፡፡

## “በትጋት ... ከገጽ 1 የዞረ

የኢትዮጵያን ብልጽግና እናወጣዋለን ብለዋል።

ይህ ዓመት የኢትዮጵያ ብርሃን ሲወጣ የምናይበት ይሆናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የኢትዮጵያ እውነት እንደ መስቀሉ ሁሉ አቧራውን ጥሶ፣ አፈሩን አፍልሶ፣ ቆሻሻውን ደርምሶ ይገለጣል። የወጓት ያዩዋታል። ከላይ ሆነው እንዳዩዋት ሁሉ፣ ከታች ሆነው ይገረሙባታል ሲሉም አክለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር) በማብራሪያቸው፣ የመስቀል በዓል ሲታሰብ እውነት ተቀብራ እንደማትቀር እናስባለን። መስቀሉ የተቀበረበት ቦታ ተራራ ሠርቶ ነበር። የቀበሩት ሰዎች ከዚህ በኋላ እንደማይወጣ ደምድመው ነበር። አንዳንድ አማኞችም ተስፋ ቆርጠው ነበር። ጊዜው በረዘመ ቁጥር ቀባሪዎቹ ያሸነፉ መስሏቸው ተደሰቱ። የተቀበረው መስቀልም ታሪክ የሆነ መሰለ የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

አያይዘውም ብርቱ ሰዎች፣ እውነት ፈላጊ ሰዎች፣ አቧራውን የሚገልጡ፣ ቆሻሻውን የሚያነሡ ሰዎች፣ ሲመጡ ግን መስቀሉ ከተቀበረበት ወጣ። እውነት አይቀበርም። ጊዜው ሲደርስ አቧራውን አንሥቶ ዐሻራውን ያሳያል። ሐሰቱን እንደ ጉም አትንኖ፣ ሐቁን እንደ ዐለት አግንኖ ያሳያል ብለዋል።

የኢትዮጵያም እውነት እንደዚሁ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ የአውራ ዶሮዎች ጩኸት የፀሐይን መውጣት አያስቀረውም። የሌሊት ወፎች ክንፍ የፀሐይን ንጋት አያግደውም። በዚህም ተባለ በዚያ ፀሐይ ትወጣለች ብለዋል በመልዕክታቸው።



## “አዲስ ... ከገጽ 1 የዞረ

ወቅት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል። በመልዕክታቸውም፣ አዲስ አበባ እንደ ስሟ ውብ አበባ እየሆነች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየታደሰች ለኢትዮጵያ ተጨማሪ ድምቀት እየሆነች ስለመምጣቷ አስረድተዋል፡፡

ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች በማብራሪያቸው፣ ለዚህ ማሳያ ነው ያሉትን ሲገልፁ ራሱ የመስቀል አደባባይ አንዱ ማሳያ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡ ጉዳዩን ሲያብራሩም፣ ይህ የከተማ ዕድሳት የጀመረው ከመስቀል አደባባይ መሆኑን ጠቅሰው፣ “በቀጣይም የኢትዮጵያን ጉስቁልና እየናድን ብልፅግናዋን ማረጋገጥ ይጠበቅብናል” ብለዋል፡፡

“እንደ ሀገር የዘመናት ጨለማን የሚገፈውና የሀገራችን ህዝቦች እንደ መስቀሉ ደመራ ተደምረው በአንድነት መንፈስ በመረባረብ ለፍጻሜ ያበቁት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ባስተላለፉበት ወቅት

የተጠናቀቀበትና ለሀገራችን ብርሃናማ ጊዜ የመጣበት ወቅት በመሆኑ እንኳን ደስ አለን” ሲሉም ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ የመልካም ምኞች መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

አያይዘውም ይህ የኢትዮጵያውያን ታሪካዊ ድል በብዙ ፈተናዎች ውስጥ በፀሎትና በአምላክ እርዳታ የተገኘ ስኬት በመሆኑ ለፈጣሪ አምላካችንም ትልቅ ክብርና ምስጋና ይድረሰው እንላለንም ብለዋል፡፡

የመስቀል ደመራ በዓል የማይዳሰስ የዓለም ቅርስ ሆኖ የተመዘገበና ከኢትዮጵያውያን አልፎ በዓለም ያስተዋወቀን በዓል በመሆኑ ኃይማኖታዊ እሴቱን ጠብቆ በታላቅ ድምቀት እየተከበረ ይገኛል፡፡ ይህንን ልዩና ውብ ትዕይንት ለመመልከት ባህር ተሻግረው በመካከላችን የተገኙ የውጭ ሀገር እንግዶችን ”እንኳን ወደ ቀደምት ሀገር ኢትዮጵያ፣ የአፍሪካ መልህቅ ወደሆነችው ከተማችን አዲስ አበባ በሰላም መጣችሁ” ሲሉም ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ ተናግረዋል፡፡

በዓሉ የአብሮነት፣ የፍቅር እና የሰላም እንዲሆን ምኞታቸውን የገለፁት ከንቲባዋ፣ የመስቀል በዓል ከምንም በላይ ህዝባችን በስፋት የሚታደምበት፣ በዓሉን ለሚያከብሩ ምዕመናን ሁሉ በሰላምና ባማረ የኢትዮጵያን ከፍታ በሚያሳይ መልኩ በመከበሩ ደስ ብሎናል፤ እንኳን አደረሳችሁ በማለት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የትምህርት፣ ሳይንስ እና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) በማይዳሰስ ቅርስነት የተመዘገበው የመስቀል ደመራ በዓል በትናንትናው ዕለት በመስቀል አደባባይ በታላቅ ድምቀት ተከብሯል፡፡

# “የኢትዮጵያን የከፍታ ጉዞ ከዳር ለማድረስ እንደ ደመራ ችቦ ተሳስረን በአንድነት መነሳት ይገባናል”

**የኢፌዴሪ ባህል እና ስፖርት ሚንስትር ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ**

**በይግለጡ ጓዴ**

ኢትዮጵያ የጀመረችውን የከፍታ እና የማንሰራራት ጉዞ ከዳር ለማድረስ እንደ ደመራ ችቦ ተሳስረን በአንድነት መነሳት ይገባናል ሲሉ የኢፌዴሪ የባህል እና ስፖርት ሚኒስቴር ሚንስትር ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ ተናገሩ

የመስቀል ደመራ በዓልን አስመልክቶ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ያስተላለፉት ወይዘሮ ሸዊት ሻንካ፣ የዘንድሮው የመስቀል በዓል ኢትዮጵያ አስቸጋሪውንና ፈታኙን የከፍታ እና የማንሰራራት ጉዞ በጀመረችበት ወቅት የሚከበር ልዩ በዓል መሆኑን ጠቁመው፣ ይህን ጉዞ ከዳር ለማድረስ እንደ ደመራ ችቦ ተሳስረን በአንድነት መነሳት ይገባናል ብለዋል፡፡

አክለውም፣ የኢትዮጵያ ህዝቦች በመከባበር አብረው የዘለቁ መሆኑን አውስተው፣ አብሮ የመኖር ጥበብ፣ መነሻው ፍቅርና መከባበር ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ይህ እውነተኛ ትውፊት ካለፈው ትውልድ እስከዛሬ የዘለቀ እና ለመጪው ትውልድም የሚተላለፍ ኢትዮጵያዊ ባህላችን ነው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

በመንፈሳዊም ሆነ በመደበኛ አስተምህሮዎች የሰላም እና የፍቅር መሰረት የሆኑ ትርክቶችን ለትውልድ በሚገባ በማውረስ ተደራሽ እንዲሆኑ በትኩረት መስራት እንደሚገባም በመልዕክታቸው አንስተዋል፡፡

ይህ ከሆነ ሀገር ሰላም ይሆናል፣ ልማት ይፋጠናል፣ ድህነትና ጉስቁልና ከሀገራችን ይርቃል፤ ሀገራችንም በቃልም ሆነ በተግባር የከበረችና የገነነች ትሆናለች ብለዋል፡፡

አክለውም፣ “ንግስት ኢሌኒ መስቀሉን ለማግኘት እጅግ ከባድ ፈተና አልፋለች፤ ብዙም ፈልጋለች፤ ብዙም ደክማለች፤ የብዙዎች ትብብር አንድነት እና ህብረት ተዳምሮ ግን ጥረቷ እንዲሳካ አድርጎታል። ልፋቷ ከንቱ አልነበረም፤ ድካሟም ባዶ አልቀረም፤ ዛሬ የምናከብረው በዓልም የብዙዎች ልፋት፣ ድካም እና ጉልበት ተሰባስቦ መስቀሉ እንዲገኝ ምክንያት በመሆኑ ነው” ብለዋል፡፡

የሀገራችንን እድገትና ብልጽግና ለማረጋገጥ የብዙዎችን ጥረት እና ድካም ይጠይቃል፤ ጠንካራ ስራ እና ልፋትም ይፈልጋል ያሉት ወይዘሮ ሸዊት፣ ከድካም በኋላ ደስታ፣ ከልፋት በኋላ ውጤት እንደሚኖር ትናንት የተጓዝንባቸው መንገዶች እንደሚጠቁሙ ተናግረዋል፡፡

ዓባይን በተባበረ ክንድ ተነስተን እንዳሳካነው ሁሉ በርካታ የምናሳካቸው የጋራ ድሎች ከፊታችን አሉ ያሉት ሚንስትሯ፣ ይህን ለማድረግ በህብረትና በአንድነት ቆርጠን ተነስተናል ብለዋል። በዓሉ የሰላም፣ የፍቅር የመደጋገፍ እና የመረዳዳት እንዲሆን መልዕክታቸውን አስተላለፈዋል፡፡

# የኢትዮጵያን ከፍታ ማረጋገጫ ማህተም

- ሀገራዊ ዕድገትን በፅኑ መሰረት ላይ ለመገንባት ከተፈጥሮ ጋር የተስማሙ የተለያዩ የኃይል አማራጮችን ማልማት እንደሚገባ ተጠቁሟል

**በመለሰ ተሰጋ**



ፎቶ- ከገፀ ድር

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ድ/ር) ከሩሲያው ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጋር የኒውክለር ኃይል ማመንጫ ለማልማት ስምምነት በተፈራረሙበት ወቅት

በዓለማችን ትንሽ የኤሌክትሪክ ኃይል የምትጠቀም ሀብታም ሀገር ወይም ብዙ ኃይል የምትጠቀም ድሃ ሀገር የለችም፤ ይላል 'The Energy for Growth Hub' እ.ኤ.አ መጋቢት 7 ቀን 2023 ይፋ ያደረገው መረጃ፡፡

የኃይል እጥረትን ለማስወገድ ዓለም አቀፍ ምሁራን በጥናታዊ መረጃ የተደገፉ መፍትሔዎችን የሚያመላክቱበት ማዕከል 'The Energy for Growth Hub' (ኢነርጂ በኢኮኖሚ እድገት ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?) በሚል ርዕስ ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት የኤሌክትሪክ ኃይል ለሁሉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ሞተር አሊያም የደም ሥር ነው፡፡

የኤሌክትሪክ እጥረት ጉዳቱ ከግለሰብ እስከ ሀገር እና አህጉር ከፍ ያለ ነው የሚለው የምሁራኑ መረጃ፣ ለአብነትም የኤሌክትሪክ እጥረት አንድን ግለሰብ በከፍተኛ ሙያ የመቅጠር ዕድልን ከ35 እስከ 41 በመቶ እንዲሁም በግል ስራ ተሰማርቶ ውጤታማ መሆንን ከ32 እስከ 47 በመቶ እንደሚቀንስ በጥናት ተረጋግጧል፡፡

እንደ መረጃው ከሆነ እ.ኤ.አ በ2045 በአፍሪካ ካሉ ሀገራት መካከል ናይጄሪያን ብቻ በዋቢነት ብንጠቅስ ከዩናይትድ ስቴትስ የሚበልጥ ህዝብ ይኖራታል፡፡ ነገር ግን ከአሜሪካ የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም 2 በመቶውን ብቻ ለማግኘት የሚያስችል መንገድ ላይ ትገኛለች ሲል አሳሳቢነቱን ጠቁሟል፡፡

በመሆኑም በሚሊዮን የሚቆጠሩ አፍሪካውያንን ከድህነት ለማላቀቅ ከተፈለገ ሀገራት በተለይም አፍሪካውያን የኃይል ምንጫቸውን ሊያሳድጉና ሊያሰፉ እንደሚገባ ምሁራኑ በዓለም አቀፉ ህብረታቸው በኩል የመፍትሔ ሀሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡

ይህንን ዕውነት በውል የተረዳችው ኢትዮጵያም ያለፈውን፣ የአሁኑን እና በተለይም መጭውን ዘመን ታሳቢ በማድረግ ሀገራዊ ዕድገትን በፅኑ መሰረት ላይ ለመገንባት ከተፈጥሮ ጋር የተስማሙ የተለያዩ የኃይል አማራጮችን በማልማት ላይ ናት፡፡

ለአብነትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ባሳለፍነው ሐሙስ መስከረም 15 ቀን 2018 ዓ.ም ከሩሲያው ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጋር የኒውክሌር ልማትን አስመልክቶ የሁለትዮሽ ውይይት ማድረጋቸው አይዘነጋም፡፡ በዚሁ ወቅት ባስተላለፉት መልዕክትም ኢትዮጵያ በቀጣይ በኒውክሌር ቴክኖሎጂ ላይ በትኩረት ትሰራለች ብለዋል፡፡

በውይይታቸውም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፣ ኢትዮጵያ የንቁ ወጣቶች መገኛ መሆኗን ጠቅሰው፣ ከተሞች እየዘመኑና ኢንዱስትሪዎቿም እያደጉ፣ ኢኮኖሚዋም በዓለም ፈጣን ዕድገትን እያስመዘገበ መምጣቱን አመላክተው ኢትዮጵያ በወሳኝ የዕድገት ጎዳና ላይ እንደምትገኝም ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በአረንጓዴ ኃይል ዘርፍ ምሳሌ ሆና መቆየቷን ያስታወሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ለአብነትም በቅርቡ ተጠናቅቆ ለምረቃ የበቃው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በዘርፉ ያላትን ቁርጠኝነት እንደሚያሳይም አስታውቀዋል፡፡

ራዕያችን ከዛሬ የተሻገረ በመሆኑ የተለያዩ የልማት አማራጮችን ተግባራዊ እናደርጋለን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፣ በቀጣይነት በኒውክሌር ቴክኖሎጂ ዘርፍ በትኩረት እንደሚሰራ ጠቁመዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ የኒውክሌር ቴክኖሎጂ ለኢትዮጵያ እድገት ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰው፣ ለአብነትም ለህክምና፣ ለምግብ ዋስትና፣ ለውሃ አስተዳደር እንዲሁም ለኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው አስገንዝበዋል፡፡

ዓለም አቀፉ የኒውክሌር ማህበር እ.ኤ.አ ሰኔ 17 ቀን 2025 የኒውክሌር ኃይል ታሪክ (The History of Nuclear Energy) በሚል ርዕስ ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት እ.ኤ.አ በ1939 እስከ 45 ባሉት ዓመታት አብዛኛው ልማት በአቶሚክ ቦምብ ላይ ያተኮረ ነበር። ከ1945 ጀምሮ ግን ይህንን ኃይል ኤሌክትሪክን ለማምረት ቁጥጥር ባለው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል በትኩረት መሰራት ተጀመረ፡፡

ይህንን ተከትሎም ቀላል የማይባሉ ሀገራት የኒውክሌር ኃይልን ለልማት በማዋል ከፍታቸውን ጨመሩበት። ክንዳቸውንም አፈረጠሙበት፡፡ ለአብነትም አሜሪካ፣ ቻይና፣ ፈረንሣይ፣ ሩሲያ እና ደቡብ ኮሪያን የመሳሰሉ ሀገራት የዕድገታቸው አንዱ ምስጢር ይሄው የኒውክሌር ኃይል ነው ይላል መረጃው፡፡

እንደ ዓለም አቀፉ የኒውክሌር ማህበር መረጃ በፈረንሣይ እ.ኤ.አ ከ1970ዎቹ አካባቢ የአንድ በርሚል የነዳጅ ዋጋ በአምስት እጥፍ ጨመረ፡፡ ይህንን ተከትሎ በሀገሪቱ ከፍ ያለ ድንጋጤን ፈጠረ፡፡ ከዚህ ድንጋጤ በኋላም ፈረንሳይ የኃይል ነፃነቷን ለማስጠበቅ እና የተረጋጋና ዝቅተኛ ዋጋ ያለው ኤሌክትሪክ ለማቅረብ በመንግስት የሚመራ የኒውክሌር ኃይል ግንባታን በስፋት ጀመረች፡፡

መንግስት የተከተለውም ይህ አዋጭ ፖሊሲ ፈረንሳይ 70 በመቶ የሚሆነውን ፍጆታዋን ከኒውክሌር ጣቢያዎቿ እንድታገኝ አስቻለ፡፡ ይህ ኃይል በፈረንሳይ የኢንዱስትሪ ኤሌክትሪክ ዋጋን ማረጋጋት፣ ኢነርጂ-ተኮር ኢንዱስትሪዎችን በመደገፍ፣ ምርትና ምርታማነታቸውን እንዲጨምር በማድረግ የሀገሪቱን ሁለንተናዊ ተወዳዳሪነትና ብልፅግናዋን ከፍ አደረገ፡፡

ደቡብ ኮሪያም እ.ኤ.አ ከ1970 እስከ 2000ዎቹ ባለው ጊዜ ውስጥ አስተማማኝ፣ በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ዋጋ ያለው የኤሌክትሪክ ኃይልን ወደ ውጭ መላክን ታሳቢ ያደረገ የኒውክሌር ግንባታን በትኩረት መስራት ጀመረች። ይህም የደቡብ ኮሪያ የኒውክሌር ስትራቴጂ ሀገሪቱን የተረጋጋ የኢንዱስትሪ ዕድገትና መስፋፋት፣ ወጥነት ያለው የቴክኖሎጂ ፈጠራና የኤክስፖርት ዕድገት ተምሳሌትና መድረክ እንድትሆን አደረጋት ይላል ዓለም አቀፉ የኒውክሌር ማህበር መረጃ፡፡

ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት በዋቸሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር ሙሉጌታ አስፋው በበኩላቸው ያደጉ ሀገራት በታላላቅ መድረኮች ይጠቅመናል ብለው፣ ያሰቡትን አጀንዳ በሌሎች ላይ የሚጭኑበት ምስጢር አንዱና ዋናው የኢኮኖሚ ጉልበት ነው፡፡ ለዚህ ኢኮኖሚ ከፍታቸው ደግሞ የኤሌክትሪክ ኃይል የማምረት አቅማቸው ወሳኝ ድርሻ አለው። በመሆኑም እንደ ሀገር በኢኮኖሚ ከፍ ብሎ ለመታየት ኢኮኖሚውን የሚያንቀሳቅስ ኃይል ግድ እንደሚል ተናግረዋል፡፡

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ለብልፅግናዋ ከፍታ አስተማማኝ መሰረት መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ከተፈጥሮ የተወዳጁ የተለዩ የኤሌክትሪክ ኃይል አማራጮችን በማልማት ላይ ትገኛለች፡፡ ለአብነትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጳጉሜን 4 ቀን 2017 ዓ.ም የህዳሴውን ግድብ መርቀው በከፈቱበት ወቅት ይፋ ካደረጓቸው አዳዲስ እና ዋና ዋና ፕሮጀክቶች መካከል የኒውክሌር ኃይል ልማትን ለሰላማዊ ዓላማ ማዋል የሚለው አንዱ መሆኑ አይዘነጋም፡፡

በጎንደር ዩኒቨርሲቲ የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ ይንገስ አለሙ (ዶ/ር) እንደሚሉትም መሰል የኤሌክትሪክ ኃይል ኢንዱስትሪን ከፍ በማድረግና በማስፋፋት፣ ምርታማነትን በማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ዕድገትን በማጎልበት እና አጠቃላይ የኑሮ ደረጃን በማሻሻል ለሀገር ብልጽግና ወሳኝ ሚና ይጫወታል።

አስተማማኝ የኤሌክትሪክ ኃይል ማግኘት የሀገር ኢኮኖሚያዊ አውታሮች በብቃት እንዲንቀሳቀሱ ያደርጋል፤ አዳዲስ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን በመፍጠር ድህነትን ይቀንሳል፤ ኢንቨስትመንትን ይስባል፤ ይህ ሁሉ ለዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ ያደርጋል። በመሆኑም የኒውክሌር ኃይልን የመሳሰሉ አዋጭ የኤሌክትሪክ ኃይል አማራጮችን መጠቀም በኢኮኖሚ የጠነከረች ኢትዮጵያን ለመገንባት ያግዛልም ብለዋል፡፡

መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የኒውክሌር ኃይል አተሞች ለሁለት እና ከዚያ በላይ ተሰባብረው (ኒውክለስ) ሲብላሉ የሚለቁት ኃይል ነው። በመሆኑም በመላው ዓለም ኒውክሌርን በማብላላት የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት የተለመደና አዋጭ መንገድ ነው፡፡

ተሰባብረው የተብላሉት አተሞች በሚለቁት ሙቀት የሚፈላው ውሃ እንፋሎት በመፍጠር ተርባይኖችን እና ጀነሬተሮችን በማንቀሳቀስ ኤሌክትሪክ ይመረታል። የኒውክሌር ኃይል ማመንጫ ጣቢያ (ኒውክሌር ፕላንት) አብላልቶ ሙቀት ለማምረት 'ዩራኒየም-235' የተባለውን ንጥረ ነገር እንደ ነዳጅ እንደሚጠቀም ዓለም አቀፉ የኒውክሌር ማህበር መረጃ ይጠቁማል፡፡

**የኒውክሌር ኃይል በቀን ለ24 ሰዓታት የአየር ንብረት ሁኔታ ሳይበግረው ኃይል የማመንጨት ብርቱ አቅም አለው**

የኒውክሌር ኃይል እንደ ሌሎች ታዳሽ ኃይሎች ሳይሆን በቀን ለ24 ሰዓታት የአየር ንብረት ሁኔታ ሳይበግረው ኃይል የማመንጨት ብርቱ አቅም እንዳለው የሚጠቅሰው የዓለም አቀፉ የኒውክሌር ማህበር መረጃ በአንድ ኪሎ ግራም ዩራኒየም የሚመረት የኒውክሌር ኃይል በከሰል ከሚመረተው ኃይል በ20 ሺህ እጥፍ የሚበልጥ ነው፡፡

ከዓለም ከፍተኛ የኒውክሌር ኃይል በማምረት ቀዳሚዋ ሀገር አሜሪካ ስትሆን፤ የኒውክሌር ኃይል ከአጠቃላይ የኃይል አቅርቦቷ 19 በመቶውን ይሸፍናል። ፈረንሳይ ከቻይና በመቀጠል የዓለም ሦስተኛዋ ከፍተኛ ኒውክሌር ኃይል አምራች ስትሆን፤ ከአጠቃላይ የኃይል አቅርቦቷ 70 በመቶ በላይ ኃይሏን ከኒውክሌር ኃይል በማግኘት ቀዳሚዋ ሀገር ናት። የኒውክሌር ኃይል ስምምነት ከኢትዮጵያ ጋር የተፈራረመችው ሩሲያ የዓለም አራተኛ የኒውክሌር ኃይል አምራች ሀገር ስትሆን 36 ማብላያ ጣቢያዎች አሏት። በአምስተኛ ደረጃ ላይ የተቀመጠችው ደቡብ ኮሪያ ደግሞ 26 ማብላያ ጣቢያዎች ሲኖሯት አንድ ሦስተኛውን የኤሌክትሪክ ፍጆታዋንም ከኒውክሌር ኃይል ታገኛለች፡፡

ኢትዮጵያ የኒውክሌር ሳይንስና ቴክኖሎጂን ለሰላማዊ ዓላማ ማለትም ለኃይል አቅርቦት፣ ለምርምር፣ ለጤና፣ ለግብርና፣ ለኢንዱስትሪ እና ለአካባቢ ጥበቃ መጠቀም ያስችላት ዘንድ እ.ኤ.አ ከ1957 ጀምሮ የዓለም አቀፍ አቶሚክ ኢነርጂ ኤጀንሲ (IAEA) አባል መሆኗን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል፡፡

# የአደባባይ በዓላት በብርሃናማዋ ከተማ

- **የመስቀል ደመራ እና ኢሬቻ በዓላት ከኮሪደር ልማቱ ጋር የሚፈጥሩትን ውብ እና አይረሴ ድባብ በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ ተመላክቷል**



ፎቶ-ከፋይል
የመስቀል ደመራ በዓል ከፊል ገጽታ

ፎቶ-ከፋይል
የ2017 ዓ.ም የሆራ ፊንፊኔ ኢሬቻ ክብረ በዓል ከፊል ገጽታ

**በመለሰ ተሰጋ**

ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ከተሞችም መልክና ልክ፣ ማንነትና ዕውነት አላቸው፡፡ የከተማ ልማት ባለሙያዎች ሲንጋፖርን ሁሉን አቀፍ ከሆነ ጠንካራ የሀገረ መንግስት ግንባታ፣ ሞንትሪያልን በቋንቋ ብዝሃነት፣ ሆንግ ኮንግን ከንግድ እንቅስቃሴ፣ ቤጂንግን በፖለቲካ ማዕከልነት፣ ኦክስፎርድን ከትምህርት፣ ኒው ዮርክን ከብዙዎች ምኞትና ከምኞት የተዋደዱ ከተሞች ናቸው ይላሉ፡፡

በርግጥም ሁሉም ከተሞች እንደ ስሪታቸው፣ እንደ ታሪካቸው እና እንደ ዕጣ ፋንታቸው የራሳቸው ማንነት እንዳላቸው የከተማ ልማትና ፖለቲካል ሳይንስ ተመራማሪዎቹ ፕሮፌሰር ዳንኤል ኤ. ቤል እና አቨነር ዴ ሻሌት የከተሞች መንፈስ (The Spirit of Cities: Why the Identity of a City Matters in a Global Age) በሚል ርዕስ ፕሪንስተን ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ እ.ኤ.አ 2011 ባሳተመው ጥናታዊ መፅሐፋቸው ላይ አስፍረውታል።

ዋና መቀመጫውን ኒው ዮርክ ከተማ ያደረገው ዓለም አቀፉ የበይነ መረብ ሚዲያ ተቋም "Youth Journalism International" እ.ኤ.አ ታህሳስ 15 ቀን 2020 "Diversity and wonder in Addis Ababa" በሚል ርዕስ ባስነበበው መጣጥፍ አዲስ አበባን ብዝሃነት ጎልቶ፣ ደምቆና ፈክቶ የሚታይባት 'የሁሉም ቤት' የሆነች ከተማ በማለት ገልጿታል፡፡

እ.ኤ.አ ጥር 2021 "Cities and Identities" በሚል ርዕስ በታተመ መፅሐፍ እንደሰፈረውም የከተሞች ውበት ከማንነታቸው ይመነጫል፡፡ ከተሞች የማይደበዝዝ ውበት፣ የማያልቅ ቁንጅና እንዲሁም እንደ መስታወት ሁሉንም በልኩ የሚያሳይ ገፅታ ይኖራቸው ዘንድ የነዋሪዎቻቸውን ባህልና ማንነት ማክበር፣ ሁሉም እንደ እምነቱ፣ ባህሉና ወጉ ዘና የሚልባቸው ሳሎኑ፣ አረፍ የሚልባቸው መኝታ ቤቱ ሲያሻውም የሚቦርቅባቸው መስኩ መሆን እንዳለባቸው ተመላክቷል።

በርግጥም አዲስ አበባ ህብረ ብሔራዊነት ከፍ ብሎ የሚታይባት፣ ብዝሃ ባህል እንደ ከዋክብት የሚደምቁባት፣ የሁሉም ቤት የሆነች ከተማ መሆኗን ለማረጋገጥ ከነሐሴ አጋማሽ እስከ መስከረም ማብቂያ የሚከበሩ እንደ መስቀልና ኢሬቻ ያሉ የአደባባይ በዓላትን መመልከት በቂ ነው፡፡

በተለይም በደማቁ የመስከረም ወር የሚከበሩት የመስቀልና የኢሬቻ በዓላት ለአዲስ አበባ እንደ አደይ አበባ ሲያም እንደ መስቀል ወፍ ተናፋቂዎች ናቸው፡፡ በዓላቱ በሚከበሩበት ወቅት እንደ ዐባይ ወንዝ ከብዙ ማንነቶች የመነጨ ውበት በህብረ ቀለማት ተሸምኖ በየጎዳናዎቹ ሰላምና ደስታን እየዘራ ይገማሸራል፡፡

ወዲህ ደግሞ እንኳን ተኳኩላ ሹርባ ተሰርታ፣

ልቤ ፍስስ ይላል ቤቷን ያየሁ ለታ፡፡

እንዲል የሀገሬ ኮበሌ አዲስ አበባ መንገዶቿ በመልክ በረድፉ ተሰድረው፣ ሕንፃዎቿ ልክ እንደ ሙሽራ ቀልብን በሚገዙ ቀለማት ተኩለው፣ መናፈሻዎቿ ሰፍተውና ፋፍተው፣ ቀበናን የመሳሰሉ ወንዞቿ ፀድተውና ወዝተው፣ የመስቀል አደባባይን የመሳሰሉ የበዓላት ማድመቂያ ስፍራዎች እንደ አደይ አበባ አጊጠው፣ እንደ መስቀል ወፍ ተሽቀርቅረው፣ እንደ ንጋት ሐይቅ በራስ አቅምና እውቀት እንዳሻቸው ተንጣለው በኮሪደር ልማቱ ብርሃን ከዘመን ጋር እኩል በተገለጡበት ወቅት የሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል በርግጥም ልዩ ነው፡፡

ከዝግጅት ክፍላችን ጋር ቆይታ ያደረጉት በቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ፕሮሞሽን መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተሾመ ተክሉም ከላይ በጠቀስናቸው ሀሳቦች ይስማማሉ፡፡ መስቀልና ኢሬቻን የመሳሰሉ የአደባባይ በዓላት በቱሪዝሙ ከፍታ ላይ ትልቅ ሚና አላቸው፡፡ በዓላቱ በዓመት አንዴ ወይም ሁለቴ የሚከበሩ በመሆናቸው ተናፋቂነታቸው ይጨምራል፡፡

ከዚህም ባሻገር መቼ፣ እንዴትና የት ይከበራሉ? የሚለው ጉዳይ በቱሪስቶች ዘንድ ቀድሞ የሚታወቅ ነው የሚሉት አቶ ተሾመ፣ በዚህ መሰረትም የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ጎብኚዎች በበዓላቱ ለመታደም ቀደም ብለው ያቅዳሉ፡፡

በዓላቱን አስታከውም የተለያዩ ቦታዎችን መጎብኘት የሚያስችላቸውን ፓኬጅ ይገዛሉ፡፡ ከተለያየ ማንነትና አካባቢ በአንድ ስፍራ የተሰባሰቡ እና በልዩ ልዩ አልባሳት ያጌጡ ኢትዮጵያውያን ከጎብኚዎቻቸው ጋር በአንድ ልብና መንፈስ ሲደሰቱ ማህበራዊ መስተጋብራችንን የበለጠ ያጣምሩታል፤ ያሳድጉታል፤ ያጣፍጡታል፡፡ በዓለም መድረክ ያለንንም በጎ ስም በደማቁ ይፅፉታል ይላሉ አቶ ተሾመ ተክሉ፡፡

እንደ መስቀል ያሉ በዓላት በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት (UNESCO) የተመዘገቡ በመሆናቸው ከኢትዮጵያውያን አልፈው የሰው ልጅ ሁሉ የጋራ ሀብት ሆነዋል። ይህንንም ተከትሎ እንደ መስቀል ያሉ በዓላት ሲከበሩ የዓለም ዐይንና ልብ ወደ ኢትዮጵያ ያማትራል፡፡

በዚህ ላይ ደግሞ አዲስ አበባ ለአደባባይ በዓላት የበለጠ ምቹ ሆናለች። የመስቀል በዓልን ደግሞ የኃይማኖቱና የእሴቱ ባለቤት ከሆኑት ባሻገርም ሁሉም በጉጉት ይጠብቀዋል፡፡ ስለሆነም ዛሬ ላይ ሆነን የመስቀል ደመራን፣ የአዲስ አበባን ማራኪ ውበት እና ቱሪዝምን ስናስብ ከፍ ባለ ሞራልና አቅም ነው፡፡

ቱሪዝም ቢዝነስና መዝናኛዎችን የያዘ ነው የሚሉት አቶ ተሾመ መዝናናት ደግሞ ዐይንም፣ ልብም፣ ቀልብም እኩል የሚደሰቱበት ነው፡፡ በመሆኑም መዝናናትን ስናስብ ዐይንም፣ ልብም እንዲሁም ዐዕምሮም ሰብሰብ ብለው ጥሩ ነገር የሚያዩበት፣ የሚያስቡበት እና የሚደሰቱበት ነው፡፡ አዲስ አበባም ደግሞ ለዚህ ምቹ ሆናለች፡፡

ከተማዋ አሁን በጣም የለማችና የተዋበች ሆናለች የሚሉት አቶ ተሾመ፣ ይህንንም ዓለም እየመሰከረ ነው፡፡ ከተዋቡት የከተማዋ ስፍራዎች አንዱ ደግሞ የመስቀል አደባባይ ነው፡፡ ይህ አደባባይ ከበፊቱ በተለየ ማራኪ ውበትና ምቾትን ተጎናፅፏል፡፡

ይህም የበዓሉ ታዳሚዎች ያለምንም መጨናነቅ የሚያከብሩበትን ዕድል ፈጥሯል፡፡ ቱሪስቶችም ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎችና ዓለማት ወደ ከተማዋ ሲመጡ ከመቼውም ጊዜ በላይ በየቀኑ በአስደማሚ ለውጥ ውስጥ ባለችው ከተማ ዘና እያሉ ደስታቸውን እንዲያጣጥሙ ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር በዓል እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

መስቀል በዩኔስኮ የተመዘገበ መሆኑ፣ አዲስ አበባ ደግሞ በኮሪደር ልማት መዋቧ እና እንደ ከተማም ሆነ እንደ ሀገር ልዩ ልዩ የቱሪስት መዳረሻዎች በመገንባታቸው የጎብኚዎች ቁጥር ይጨምራል፤ የሀገርን ገፅታ የበለጠ ለመገንባት ያግዛል፤ በቱሪዝም ኢኮኖሚው ላይም ትልቅ አቅምን ይፈጥራል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ተሾመ ማብራሪያ የመስቀል በዓል ከአዲስ አበባ ውብ የኮሪደር ገፅታ ጋር የሚፈጥራው ድባብ ቱሪስቶች የቆይታ ጊዜያቸውን እንዲያራዝሙ፣ እንደ አንድነት ፓርክ፣ ብሔራዊ ቤተ መንግስት፣ የዐድዋ ድል መታሰቢያ፣ ሳይንስ ሙዚየምን እና እንጦጦ ፓርክን የመሳሰሉ ስፍራዎችን እንዲጎበኙ ዕድል ይፈጥራል፡፡

የመስቀል ደመራ በዓል ከኮሪደር ልማቱ ጋር የሚፈጥረውን ውብ እና አይረሴ ድባብ በአግባቡ መጠቀም ይገባል የሚሉት አቶ ተሾመ፣ ይህ ደግሞ በአንድ አካል ብቻ ሳይሆን ሁሉም እንደ ኃላፊነቱ የሚተገብረው ነው ብለዋል፡፡

በቱሪዝሙ ዘርፍ ከሚጠበቁ ተግባራት መካከልም በመንግሥት የሚከናወን መሰረተ ልማት የማሟላት ሥራ፣ የግል ባለሀብቱና መሰል አገልግሎት ሰጪ አካላት እንዲሁም በግልና በመንግስት የሚከናወኑ የማስተዋወቅና መሰል ስራዎች አሉ፡፡

ይህንንም ተከትሎ መንግሥት ከሞላ ጎደል በተለይ እንደ አዲስ አበባ መሰረተ ልማቱን አሟልቷል፡፡ በመሆኑም አሁን በትኩረት መስራት ያለብን የአገልግሎት አሰጣጥና ጥራትን ማሻሻል፣ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብና ከገንዘብ ባሻገር ያለውን የሀገር ገፅታ ግንባታን ማስቀደም፣ ዓለም በተምሳሌትነት የሚጠቅሰውን እንግዳ ተቀባይነታችንን የበለጠ አጉልቶ ማሳየት፣ በየአካባቢው ያለ ዜጋ ቱሪስቶችን ማገዝ፣ መንገድ መምራት እና በቂ መረጃ በመስጠት ሌሎች ቦታዎችንም እንዲጎበኙ በማነሳሳት ዕድሉን በሚገባ መጠቀም አለብን ብለዋል አቶ ተሾመ ተክሉ፡፡

ልክ እንደ ህብረ ብሔራዊነታችን ከተለያዩ ስፍራዎች የተሰባሰቡ ችቦዎች፣ በአደይ፣ በአሽከት እና በቄጤማ ደምቀው በሰፊው ሜዳ ላይ ትልቅ ደመራን ይፈጥራሉ፡፡ በዚህ ወቅት መስቀል አደባባይ መሽት ሲል ደመራው ሲለኮስ ከፍ ብሎ ከሚታየው የብርሃኑ ፀዳል ጋር በኮሪደር ልማቱ እንደ አዲስ የተወለደችውን ከተማ መመልከት ልብን በሀሴት ያረሰርሳል፡፡

# አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ

## “ህብረተሰቡንና የፀጥታ ተቋማትን የማገናኘት ስራውን አጠናክሮ መቀጠል አለበት”

**የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገ/ሚካኤል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

ከተሞች ለስራ፣ ንግድና ቱሪዝም እንቅስቃሴ ምቹና ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ሁኔታዎች መካከል የተሟላ ሰላምና ደህንነት የመኖር ጉዳይ አንዱ ነው፡፡ ዜጎች በሰላም ወጥተው የሚገቡበትን ሁኔታ የፈጠሩ፣ ሰላምና ደህንነታቸውን ያረጋገጡ፣ ዝቅተኛ የወንጀል ምጣኔ ያለባቸው ከተሞች ለኑሮ ተመራጭ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካውያን መናኸሪያ፣ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ፣ በዓለም ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ ማዕከል የሆነችውን አዲስ አበባ ሰላሟንና ደህንነቷን አጠናክሮ ለማስቀጠል በርካታ ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ በከተማዋ ወንጀልን አስቀድሞ በመከላከል፣ ሰላም፣ ደህንነትንና የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ከተለያዩ የፀጥታ አካላት ጋር በመቀናጀት ከፍተኛ ሚና እየተወጡ ካሉ ተቋማት መካከል የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ አንዱ ነው፡፡


ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈጻሚ ከማኔጅመንት አባላት ጋር የፌዴራል ፖሊስን የሪፎርም ስራዎች ከጎበኙ በኋላ ከተቋሙ ከፍተኛ አመራሮች ጋር በተወያዩበት ወቅት

ረጅም ዓመታትን ያስቆጠረውና አንጋፋው የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ፣ ሪፎርም በማካሄድ ወንጀልን አስቀድሞ በመከላከልና ሰላምንና የህግ የበላይነትን የማረጋገጥ ተልዕኮውን በብቃት መወጣት የሚችል ተቋም መሆን ችሏል፡፡ ከትናንት በስቲያም የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ እና የማኔጅመንት አባላት በተቋሙ በመገኘት በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና በተለያዩ ጉዳዮች ያከናወናቸውን የሪፎርም ስራዎችን ጎብኝተዋል፤ ከተቋሙ አመራሮች ጋርም ውይይት አድርገዋል፡፡

በውይይቱ ወቅት የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ገ/ሚካኤል ፌዴራል ፖሊስ ወንጀልን አስቀድሞ በመከላከል እና ከተማዋ ደህንነቷ የተጠበቀና ዜጎቿ ያለ ስጋት የሚንቀሳቀሱባት እንድትሆን ለማስቻል የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝ አብራርተዋል፡፡

አዲስ አበባ በርካታ ዓለም አቀፍ ተቋማት የሚገኙባት፣ ዲፕሎማቶች የሚኖሩባት፣ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ቱሪስት የሚጎበኛት ከተማ ናት፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገች፣ እየተዋበችና እያማረች በመምጣቷ ቀጣናዊ፣ አህጉር እና ዓለም አቀፍ ትላልቅ ጉባኤዎች በስፋት እየተካሄዱባትና ተመራጭ እየሆነች መጥታለች፡፡

ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫቸውን በከተማዋ ሲያደርጉ፣ ዓለም አቀፍ ጉባኤዎችና ኮንፈረንሶች ለማድረግ ሲታሰብ አስቀድሞ ከግምት የሚገባው የከተማዋ ሰላምና ደህንነት የተጠበቀ መሆን ነው፡፡ የሰላምና ደህንነት መረጋገጥ ከተማዋ ትላልቅ ጉባኤዎችን የመሳብ አቅሟ እንዲጨምር ያደርጋል፡፡

አሁን ላይ አዲስ አበባ በአፍሪካና በዓለም አቀፍ ደረጃ ዝቅተኛ የወንጀል ምጣኔ የሚመዘገብባት፣ የተሻለ ሰላምና ደህንነት ያላት ከተማ ነች፡፡ ለዚህ ውጤት መገኘትም የፀጥታና ደህንነት ተቋማት፣ የህብረተሰቡና የከተማ አስተዳደሩ ተቋማት ቅንጅት ትልቁን ድርሻ እንደሚይዝ ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ተናግረዋል፡፡

የፌደራል ፖሊስም እንደ አንድ የፀጥታ አካል ተልዕኮውን ለመወጣት ባደረገው ሪፎርም የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡ ከእነዚህም መካከል ህዝቡ በቀላሉ የፖሊስ አገልግሎት ሊያገኝ የሚችልበት የዜጎች ተሳትፎ መተግበሪያ (EFPApp) በማልማት ስራ ላይ ማዋሉን ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ ተናግረዋል። መተግበሪያው ህብረተሰቡ ከፖሊስ በቀላሉ የሚፈልገውን አገልግሎት የሚያገኝበት፣ ወቅታዊ የሰላምና ፀጥታ መረጃዎች የሚለዋወጥበት፣ በራሱ ፖሊስ ሆኖ አካባቢውና ከተማዋ የሚጠበቅበት ዕድል የሚፈጥር ስለሆነ መተግበሪያውን በስፋት እንዲጠቀምበት በማስተዋወቅ ረገድ የመገናኛ ብዙሃን ሚና የላቀ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ህዝብና መንግስትን እንደ ድልድይ ሆኖ በማገናኘት እየሰራቸው ያሉ ስራዎች ይበል የሚያሰኙ መሆናቸውን ያነሱት ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ፣ ወንጀልን ለመከላከል የሚደረጉ ጥረቶችና በከተማዋ ውስጥ የሚከናወኑ ሁሉን አቀፍ ልማቶች ከህዝብ ለማድረስ የሚሰራውን ስራ አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

“አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የከተማዋን ስያሜ የያዘ በመሆኑ በከተማዋ የሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ላይ ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ህብረተሰቡ ከምንም በላይ በሰላም ወጥቶ በሰላም እንዲገባ ደህንነቱ እንዲረጋገጥለት ይፈልጋል፡፡”

> **“አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በከተማዋ የሰላምና ፀጥታ ጉዳይ ላይ ቅድሚያ ሰጥቶ መስራት ይጠበቅበታል”**

ያሉት ኮሚሽነር ጀነራል ደመላሽ፤ ከዚህ አኳያ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የሚሰራቸው ስራዎች በአዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን በሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ደረጃም ጭምር ተደራሽ በመሆናቸው በእውነት ላይ በመመስረት ህብረተሰቡና መንግስት፣ ህብረተሰቡና የፀጥታ ተቋማትን ማገናኘት የሚችል በጣም ጥሩ የሚባል ስራ መስራቱን አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

በኢትዮጵያ የፌዴራል ፖሊስ የወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ አዛዥ ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መላኩ ፈንታ እንዲሁ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ፖሊስ በሚሰራው ስራ ደጋፊ በመሆን እየሰራ ያለው ስራ አበረታች መሆኑን አንስተዋል። “የእኛ ተቋም ሰፊ ሪፎርም በማድረግ ብዙ ስኬት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ በሰው ሀይል፣ በሎጂስቲክስ፣ በቴክኖሎጂና በአፈጻጸም የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኝ፤ በመላ ሀገሪቱ ስምሪት ወስዶ የሚሰራ ተቋም ነው፡፡ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እኛ ለምንሰራው ስራ ከፍተኛ እገዛ እያደረገ ነው፡፡ የአዲስ አበባ ፖሊስና ፌዴራል ፖሊስ ሰላምና ፀጥታን ከማስጠበቅ ጋር በተያያዘ የሰሯቸውን መልካም ስራዎች ያሰራጫል፡፡ ከህዝብ የሚገኙ መረጃዎችን ለፖሊስ ያቀርባል፡፡ ታማኝና ተጨባጭ መረጃዎችን በመስጠት ጠንካራ የሚዲያ ተቋም እንደሆነ በተለያየ ጊዜ አይተነዋል” ብለዋል፡፡

የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ ካሳሁን ጎንፋ በበኩላቸው በፌዴራል ፖሊስ የተካሄደው ሪፎርም ስኬታማና ለአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም ጥሩ ግብአት መሆን እንደሚችል ተናግረዋል፡፡ “ኢትዮጵያ ከብዙ ዓመታት በኋላ አሁን ላለችበት ደረጃ እንድትደርስ የፌዴራል ፖሊስ ትልቅ ድርሻ ተወጥቷል። ተቋሙ ባደረገው ሪፎርም የተገኘውን ውጤት በተጨባጭ እያየነው ነው፡፡ ወደ ህዝብ ቀርቦ በሚሰጠው ምላሽም ተአማኒነትን እያረጋገጠ ይገኛል። ተቋሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳየ ያለው ለውጥ ለሀገራችንና ከተማችን አልፎም ለቀጣናችንም የሚተርፍና ተምሳሌት የሚሆን ነው” ብለዋል፡፡

“የሀገር ፍቅርን ለመማር ከፀጥታ ሀይል የተሻለ ሌላ አካል የለም” ያሉት አቶ ካሳሁን፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክም እንደ ሜትሮፖሊታን ሚዲያ በከተማዋ በቴክኖሎጂ ታግዘው አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን ስራ መመልከት ስለሚያስፈልግ የተቋሙ አመራሮች በአካል በመገኘት ጉብኝት ማድረጋቸውን ተናግረዋል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ለመዲናችን ቀዳሚ የመረጃ ምንጭ መሆን አለበት። መረጃዎችን በቴክኖሎጂ በማስደገፍ በወቅቱ ለህብረተሰቡ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡ አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካ ዋና መናኸሪያና የዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲ ማዕከል ናት። የፌዴራል ፖሊስ ከሌሎች የፀጥታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት፣ በቴክኖሎጂ በመታገዝ የከተማውን ሰላም እና ፀጥታ በማስከበርና የትራፊክ እንቅስቃሴን በማሳለጥ በኩል የሚሠራቸው ተግባራትን በመከታተል ለሕዝብ ተደራሽ በማድረግ እንደሚሰራ ጠቁመዋል፡፡

አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በአራት የመገናኛ ሚዲያ አውታሮች በቴሌቭዥን፣ ሬዲዮ፣ ዲጂታልና ህትመት መረጃዎችን ለህብረተሰቡ እያደረሰ እንደሚገኝ ያነሱት አቶ ካሳሁን፣ በፌዴራል ፖሊስ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን በመከታተል ለህዝቡ መረጃ ተደራሽ በማድረግ ተመራጭና ተወዳዳሪ የሆነ ሚዲያ ለመሆን እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡ ጉብኝቱ አስደሳች እንደነበር ያነሱት አቶ ካሳሁን፣ አዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ የኢትዮጵያ ፌዴራል ፖሊስ ከደረሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃ ትምህርት በመውሰድና ተቋሙን ከህዝብ ጋር በማገናኘት በቅንጅት እንደሚሰራም ተናግረዋል፡፡



አቶ ጃንጥራር አባይ
የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል
ከንቲባ እና የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ሃላፊ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ
ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION
INDUSTRY DEVELOPMENT BUREAU

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

ከመስከረም ወር ልዩ በዓላት መካከል መስቀል አንዱ ነው። መስቀል የብርሃን፣ የመገለጥ፣ የመታደስ፣ የመዳን፣ የፍቅር ምልክት ተደርጎ የሚወሰድ ሃይማኖታዊ በዓል ነው። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ መስከረም 16 ቀን የሚደመረው ደመራ ሀገራዊ ሀይማኖታዊ በዓል ብቻ ተደርጎ አይወሰድም። የመስቀል ደመራ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) እውቅና ተሰጥቶት ዓለም አቀፋዊ ቅርስ ተብሎ በመመዝገቡ ዓለም አቀፋዊ በዓልም መሆኑን እንረዳለን።

የመስቀል በዓል በመስከረም ወር መከበሩ ከንጋት ብስራት ጋር እናመሳስለዋለን። መስቀል መቃረቡን የመስቀል ወፍም ትነግረናለች። በሀገራችን ወግና ብሂል "ምነው እንደ መስቀል ወፍ በዓመትህ ብቅ አልክ" ይባላል። ይህ አባባል መነፋፈቅን በዓመት አንድ ጊዜ መገናኘትን ያስረዳናል። የመስቀል በዓል በዓመቱ መስከረም ከጠባ በኋላ ወንዞቹ በጠሩበት ሜዳው ባጌጠበት፣ እንስሳቱ በሚቦርቁበት፣ የደፈረሰው በጠራበት፣ ጨለማው በገለጠበት የሚከበር ሀይማኖታዊ በዓል መሆኑ ልዩ ስሜትን የሚፈጥር ሀገራዊም አለማቀፋዊም ሀብት ነው።

ስለሆነም ይህንን ትልቅ ሀይማኖታዊ በዓል በፍቅር፣ በደስታ፣ ሀይማኖታዊ ትውፊቱ ተጠብቆ ለትውልድ እንዲሸጋገር ማድረግ የኛ የኢትዮጵያዊያን ሀላፊነት ስለሆነ በዓሉ በድምቀት እንዲከናወን ማድረግ ይገባል።

## እንኳን ለመስቀል በዓል አደረሳችሁ፤ አደረሰን::





Akaki Polytechnic College

### አቃቂ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ እንኳን ለ2018 ዓ.ም ብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ አደረሰን ይላል!

- በተለይ ደግሞ የአንድነታችን ፍሬ የሆነውና የዘመናት ቁጭት የነበረው የህዳሴ ግድብ ምርቃት ማግስት ላይ መሆናችን ደስታችንን ድርብ ያደርገዋልና እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ደስ አለን!
- አቃቂ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ የሚገኝ ብቸኛ የመንግስት ኮሌጅ ሲሆን የስልጠና ጥራቱን ለማስጠበቅ እና አገልግሎት አሰጣጡን ለማሳለጥ በተከናወኑ ስራዎች በISO-9001/2015 ሰርቲፋይድ መሆኑ እንዲሁም በከተማ አስተዳደሩ በተደረገው ምዘና ከሁሉም ኮሌጆች የላቀ የስራ አፈፃፀም በማግኘት 1ኛ ደረጃ የያዘ ኮሌጅ ሲሆን:-
- በኮሌጁ በ2018 ዓ.ም በዞኒንግ:-
  - 1ኛ. አውቶሞቲቭ ቴክኖሎጂ
  - 2ኛ. ሜታል ኢንጂነሪንግ
  - 3ኛ. ኤሌክትሪካል ኤሌክትሮኒክስ ቴክኖሎጂ
  - 4ኛ. ሌዘር ጋርመንት እና ፋሽን ዲዛይን ቴክኖሎጂ
  - 5ኛ. አግሮ ፕሮሰሲንግ እና ከተማ ግብርና
  - 6ኛ. ሆቴል እና ቱሪዝም

በተጨማሪም

1. ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ(ICT)
2. ኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ
3. ፈርኒቸር ሜኪንግ (ውድወርክ ቴክኖሎጂ)
4. ቢዝነስ
5. ሰርቬይንግ እና ድራፍቲንግ ቴክኖሎጂ የስልጠና ዘርፎች ስልጠና ለመስጠት ዝግጅቱን አጠናቋል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተጠቀሱ ሙያዎች የስራና ክህሎት ሚኒስቴር በሚያወጣው የመቁረጫ ነጥብ መሰረት በኮሌጃችን በመመዝገብ የስልጠና ተጠቃሚ እንድትሆኑ መልዕክቱን ያስተላልፋል፡፡





አቶ ጥራቱ በየነ፤ በምክትል ከንቲባ ማዕረግ
የአዲስ አበባ ስራና ክህሎት ቢሮ ኃላፊ



**ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላምና በጤና አደረሳችሁ፤አደረሰን።**

የዘንድሮው የመስቀል በዓል የደምና የላብ ዋጋ የከፈልንበት፣ የአንድነታችንና የጥንካሪያችን ማሳያና የማንሰራራታችን ማረጋገጫ የሆነው ታላቁ የህዳሴ ግድባችንን አጠናቀን በይፋ ባስመረቅንበት ማግስት የሚከበር መሆኑ በዓሉን የተለየ ያደርገዋል።

ሁላችንም እንደምናውቀው የተጠናቀቀው 2017 ዓ.ም እንደ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አርፎ ከመነሳት ጎጂ ልማድ በመላቀቅ 24/7 የመስራት ባህላችን ይበልጥ ተጠናክሮ የቀጠለበት በዚህም 1ኛው ዙር የኮሪደር ልማት ስራችን መጠናቀቁን ተከትሎ 2ኛውን የኮሪደር ልማት በፍጥነት አስጀምረን በጥራት ያጠናቀቅንበት ስኬታማ ዓመት ነበር።

እኛም የዘንድሮውን የመስቀል በዓል ስናከብር ህልማችንን በትጋት ለማሳካት የምንነሳበት፣ እጅ-ለእጅ ተያይዘን ወደ አዲስ የብልፅግና ምዕራፍ በአብሮነት ለመሻገር ቃል-ኪዳን የምናስርበት በዓል እንደሚሆን እምነቴ ሙሉ ነው።

በዓሉን ስናከብር ልክ እንደ ሁልጊዜው አቅመ-ደካሞችን በመደገፍ አብሮነታችንን ይበልጥ የምናጠናክርበት የሰላም፣ የፍቅርና የጤና እንዲሆን መልካም ምኞቴን እገልፃለሁ፡፡

# መልካም በዓል!

ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል
Gullele Botanic Garden

# እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ!

የከተማችን ብሎም የሀገራችን ነዋሪዎች እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ የሚለው፤ ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ከኢትዮጵያ የተለያዩ አካባቢዎች ሀገር በቀል፣ ብርቅዬ እና ለመጥፋት የተቃረቡ የዕፅዋት ዝርያዎችን በማሰባሰብ፣ በማላመድ፣ በማልማትና በመንከባከብ፣ ለከተማዋ ነዋሪዎች፣ ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገር ጎብኚዎች ተመራጭ መዳረሻ የዕፅዋት ማዕከል ሆኖ ደረጃውን የጠበቀ የኢኮ ቱሪዝም አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፡፡

ይህም የተፈጥሯዊ መስህብነቱና ከብክለት ነፃ መሆኑ ተመራጭ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም፤ የእግር ጉዞ፣ የከፍታ እይታ፣ የዱር አዳር፣ የደሴት ማረፊያ፣ የፊልምና የፎቶ ግራፍ አገልግሎቶችን የሚያገኙበት ሲሆን፣ የልዩ ልዩ ሁነቶች ዝግጅት፣ ተራራ መውጣት፣ የተመስጦ፣ የሰርግ፣ የመኪና ማቆሚያ፣ የካፌና ሬስቶራንት፣ የብስክሌት ማሽከርከር፣ ብርቅዬ ወፎችንና የተለያዩ የዱር እንስሳትን የመመልከት አገልግሎቶችን ተመጣጣኝ በሆነ የመግቢያ ክፍያ ለማህበረሰቡ እየሰጠ ይገኛል፡፡

እርስዎም ተፈጥሮን መሰረት ያደረጉ አገልግሎቶችን ማግኘት ከፈለጉ፤ ወደ ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል ጎራ ይበሉ እያልን የመስቀል በዓል የደስታና የፍቅር እንዲሆንላችሁ እንመኛለን፡፡፡



# መልካም በዓል!
# ጉለሌ የዕፅዋት ማዕከል




# በቂርቆስ ክፍለ ከተማ አስተዳደር

## እንኳን ለብርሐነ- መስቀሉና ለኢሬቻ የአብሮነት በዓሎቻችን በሰላምና በጤና አደረሳችሁ!!

የከተማችን መሐል የሆነችው ቂርቆስ ኃይማኖታዊ፣ ባህላዊና የተለያዩ ሁነቶች የሚከበሩበት ቦታ እንደመሆኑ መጠን ክፍለ ከተማችንን ለየት ያደርገዋል። የዘንድሮውን የመስቀልና የኢሬቻ በዓላትን ስናከብር በተለያዩ ዘርፎች ድርብ ድል የተጎናፀፍንበት በስመ ጥሩ የዐባይ ውኃ ፍትሐዊ በሆነ አግባብ ለመጠቀምና ዘመን ተሻጋሪ ምኞታችንን ዕውን ለማድረግ በሀገራዊ አቅም በመንግስታችንና በህዝባችን የተቀናጀና ያላሰለሰ ከፍተኛ ጥረት እየገነባነው ያለው "የነፃነታችን ዓርማ"! የሆነውን የታለቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድባችንን የተለያዩ ሀገራት መሪዎች በታደሙበት በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትራችን በዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቆ ሀገራችን ኢትዮጵያ በዓባይ ውኃ የመጠቀም ሀገራዊ መብታችንና ሉአላዊነታችን ልክ እንደ አድዋ ድል ሁሉ ከፍ አድርገን ያረጋገጥንበት ከመሆኑም ባሻገር ሌሎች ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት የተበሰሩበት የኢትዮጵያችን የማንሰራራትና ከፍታን በአንፀባራቂ ድል የጀመርንበት በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

መስቀል - ብርሐነ መለኮቱ የተገለጠበት ለዓለም የሰላም ምልክት የሆነበት፣ ከማይዳሰሱ ቅርሶች ውስጥ በዓለም በዩኔስኮ የተመዘገበበትና ለሀገራችንም ለቱሪስት መስህብ የሆነ በዓል ነው፡፡

ከመሆኑም ሌላ መስቀል ከጌታ ስቅለት በኋላ የመዳን ምልክት ሆነ ከዚህ በኋላም በቅናት የተነሳሱ አይሁዶች ቀብረውት የነበረውን መስቀል ንግስት ኢሌኒ ካወጣችው በኋላ የጌታ መስቀል መገኘቱን አስመልክቶ ደመራ አብርተው ደስታቸውን በመግለጥ ለዓለም እንዲታወቅ አደረጉ፤ ይህንን በማስመልከትም ደመራ የማብራትና ብርሐነ - መለኮቱ የተገለጠበትን ዕለት በማስመልከት ከዋዜማው ጀምሮ የኃይማኖት አባቶች በተገኙበት በተለያየ ሁነት ይከበራል። ይህ በእንዲህ እንዳለ የህብረ-ብሔራዊነታችን ምሰሶ እና የአብሮነታችን ዋነኛ ማሳያ የሆነው ኢሬቻ በዓላችን የገዳ ስርዓት መገለጫ ከሆኑት መካከል የምስጋና እና የምልጃ በዓል ሲሆን፤ የተከበረውና የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ባለቤት የሆነው ሰፊው የኦሮሞ ህዝብ ሁሉ ነገር ለፈጠረው አምላክ ሰውን፣ እንስሳትን፣ መሬትና ሰማይን፣ ወንዝን፣ ብርሐንና ጨለማን ዝናብ፣ ዕፅዋት፣ ህይወትንና በአጠቃላይ ሁሉን ለፈጠረና ሁሉንም ማድረግ ለሚችል ዋቃ - አምላክ ምስጋናና ክብር የሚያቀርብበት ስርዓት ከመሆኑም ባሻገር መላ ህዝባችን ላገኘው ፀጋ፣ በረከት፣ ሰላም፣ ደስታ፣ ጤና፣ ዕድሜ፣ ፍቅርና ክብር ለሚያምንበት አንድ ዋቃ - አምላክ ምስጋና የሚያቀርብበት ዕፁብ ድንቅ ዕሴታችን ክብረ- በዓል ነው!!

ኢሬቻ ከዘመን ወደ ዘመን ከአንድ ወቅት ወደሌላ ወቅት በሰላም ያሸጋገረውን ዋቃ - አምላኩን የሚያመሰግንበትና መጭውን ዘመን የሰላም፣ የደስታ፣ የፍቅር፣ የአብሮነት እንዲሆን የሚለምንበት የተራራቀ የሚቀራረብበት ፣ ፈጣሪ የሚመሰገንበት፣ የምርቃት፣ የምስጋና፣ የተማፅኖ፣ የእርቅ፣ የይቅርታ፣ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የወንድማማችነትና እህትማማችነት የበረከትና የቃል - ኪዳን ታላቅ በዓል ነው ።

የተከበራችሁ የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች እነዚህ የመስቀልና የኢሬቻ ክብረ- በዓሎቻችን ሁለቱም የምስጋና፣ የመታደስ እና የመሰባሰብ የብርሃን ምልክቶች እና የማይናወጡ የህብረ- ብሔራዊነታችን ምሰሶዎች ከመሆናቸውም በላይ በእነዚህ ሁለቱ በዓላት ወቅት አዲስ ተስፋ ይሰነቃል የተጣላ ይታረቃል፣ የተራራቀ ይቀራረባል ፣ ፈጣሪያችንም ይመሰገናል።

በአጠቃላይ፡- እነዚህንና ሌሎችንም የአደባባይ በዓላቶቻችንን ስናከብር ከመቸውም ጊዜ በበለጠ ልዩ ትኩረት በመስጠት በዓላቶች ተጀምረው እሲኪጠናቀቁ ድረስ ሁሉም የኃይማኖት አባቶች፣ አባገዳዎች፣ ሐደ ስንቄዎች፣ የሐገር ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች ሁሉም የህብረተሰባችን ክፍል የበኩላችሁን የላቀ አስተዋፅኦ ትወጡ ዘንድ የክፍለ ከተማው አስተዳደር በአክብሮት ለማስገንዘብ ይወዳል፡፡

በድጋሜ እንኳን ለብርሐነ - መስቀሉ እና ለኢሬቻ ክብረ በዓላቶቻችን በሰላም አደረሳችሁ በዓላቱም የሰላም፣ የፍቅር ፣ የጤና፣ የብልፅግና እና የማንሰራራት ዘመን እንዲሆንልን የክፍለ ከተማው አስተዳደራችን ከወዲሁ መልካም ምኞቱን በአክብሮት ይገልፃል!!

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ ምስክር ነጋሽ (ዶ/ር)**

# መልካም በዓል!!

# የቱሪዝሙ ንጋት ነፀብራቅ

- ሠው ሠራሽ ግድቦች በዓለም ቱሪዝም ዘርፍ ዕድገት ላይ የማይተካ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ

**በደረጀ ታደሰ**

ከቀንም ቀን አለው፡፡ አንዳንድ ቀናት ታሪክ የሚዘከረውን ሁነት እና ዕውነት ያስተናግዳሉ፡፡ ከዓመት ዓመትም ከታሪካዊው ሁነት ጋር አብረው ይታወሳሉ፡፡ ጷጉሜን 4 ቀን 2017 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የተበሰረው ታላቅ ብስራት፤ የጷጉሜን 4ኛ ቀን ከቀኖች ልቃ እንድትታወስ አድርጓታል፡፡ ምክንያቱም፤ በዚህች ቀን የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ተጠናቅቆ በይፋ የተመረቀበት ታላቅ ሁነት ዕውን ሆኗል፡፡

በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በሚገኙ ጉባ እና ሰዳል ተራሮች መካከል የተገነባው የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ፤ የመሠረት ድንጋይ ከተጣለበት መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ማጠናቀቂያው ድረስ በነበሩት ዓመታት ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን፤ “የደም፣ የላብ፣ የእንባ ጠብታን” ጨምሮ ያላቸውን ሁሉ ከፍለውበታል። አሁን ላይ ውድ ዋጋ ከከፈሉለት ታላቅ ፕሮጀክት ፍሬ መጠቀም ጀምረዋል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለሀገሪቱ የኤሌክትሪክ ብርሃን ከመስጠት የተሻገረ ጥቅምን እንደሚያስገኝ በጥናትም በተጨባጭ ውጤትም የተረጋገጠ ሀቅ ነው፡፡ ለአብነት ከግድቡ የሚመነጨው የኤሌክትሪክ ኃይል በቀጠናው ላሉ ሀገራት ጭምር እንደሚሰራጭ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በምረቃው ዕለት ባደረጉት ንግግር መግለፃቸው ይታወሳል፡፡ የግድቡ መጠናቀቅ ለቱሪዝም ዘርፉ ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥርም ተናግረዋል፡፡ በተለይ በአፍሪካ አህጉር ደረጃ በግዝፈቱ ቀዳሚ የሆነውን ግድብ ጀምሮ ፍፃሜ በማድረሱ ሂደት ውስጥ ዋነኛ ተሳታፊ ለሆኑት ኢትዮጵያውያን፤ “ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጉባ ተገኝቶ ይህን ታሪክ እና ገድል ማየት ይገባዋል፡፡ ይህን የትውልድ ገድል ሁሉም መመልከት አለበት” በማለት ግድቡን እንዲጎበኙ አበረታተዋል፡፡

ከጉባ ተራራ ራስ ላይ የተበሰረው የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ፍፃሜ፤ ከኢትዮጵያ አልፎ የዓለም መነጋገሪያ ለመሆን ጊዜም አልፈጀበት፡፡ ቅስቀሳም አልፈለገም፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚታወቁትንና ሰፊ ተደራሽነት ያላቸውን የመገናኛ ብዙሃን ተቋማትን ጨምሮ የዕለቱ ቁልፍ አጀንዳቸው አድርገውት ውለው፤ አድረዋል፡፡ የዲጂታል ሚዲያውም በተመሳሳይ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ (Great Ethiopian Renaissance Dam- GERD) የሚለው ስያሜና እሱን የተመለከቱ መረጃዎች ተቆጣጥረውት ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ፤ የሚታወቀውን የኢትዮጵያውያን ግዙፍ ፕሮጀክት የበለጠ እንዲታወቅ ዕድል ፈጥሮለታል። መታወቁ ደግሞ፤ “ሁሉም ኢትዮጵያዊ በጉባ ተገኝቶ ይህን ታሪክ እና ገድል ማየት ይገባዋል”

> ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ከአፍሪካ ትልቁ ፕሮጀክት ነው። የዚህ ፕሮጀክት ትልቅነት፣ ያለበት መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ፣ የግንባታው የምህንድስና ጥበብ፣ የፈጠረው አዲስ ገፅታ እና ሌሎች ጉዳዮች ግድቡ ለቱሪዝም መስህብነት የላቀ አቅም እንዲኖረው ያደርጋል

በሚል ለኢትዮጵያዊያን በመሪያቸው አማካኝነት የተላለፈውን ጥሪ አድማስ በማስፋት ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የሚዳረስ የሕዳሴ ግድብን የመጎብኘት ስሜትና ፍላጎትን እንደሚያነቃ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ በቅርበት የሚሠሩ ምሁራንና ባለሙያዎች ይስማማሉ፡፡

በጅማ ዩኒቨርስቲ የቱሪዝም እና የሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ኃላፊ እና መምህር ደመቀ ክብሩ፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መጠናቀቅ፤ የአንድ ግዙፍ ፕሮጀክት መፈፀም ብቻ ተደርጎ የሚወሰድ አለመሆኑን ያነሳሉ። አያይዘውም፤ የግድቡ መጠናቀቅ ለእሳቸው ያለውን ትርጉም ሲገልፁ፤



ፎቶ- ከገፀ ድር

ለኢትዮጵያ የቱሪዝም ዕድገት ከፍተኛ አቅም እንደሚፈጥር የሚጠበቀው ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ

“ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ከጨለማ የምንወጣበት ብርሃን የምናይበት ነው። ሕዝቦችን ያስተሳሰረ የአንድነታችን ምልክትም ነው፡፡ አንድ ስንሆን ምን መሥራት እንደምንችል ለዓለም ያሳየ ነው፡፡ የትውልዱ ሕልም የተፈፀመበት ፕሮጀክትም ነው፡፡ ይህ ትውልድ ለቀጣዩ ትውልድ የሚያወርሰው ስጦታ ነው፡፡ ቀጣዩ ትውልድ ለበለጠ ሥራ የሚነሳሳበት ነው” በማለት ነው፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ለሀገር ከሚሰጣቸው ዘርፈ ብዙ አገልግሎት መካከል አንዱ በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ የሚያመጣው ትሩፋት እንደሆነ ትምህርት ክፍል ኃላፊ እና መምህር ደመቀ ክብሩ ጠቁመዋል፡፡ የሚከተለውን ማብራሪያም ሰጥተዋል፤ “ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ከአፍሪካ ትልቁ ፕሮጀክት ነው፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ትልቅነት፣ ያለበት መልክዓ ምድራዊ ሁኔታ፣ የግንባታው የምህንድስና ጥበብ፣ የፈጠረው አዲስ ገፅታ እና ሌሎች ጉዳዮች ግድቡ ለቱሪዝም መስህብነት የላቀ አቅም እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ በዚህ ግድብ ማዕከላዊ ውሃማ አካላት ላይ የሚፈጠሩ የተለያዩ ሠው ሠራሽ ደሴቶች አሉ፡፡ እነዚህ ደሴቶችም ጎብኚዎችን በመሳብ አስተዋጿቸው ከፍ ያለ ነው፡፡”

መምህሩ አያይዘው ፤ “ሠው ሠራሽ ግድቦች በዓለም ቱሪዝም ዘርፍ ዕድገት ላይ የማይተካ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ። የአካባቢ ጥበቃ ውጤታማነትን ያሳድጋሉ፡፡ የውሃማ አካላት ሥነ ሕይወትን ይጠብቃሉ፡፡ እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ዓይነት ፕሮጀክቶች ሲከናወኑ ከአካባቢና ከማህበረሰብ ጋር ያላቸው መስተጋብር ጤናማ እንዲሆን በጥናት ላይ የተመሰረተ ሥራ ይሠራል፡፡ ይህም በግድቦች አካባቢ ያለው ተፈጥሯዊ ሃብት እና ማህበረሰባዊ እሴት እንዲጠበቅ ያግዛል። የአካባቢው ማህበረሰብም ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነቱን ያሳድጋል፡፡ ይህ ደግሞ ለቱሪዝም ዕድገት እና ከቱሪዝም ጋር ተያይዞ የሚመጡ የትራንስፖርት፣ የሆቴል፣ የአስጎብኚ እና መሰል አገልግሎቶችን ያስፋፋል፤ ያጎለብታል። ለብዙዎች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፡፡ ሌሎች የቱሪዝም መዳረሻዎችን ያነቃቃል” በማለት በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ምሁራዊ ትንታኔ ሰጥተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ በሠው ሠራሽ ግድብ የቱሪስት መዳረሻ ማዕከልነት በቀዳሚነት ሊያስቀምጠው የሚችል አቅምን ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መያዙን ያነሱት የታላቅ ኢትዮጵያ ቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ማሕበር ቦርድ አባል አቶ ናሆም አድማሱ ናቸው፡፡ እንደ እሳቸው ገለፃ፤ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ መጠናቀቅ የቱሪዝሙ ዘርፍ ላይ የሚያመጣው ውጤት ከፍተኛ ነው፡፡ በግድቡ ላይ የተፈጠረው ሠው ሠራሽ ሀይቅ (ንጋት ሀይቅ) በጣም ሰፊ የሚባል ነው፡፡ ይህም በኢትዮጵያ የውሃ ላይ ቱሪዝምን በስፋት ለመተግበር ዕድልን ይፈጥራል፡፡ በውሃ ላይ የጀልባ መንሳፈፍ እና ጉብኝትን በስፋት ማካሄድ ያስችላል፡፡ በሀይቁ ውሃ ላይ እየተዘዋወሩ ደሴቶች የሚጎበኙበትን መልካም አጋጣሚም ይፈጥራል፡፡ የስፖርት ቱሪዝም ማከናወኛም ይሆናል። በግድቡ ሥራ ላይ የተተገበረውን የምህንድስና ዕውቀት፣ ጥበብና ክህሎት እንደ አንድ የጉብኝት ፓኬጅ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥናትና ምርምር ማድረግ የሚፈልጉ ተማሪዎች፣ ተመራማሪዎች ወደሥፍራው የሚመጡበት አጋጣሚ ይጨምራል፡፡ የሀገር ገፅታን ያስተዋውቃል፤ ይገነባል፡፡ የውጭ ምንዛሬ ያስገኛል፡፡

የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ መጠናቀቅ እና ለአገልግሎት መብቃት ብቻውን ተጠባቂውን የቱሪዝም ዘርፍ ዕድገትና ጥቅም እንደማያመጣ ያነጋገርናቸው አስተያየት ሰጪዎች ተመሳሳይ ጭብጥ ባለው ሃሳባቸው አረጋግጠዋል፡፡ ግድቡ ይዞት ከመጣው የቱሪዝም ዕድል በአግባቡ ለመጠቀም እንደሀገር መሠራት የሚገባቸው ወሳኝ ተግባራት ስለመኖራቸው አንስተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ አቶ ናሆም አድማሱ፤ “ይህንን ትልቅ የቱሪዝም ሀብት ወደገበያ ይዘን ከመቅረባችን በፊት በሁሉም መስክ በቅድሚያ መሠራት ያለባቸውን ተግባራት ጥንቅቅ አድርጎ መሥራት ይገባል፡፡ ቢያንስ ቢያንስ ለጉብኝት መሠረታዊ የሚባሉ ነገሮች መሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ ደረጃውን የጠበቀ መሠረተ ልማት ማሟላት ያስፈልጋል። ለጎብኚዎች አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማትን (ሆቴሎችን፣ ባንኮችን፣ የትራንስፖርት አገልግሎትን...) በበቂ ሁኔታ ማቅረብ ይገባል፡፡ ለዚህ ደግሞ ከመንግስት በተጨማሪ፤ ባለሀብቱ መዳረሻውን በማልማት፣ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን በመገንባትና ወደሥራ በማስገባት፣ በማስተዋወቅ ... የራሱን ኃላፊነት መወጣት አለበት”

ሌላኛው የዓድዋ ድል ተደርጎ የሚቆጠረውን፣ የዚህ ትውልድ መጠቀሚያ እና መዘከሪያ ሐውልት ከሆነው የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ እንደ ሀገር የሚያስገኘውን የቱሪዝም ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ከወዲሁ ሊሠሩ ስለሚገባቸው ተግባራት በጅማ ዩኒቨርሲቲ የቱሪዝም እና የሆቴል ማኔጅመንት ትምህርት ክፍል ኃላፊ እና መምህር ደመቀ ክብሩ አንድ ሁለት በማለት ቆጥረው አስቀምጠዋል፡፡ እንደሳቸው ምሁራዊ ዕይታ መሰረት፤ የግድቡን የቱሪዝም አቅም ለመጠቀም እንደ ሀገር አምስት ቁልፍ ሥራዎች መሠራት አለባቸው፡፡ የመጀመሪያ ሥራ መሆን ያለበት፤ ቱሪዝምን የመስከ ዕቅድ አና ዘመቻ ላይ መሥራት ነው። ይህም ማለት፡- የግድቡ ሐይቅ (ንጋት ሐይቅ) የታችኛው ክፍል ያሉ የቱሪዝም ሥፍራዎችን ማስተካከል፣ በመሰረተ ልማት እና በአገልግሎት ማሟላት ይገባል።

ወደ ገጽ 43 ዞሯል

# ከህዳሴ ግድቡ የሚቀዳ ትምህርት

- ግድቡ ሃይል ብቻ ሳይሆን ማሳካት መቻልንም ጭምር ማመንጨት የቻለ እንደሆነ ተጠቁሟል



ፎቶ ከገፀ ድር

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ኃይል ከማመንጨት ባሻገር የጎብኝዎችን ቀልብ እየሳበ ነው



ፎቶ በገነት ወንድሙ

በህዳሴው ግድብ ዙሪያ አስተያየት የሰጡት ወይዘሮ ላቀች ሃይሌ እና አቶ ደሳለኝ ካሴ

በፋንታነሽ ተፈራ

“ይህ ግድብ እንዲገነባ ማንም አልፈለገም ነበር፡፡ ማንም የፋይናንስ ድጋፍ ለማድረግ ፈቃደኛ አልነበረም። በርካታ የፖለቲካና ሌሎች ችግሮችም ነበሩ፤ ቀላል መፍትሔዎች አልነበሩም። ኢትዮጵያውያን ፈተናዎችን የሚፈሩ አይደሉም፡፡ ፅኑ ናቸው፡፡ ተገዳዳሪ ወይም ጠላት ሲያጋጥማቸው አቅማቸውን በእጥፍ በማሳደግ ማሸነፍ ይችሉበታል... ኢትዮጵያ ይህንን ግድብ የገነባችው ሁሉንም ፈተናዎች በማሸነፍ ነው፡፡”

ይህንን የተናገሩት ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ በተመረቀበት ወቅት መልእክት ያስተላለፉት የዊቢዩልድ ግሩም (ሳሊኒ ኮንስትራክሽን) ዋና ስራ አስፈፃሚ ፔይትሮ ሳሊኒ ናቸው፡፡ አዎ! እሳቸው እንደገለፁት ግድቡ በግንባታው ሂደት በፋይናንስ፣ በዲፕሎማሲ፣ በፀጥታና ደህንነትና በሌሎችም ጉዳዮች እልህ አስጨራሽ ፈተናዎችን አልፎ ነው እውን የሆነው፡፡ በርካታ ፈተናዎችን አልፎ ከዳር መድረሱ እንደ ግለሰብ፣ ማህበረሰብና እንደ ሀገር የሚያስተምረው ቁም ነገር ብዙ ነው፡፡

ዋና ሳጂን ገነት መልኬ የአዲስ አበባ ነዋሪ ናቸው፡፡ “ግድቡ የሁላችንንም ስሜት አንድ ያደረገ እና የኮረኮረ ነው። የተለያዩ የውስጥና የውጭ ፈተናዎችን አልፎ ለመመረቅ የበቃ የአንድነታችን ድልድይ ነው፡፡ ከህፃን እስከ አዋቂ በነቂስ የተሳተፉበት የላብ ጠብታ ጭምር ነው” ሲሉ ለፍፃሜ መብቃቱ እንዳስደሰታቸው ነግረውናል፡፡

የህዳሴው ግድብ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ መጠናቀቅ መቻሉ የኢትዮጵያውያንን የይቻላል መንፈስን እና ቁርጠኝነትን ያሳያል ያሉት ዋና ሳጂን ገነት፤ የሰው ልጅም በህይወት ሲኖር በዚህ ዓለም ላይ እስካለ ድረስ ፈተናዎች እንደሚገጥመውና ማለፍም እንደሚችል ግድቡ ማሳያ መሆኑን ያነሳሉ፡፡

“እኔ እቅዶቼ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳኩ ሲቀሩ ተስፋ ቆርጬ አውቃለሁ። ነገር ግን ግድቡ ያለፈበትን ሂደት ስመለከት በቶሎ መሰበሬ ይቆጨኛል። ከዚህ በኋላ በህይወቴ ላሳካው የምፈልገውን ህልም እንዴት ማለፍ እንዳለብኝ ጥንካሬና ብርታት ሆኖኛል። ችግሮች እንደሚያልፉ፤ ተስፋ ማድረግ እንደሚያሻግር ግድቡ ህያው ምሳሌዩ ነው” ይላሉ ዋና ሳጅን ገነት፡፡

ፈተናዎች እንደሚያጠነክሩ፣ የወደቀ እንደሚነሳ፣ አይደርስም የተባለ እንደሚደርስ እንዲሁም የማልችለውና የማላልፈው ምንም ነገር እንደሌለ ከግድቡ ትምህርት አግኝቻለሁ፡፡ በቤተሰብ ውስጥ እናት፣ አባት እና ልጆች በአንድ ጎጆ ሲኖሩ መተባበር እና በአንድ መስራት እንዲሁም መረዳዳት ወሳኝ መሆኑን እንዲሁ ሲሉ አክለዋል፡፡

ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የሀገራችንን ስም በበጎ ያስጠራ በመሆኑ ደስተኛ ነኝ ሲሉ የገለፁልን ደግሞ ሌላኛዋ የከተማዋ ነዋሪ ወይዘሮ ላቀች ሃይሌ ናቸው። “የህዳሴ ግድብ አይችሉም የተባልነውን ወደ መቻል የቀየርንበት፣ ዓድዋን መልሰን የደገምንበት፣ የአፍሪካ ተምሳሌት የሆንበት እንዲሁም ዓለምን ያስደመምንበት፤ ‘ዓባይ ማደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል’ የሚለውን ብሂል የሻርንበት ነው” ብለዋል።

ግድቡ ለመመረቅ ብዙ ችግሮችን እንዳለፈ ሁሉ፤ እኛም በህይወታችን ብዙ ዓይነት ችግሮች በዕለት ተዕለት ህይወታችን ይገጥሙናል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ችግሮችን አግዝፈን በማየት ተስፋ እንቆርጣለን፡፡ የህዳሴ ግድብ በህይወታችን ‘አይቻልም’ ብለን ያቆምናቸው ነገሮች እንዲቆጩን እና ለችግሮች እጅ መስጠት እንደሌለብን ያስተምረናል፡፡ ግድቡ ከመገንባቱ አስቀድሞና በግንባታው ሂደት ያጋጠሙ ፈተናዎችን አልፎ መመረቁ በቁርጠኝነትና በጋራ ከተሰራ ምንም የማይቻል ነገር እንደሌለ ማሳያ እንደሆነ ወይዘሮ ላቀች ይናገራሉ፡፡

“እኔ ከዓባይ የተማርኩት በፅናት፣ በአንድነት፣ በትግል ራሴን ማበርታት፣ ቀን ከሌት በመስራት ራሴን መለወጥ እንዳለብኝ ነው። ግድቡ እንደተጠናቀቀው ሁሉ በህይወታችን የምንጀምራቸው ነገሮችም መጨረሻ እንዳላቸውና ተስፋ መቁረጥ እንደሌለብኝ የተረዳሁበት ነው” ሲሉ ለወደፊት የይቻላልን መንፈስ ይዘው የህይወት ውጣ ውረዶችን ማለፍ እንደሚችሉ ተናግረዋል፡፡

አቶ ደሳለኝ ካሴ በበኩላቸው፣ በዓባይ ውሃ ላይ ልማት ማካሄድ ለዘመናት የማይቻል ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ ለሀገሩ ባዕዳና እንግዳ፤ ለሌሎች ሀገራት ብቻ ሲሳይ ነበር፡፡ ወንዙ ላይ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን መገንባት መቻሉ እንደ ግለሰብ ተስፋ አለመቁረጥን፣ ‘ይሳካል’ የሚል መንፈሰ ጠንካራነትን፣ ከተናጠል ይልቅ በጋራ መስራትን፣ የአንድነትን ሃይል እንዲሁም የአላማ ፅናትን እንደተማሩበት ነግረውናል፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ የተጀመረበት ብሎም ለፍጻሜ የደረሰበት መንገድ በግለሰብ ደረጃ ብዙ የሚያስተምር ነው፡፡ የዝግጅት ክፍላችን ያነጋገራቸው የስነ ልቦና ባለሙያም

ወደ ገጽ 37 ዞሯል

# ምን ልርዳዎ?

## ጤናማ የበዓላት ሰሞን አመጋገብ

በበዓላት ወቅት የምንከተለው ያልተገባ አመጋገብ ጤና የሚነሳ ወይም ላልተጠበቀ አደጋና እስከ ሕይወት ማለፍ ሊዳርግ እንደሚችል ይገለጻል። በተለይም ከመጠን በላይ መመገብ፣ ስጋና የእንስሳት ተዋጽኦን ማዘውተር እንዲሁም የአልኮል መጠጦችን አብዝቶ መጠጣት የጤና እክል ያስከትላል።

ታድያ ይህን ለማስቀረት በበዓላት ወቅት የሚከተሉት ጥንቃቄዎች እንዲደረጉ የጤና ባለሙያዎች ይመክራሉ፡-



የተለያዩ ምግቦችንና መጠጦችን በአንድ ላይ ቀላቅሎ አለመመገብ፤

ምግቦቻችን ንጽህናቸውን በጠበቀ መልኩ ማዘጋጀት፤

ምግቦቻችን ቅባት የበዛባቸው እንዳይሆኑ መጠንቀቅ፤

ስንመገብ ቀስ በቀስ ጨጓራን በማላመድ፣ በልክ እና ከመጠን ባላለፈ መልኩ መመገብ፤

ጣፋጭ ምግቦችን እና የአልኮል መጠጦችን ከልክ በላይ አለመውሰድ፤

ቅባት የበዛባቸውን ምግቦች አለመመገብ

ታዲያ በዓልን በሰላም ለማክበር ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገቡ ጉዳዮች የበዓላት ሰሞን አመጋገብ አንዱና ዋነኛው ስለሆነ፣ ጤናማ የበዓል አመጋገብን በመከተል ጤናን መጠበቅ ያስፈልጋል። በጤና የታጀበ በዓል ይሁንልዎ።

**መልካም በዓል!**

ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ ጋር በመተባበር ዘወትር ቅዳሜ የሚቀርብ

# የፌዴራል ገቢ ግብር አዳዲስ ይዘቶችና ማሻሻያዎች

## ክፍል አንድ

በደርብ ምሳየ (ዐቃቤ ሕግ)

### መግቢያ

### የገቢ ግብር ምንነትና ዓላማ

ገቢ እንዴት መሰብሰብ እንዳለበት ሕግ አውጭው አካል ሚዛኑን የጠበቀ የገቢ ማሰባሰቢያ ሕግ ያወጣል። በአንድ ሀገር ውስጥ የተገኘውን ዓመታዊ ምርትና አገልግሎት መሰረት ያደረገ ግብር መሰብሰብ ካልተቻለ የሀገርን ኢኮኖሚ እድገት ወደኋላ የሚያስቀር ወይም ዜጎች ላይ የኑሮ ጫና በማሳደር የሰብዓዊ መብት ጥሰት ሊፈጥር የሚችል ይሆናል።

መንግስት በተለያዩ ሕጎች ውስጥ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር ለማከናወን ገቢ እንደሚያስፈልገውና የተገኘውን ገቢ መልሶ ወጭ በማድረግ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥበት ይሆናል።

### ገቢ ከሚገኝባቸው መንገዶች ውስጥ የሚከተሉትን ያካትታል፡-

- ግብር (ቀጥተኛ እና ኢ-ቀጥተኛ)
- ከወንጀል ገንዘብ ቅጣት (የብር መቀጮ፣ ንብረትን መውረስ)
- መንግስት ከሚሰጣቸው አገልግሎት ላይ የሚሰበሰቡ የአገልግሎት ክፍያ (የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ፣ የመብራትና የውኃ ክፍያ)
- ከሀገር ውስጥና ውጭ ብድር
- ከሀገር ውስጥና ውጭ ከሚያገኘው እርዳታ የመሳሰሉት መንግስት ገቢ የሚያገኝባቸው መንገዶች ናቸው።

ሆኖም ግን ከላይ ከተጠቀሱት መንገዶች ውስጥ አንዳንዶቹ በተዘዋዋሪ ለመንግስት ገቢ ያስገኙ እንጂ ዋና ዓላማቸው ገቢ መሰብሰብ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ ወንጀል የፈፀመን አካል የብር መቀጮ የሚቀጣው ገቢ ለማስገኘት ሳይሆን ወንጀለኛውን ሊያርመው የሚችል ሲሆን ብቻ ነው።

ከላይ እንደተገለፀው ግብር አንዱ የገቢ ምንጭ ሲሆን፤ ግብሩን ማን ይከፍለዋል በሚለው መሰረት ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ግብር በመባል በሁለት የሚመደብ ነው። ዛሬ ትኩረት የምንሰጥበት ርዕስ ‘ቀጥተኛ የገቢ ግብር’ ላይ ነው። በዚህ ርዕስ አዲስ የወጣው የፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 ያመጣቸው አዳዲስ ይዘቶችና ማሻሻያዎች ላይ ይሆናል።

### የፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 ያመጣቸው አዳዲስ ይዘቶች



የፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ለተከታታይ ዘጠኝ ዓመታት ተፈፃሚ ሲደረግ የቆየ ሲሆን፣ ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ የገቢ ግብር አሰባሰብ ስርዓቱ ላይ ብዙ አዳዲስ ይዘቶች በመምጣታቸው ምክንያት እነዚህን አዳዲስ ይዘቶች እና ማሻሻያዎች የሚያካትት የፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 እንዲወጣ ተደርጓል።

በፌዴራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 በመሰረታዊነት ያካተታቸው ይዘቶች ወይም አዋጁን ለማውጣት ያስፈለገበት ዓላማዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

#### 1. የታክስ ማስከፈያ እና ቅንፍ መጣኔ ከወቅታዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ማድረግ

የብር የመግዛት አቅሙ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ በመምጣቱ ምክንያት አዋጅ ቁጥር 979/2008 እንዲሻሻል ከመቀጠር፣ ከግለሰቦች ቤት ኪራይና ንግድ ስራዎች የሚገኘው ገቢ ላይ የሚጣልበት ቅንፍ እና መጣኔ መስተካከል ስለነበረበት እንዲስተካከል ማድረግ ነው። የታክስ መጣኔዎች በተሻረው አዋጅ ሰባት (7) የነበረ ሲሆን፣ በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 1395/2017 ወደ ስድስት መጣኔዎች የተቀነሰ ሲሆን 10%(አሥር ከመቶ) ከሁሉም ሰንጠረዦች እንዲወጣ ተደርጓል።

ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በአዋጅ ቁጥር 979/2008 ከብር 0-600 ወርኃዊ ገቢ ከሆነ በዜሮ መጣኔ ተሰልቶ ከግብር ነፃ ሲደረግ የቆየ ሲሆን አሁን ካለው ኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር የማይሄድ በመሆኑ ምክንያት፣ በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 1395/2017 ከብር 0-2000 ብር ከፍ በማድረግ ማሻሻያ ተደርጎበታል። ይሁን እንጂ በረቂቅ አዋጁ ላይ የሚመለከታቸውን አካላትና የሕዝብ አስተያየት ለማካተት የተለያዩ የመድረክ ውይይቶች በተደረጉበት ወቅት ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በዜሮ መጣኔ ውስጥ መግባት ያለበት ቅንፍ ላይ ከፍተኛ እንዲሆን የተጠየቀ ቢሆንም የመንግስት ገቢ የሚያሳጣ በመሆኑና ከሌሎች ገቢዎች ላይ ማካካስ የማይቻል በመሆኑ የተጠየቀውን አስተያየት ማካተት አልተቻለም።

#### 2. የታክስ መሰረቱን ማስፋት

በሀገሪቱ የተከናወነውን ዓመታዊ ጠቅላላ ምርትና አገልግሎት እድገትን ያገናዘበ ግብር መሰብሰብ ካልተቻለ የሀገርን እድገት ወደኋላ ሊያስቀር የሚችል ወይም የኑሮ ውድነት በመፍጠር የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶች ላይ ጥሰት ሊፈጥር የሚችል ነው። እንዲህ ዓይነት ችግር እንዳይፈጠር ሚዛኑን የጠበቀ የታክስ መሰረት ያለው የገቢ ግብር አዋጅ እንዲኖር ማስቻል ነው።

ከቅጥር፣ ከግለሰቦች ቤት ኪራይና ንግድ ስራዎች የገቢ ቅንፍና ምጣኔ በማስተካከል፣ ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ የሚገኝ ገቢ ላይ ተገቢውን ግብር በመጣል፣ በሰንጠረዥ ‘መ” ውስጥ በሚሸፈኑ ገቢዎች ላይ የግብር መጣኔውን በማሳደግ የግብር መሰረቱን ማስፋት ተችሏል።

ከዲጂታል ይዘት ፈጠራ ተገቢውን ግብር ለማስከፈል የነበረው አዋጅ ቁጥር 979/2008 በበቂ ሁኔታ ስርዓት ስላልተዘረጋለት በአዲሱ አዋጅ ቁጥር 1395/2017 ተገቢውን ግብር እንዲከፈል የሚያደርጉ ድንጋጌዎችን አካትቷል። በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ የዲጂታል አገልግሎት በመስጠት የሚገኘው ገቢ በኢትዮጵያ የተገኘ ገቢ እንደሆነ ይቆጠራል። ከዚህ የፈጠራ ስራ የሚገኝ ገቢ በንግድ ስራ ወይም ሌሎች ገቢዎች (15%) ግብር የሚጣልበት ነው።

በኢትዮጵያ የዲጅታል አገልግሎትን በማቅረብ ገቢ የሚያገኝ ነዋሪ ወይም ነዋሪ ያልሆነ ማንኛውም ሰው የሚያገኘው ገቢ ላይ ከ5% የማይበልጥ ግብር ሲሆን የማስከፈያው መጣኔ፤ የአከፋፈሉ ሁኔታ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ የሚወስን ነው።

#### 3. ታክስ ላለመክፈል በር የሚከፍቱ ሁኔታዎችን መከላከል

በፌደራል ገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 1395/2017 ግብርን ላለመክፈል በር ከፋች ሁኔታዎች የሚከላከሉ ድንጋጌዎች ተካትቷል። ይኸውም

- **በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ ግብይትን መገደብ**

ተገቢውን ግብር ለማስከፈል በግብር ዓመቱ ውስጥ ግብር ከፋዩ ያከናወናቸውን ግብይት መረጃ ማወቅ የሚያስፈልግ ሲሆን፣ በጥሬ ገንዘብ የሚደረግ ግብይት ግን ይህን ትክክለኛ መረጃ እንዳይገኝ የሚያደርግ ነው። በዚህ መንገድ የሚደረግ የመረጃ መደበቅ ተግባር ለመከላከል በአዲሱ አዋጅ ግብር ከፋዮች ከ30,000 ብር በላይ የሚያደረጉትን ግብይቶች በጥሬ ገንዘብ መቀበል እንደማይችሉ ይደነግጋል። ከተመለከተው መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ክፍያ የተቀበለ ግብር ከፋይ በብልጫ የተቀበለውን ገንዘብ እጥፍ አስተዳደራዊ ቅጣት እንዲከፍል ይደረጋል። ለምሳሌ ግብር ከፋዩ 50,000 ብር ባደረገው ግብይት ላይ ሙሉ በጥሬ ገንዘብ ከተቀበለ 50,000ብር - 30,000ብር = 20,000ብር ሲሆን፣ አስተዳደራዊ ቅጣት 40,000 ብር እንዲከፍል ይደረጋል።

ውድ አንባቢዎቻችን ክፍል ሁለትን በሚቀጥለው ሳምንት ይዘን እንቀርባለን።



አቶ ፍፁም ኃይሌ
የየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈፃሚ




### ለመላው ኢትዮጵያዊያን፣ ለከተማችንና ለየካ ክፍለ ከተማ የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን!

በዓሉ የሰላም፣ የፍቅርና የብልፅግና እንዲሆንላችሁ በራሴና በየካ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ስም ልባዊ ምኞቴን እየገለፅኩ አስተዳደሩ በባለፈው በ2017 በጀት ዓመት በመንግስት ካፒታል በጀትና በህብረተሰብ ተሳትፎ በርካታ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሰው ተኮር ፕሮጀክቶችን በአጭር ጊዜና በጥራት ሰርቶ በማጠናቀቅ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ አድርጓል።

በተለይም በመልካም አስተዳደር፣ በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በሰላምና ፀጥታ፣ በኮሪደርና ወንዝ ዳርቻ ልማት ስራዎች ከተማዋን ውብና ፅዱ እንዲሁም ለነዋሪዎቿ ምቹ ከማድረግ አንፃር አመርቂ ውጤቶችን አስመዝግቧል። በተያዘው በጀት ዓመትም እነዚህን ስራዎች አጠናክረን እንደምናስቀጥል ለክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች ቃል እየገባን አቅደን በምናከናውናቸው የልማት ስራዎች ላይ እንደከዚህ በፊቱ ከጎናችን ሆናችሁ የካን የብልፅግና ከፍታ ማሳያ እንድናደርጋት ጥሪዬን አስተላልፋለሁ፡፡

በድጋሚ እንኳን ብርሃነ መስቀሉ የሰላም፣ የጤና፣ የፍቅር፣ የአንድነትና የብልፅግና እንዲሆንላችሁ በራሴና በክፍለ ከተማ አስተዳደሩ ስም መልካም ምኞቴን እገልፃለሁ፡፡

የአዲስ አበባ አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን
ADDIS ABABA ENVIRONMENTAL PROTECTION AUTHORITY

### እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የከተማ አስተዳደሩን ፖሊሲና ስትራቴጂዎች እንዲያስፈጽሙ ከተቋቋሙት መስሪያ ቤቶች አንዱ እንደመሆኑ በከተማችን የተጀመረውን የመልካም አስተዳደር ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግና የህዝብን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የበኩሉን አስተዋፆኦ እያደረገ ከመሆኑም በላይ የከተማዋን የአካባቢ ብክለትና የተፈጥሮ ሀብት እንዲሁም የአየር ብክለት ሁኔታ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማምጣትና አካባቢው በዘላቂነት እንዲጠበቅ ለማድረግ በርካታ ተግባራትን አቅዶ በላቀ ቁርጠኝነት እየሰራ ይገኛል፡፡

በተሰጠው ኃላፊነት እና ተግባር መሰረት የተቋቋመበትን አላማ ለማሳካት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴ የከተማውን ተፈጥሮ ሀብት ማሻሻልና አካባቢን ከብክለት በመከላከል አዲስ አበባን ለኑሮና ለጤና ተስማሚ ለማድረግ በከተማው መሪ ፕላን ለአረንጓዴ ቦታ ልማት በተከለሉ የደንና የወንዝ ዳር ቦታዎች ላይ ደን እንዲለማና የአፈርና ውኃ ጥበቃ ስራዎች እንዲከናወኑ እየሰራ ይገኛል፡፡

ባለስልጣን መስሪያ ቤታችን የከተማችን አዲስ አበባ ድምቀት የሆነዉን የመስቀል ደመራ በዓል አከባበር በተባበሩት መንግስታት የትምህርት ሳይንስና ባህል ድርጅት (UNESCO) በማይዳሰስ ቅርስነት የተመዘገበ የኢትዮጵያውያንና የዓለም ሀብት በመሆኑ በዓሉን ስናከብር ከመላዉ ዓለም የሚታደሙ እንግዶችን በማክበር፣ በመውደድ እና የመስቀልን እውነተኛ ምሳሌነት በማሳየት እርስ በርስ በመተሳሰብ በዓሉን በጋራ እንድናከብር እና በዓሉ የፍቅር፣ የአብሮነትና የመከባበር ይሁንላችሁ በማለት መልካም ምኞቱን ይገልፃል፡፡



**መልካም በዓል!**

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን**


እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ አደረሳችሁ!
የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ቦሌ ክ/ከተማ አስተዳደር
Bole Sub City
እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም በጤና አደረሳችሁ የሚለው የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር እንደ ሀገር በሁሉም መስኮች ተጨባጭና የሚቆጠሩ ስኬቶችን በማስመዝገብ የኢትዮጵያን ብልጽግና ዕውን የማድረግ ጉዟችንን በአስተማማኝ ጎዳና ላይ እያፋጠንን ባለንበት ወቅት ላይ ሆነን ነው፡፡ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ በመላው ሕዝባችን ያልተቋረጠ ድጋፍ እና በጠንካራ አመራር የነበሩበትን ችግሮች አልፎ ለምረቃ መብቃቱ ሀገራችን በራስ አቅም መልማትና ማደግ እንደምትችል ያሳየችበት ታሪካዊ ድላችን ነው፡፡ ከተማችን አዲስ አበባ ዕለት ተዕለት እያበበችና ግዙፍ ፕሮጀክቶችን በፍጥነትና በጥራት እያጠናቀቀች ለአገልግሎት ማብቃት እንደምትችል በተግባር ያሳየችበትና በልዩ ልዩ መስኮች ባከናወነቻቸው ሥራዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅናና ሽልማት በማግኘት አርአያ ለመሆን የበቃችበት ነው፡፡
የቦሌ ክፍለ ከተማም በእነዚህ እና ሌሎችም ተግባራት በንቃት እየተሳተፈና ውጤታማነቱንም እያሳደገ ይገኛል፡፡ ክፍለ ከተማችን በአጠቃላይ ተግባራት አፈጻጸም ከአሥራ አንዱም ክፍለ ከተሞች ቀዳሚ በመሆን ለሦስት ተከታታይ ዓመታት ተሸላሚ ለመሆን የበቃ ሲሆን፣ ይህ ስኬትና ድል በመላው የክፍለ ከተማችን ኅብረተሰብ ተሳትፎ የተገኘ መሆኑ ከተባበርን የማናሳካው ምንም ነገር እንደሌለ ያረጋገጠ ሆኗል፡፡ ለዚህም ስኬት የበኩላችሁን የተወጣችሁ ሁሉ በቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ስም ልባዊ ምስጋናዬን እያቀረብኩ፣ በአዲሱ ዓመትም እጅ ለእጅ ተያይዘን የተለመደ ስኬታችንን እና የሀገራችንን ብልጽግና የማረጋገጥ ጥረታችንን አጠናክረን እንድንቀጥል ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡
መልካም በዓል!
ዶ/ር እሸቱ ለማ
የቦሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ሥራ አስፈጻሚ


www.bunnabanksc.com
ቡና ባንክ
BUNNA BANK
Bank of the Visionaries!
የባለራዕዮች ባንክ!
መልካም
የደመራ
በዓል
8501
SCAN ME
JION US


POESSA
እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል
በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን የሚለው የግል ድርጅት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር፤ ሠራተኛ ቀጥራችሁ የምታሰሩ የግል ድርጅቶች በሙሉ ራሳችሁን እና ሠራተኞቻችሁን የማስመዝገብና የራሳችሁን እና የሰራተኞቻችሁን የጡረታ መዋጮ በወቅቱ የመክፈል ኃላፊነታችሁን በአዋጁ መሠረት እንድትወጡ እያሳሰበ፤ ብርሃነ መስቀሉ የፍቅርና የመተሳሰብ እንዲሆን መልካም ምኞቱን ይገልጻል።
መልካም በዓል!
የግል ድርጅት ሠራተኞች ማኅበራዊ ዋስትና አስተዳደር


እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል አደረሳችሁ!
የሚለው ግሪን ላይፍ ዴንታል ክሊኒክ ሳይሳቀቁ ይሳቁ ይላችኋል!
15+
Years
GreenLife
Speciality Dental Clinic
Dr. Robera Chala
Senior Expert Dental Surgeon
የምንሰጣቸው አገልግሎቶች
ኮስሞቲክስ - DENETSTRY እና ROOT CANAL TERAPY
CAD-CAM በመጠቀም በፍሎራይድ የተጠቁ ጥርሶችን ፍፁም ውበትን እናላብሳለን
የተለያዩ የብሬስ አማራጮችም አሉን
የተነቀሉና የወለቁ ጥርሶችን በ IMPIANT እንተክላለን
አድራሻ ቦሌ አትላስ መብራቱን እንደተሻገሩ ራካን ህንፃ 2ኛ ፎቅ
ይደውሉ
0988212222
www.Greenlifethiopia.com

# ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በመዲናዋ

በአብርሃም ገብሬ

ባለፉት ቀናት የተለያዩ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች እና አዳዲስ ኪነ ጥበባዊ ስራዎች በመዲናዋ አዲስ አበባ ለጥበብ አፍቃሪያን ሲደርሱ ቆይተዋል፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናትም የተለያዩ ጥበባዊ መሰናዶዎች ይደረጋሉ፡፡ ዛሬን ጨምሮ በሚቀጥሉት ቀናት ከተሰናዱ ኪነ ጥበባዊ ዝግጅቶች መካከል የሥዕል አውደ ርዕይ፣ የአዳዲስ መጻሕፍት ህትመት፣ የቴአትር መርኃ ግብር እና ሌሎች መሰናዶዎች ይገኙበታል፡፡ ለመረጃ ይሆንዎት ዘንድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል እንደሚከተለው አዘጋጅቷቸዋል፡፡

## መጻሕፍት

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ገበያ ላይ ጠፍተው የነበሩ አዳዲስ መጻሕፍት ለህትመት አብቅቷል፡፡ ለተደራስያን ከቀረቡ ነባር መጽሐፎች መካከል የራስ ሥዩም መንገሻ ‘የትውልድ አደራ’ እና የፕ/ር ሽብሩ ተድላ ‘የሕያው ፈለግ’ የተሰኙ መጽሐፎች ይገኙበታል። እንዲሁም የኢትዮጵያ ዳር ድንበር፣ ከደስታ ባለፈ ተፈጥሯዊ የሩካቤ ሂደትና ውጤቱ፣ ዝግመተ ለውጥ፣ አካባቢ እና ጤና በኢትዮጵያ፣ የተውኔት ዝግጅት መሠረታውያን፣ መንግሥትና ሀብት እና ታላቁ የግብርና ምርምር ሥርዓት መሪ የተሰኙ መጽሐፎች ታትመው ገበያ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ መጽሐፎቹ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጻሕፍት ማዕከል (ቡክ ሴንተር)፣ በጃፋር የመጻሕፍት መደብር፣ በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ጽህፈት ቤት እና በሌሎችም የመጻሕፍት መደብር የሚገኙ ናቸው፡፡

“የድምጽ እና የቋንቋ ሥርዓት” የተሰኘ አዲስ መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ በመምህር ምጽላል ድንግል ሙሉነህ የተጻፈው “የድምጽ እና የቋንቋ ሥርዓት” በቋንቋ ሥርዓትና ተያያዥ ቋንቋ ነክ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩር መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ በተለያዩ የመጻሕፍት መሸጫ መደብር ውስጥ ይገኛል ተብሏል፡፡

የታዋቂዋ ተዋናይት ሜሮን ጌትነት ‘ሌላ እውነት የለኝም’ የግጥም መድብል መጽሐፍ ለንባብ በቃ፡፡ በተለያዩ ፊልሞችና የቴሌቪዥን ተከታታይ ድራማዎች የምትታወቀው ሜሮን ጌትነት







አሁን ደግሞ በአዲስ የግጥም መጽሐፍ እንደገና ተመልሳለች፡፡ መጽሐፉ በተለያዩ የመጻሕፍት መደብሮች ውስጥ ይገኛል፡፡

## ሥዕል

“የተመለሱ እይታዎች” አውደ ርዕይ ተከፈተ፡፡ የሠዓሊ ኪሩቤል ተፈሪ የሥዕል ስራዎች የቀረቡበት “የተመለሱ እይታዎች” የተሰኘ የሥዕል አውደ ርዕይ ባለፈው ሳምንት ረዕቡ መስከረም 7 ቀን 2018 ዓ.ም ጀምሮ፣ ሐያት ሪጀንሲ ሆቴል ውስጥ በሚገኘው ፈንድቃ የባህል ማዕከል ውስጥ ለእይታ በቅቷል። የሰዓሊው የተለያዩ ጥበባዊ የፈጠራ ሥራዎች የቀረበበት የሥዕል አወደ ርዕዩ እስከ መጪው ጥቅምት 3 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ይቆያል ተብሏል።

## ቴአትር

በመዲናችን አዲስ አበባ ቅዳሜ እና እሁድ የተለያዩ ቴአትሮች ይታያሉ፡፡ 12ቱ እንግዶች የተሰኘው ቴአትር ቅዳሜ 8:30 ሰዓት በብሔራዊ ቴአትር ቤት ይታያል። 11፡30 ሰዓት ደግሞ ባሎችና ሚስቶች የተሰኘው ቴአትር በዚያው በብሔራዊ ቴአትር ይታያል፡፡ እሁድ በ8፡30 ሰዓት ደግሞ ንጉሥ አርማህ ቴአትር፣ እንዲሁም እምዬ ብረቷ የተሰኘው ቴአትር ደግሞ በዚሁ በብሔራዊ ቴአትር 11፡30 ሰዓት ላይ ይታያል።

በሀገር ፍቅር ቴአትር ቤት ደግሞ እሁድ በ8:00 ሰዓት የደመና ዳንኪረኞች የተሰኘው ቴአትር ይታያል፡፡ በተጨማሪም በቀጣይ ቀናት በብሔራዊ ቴአትር የሚታዩት ማክሰኞ በ11፡30 ሰዓት ሾስቱ አይጦች፣ ረዕቡ በ11፡30 ሰዓት የቅርብ ሩቅ ቴአትር፣ ሐሙስ ቀን 11:30 ሰዓት ሽምጋይ ቴአትር፣ አርብ በ11፡30 ሰዓት የሕይወት ታሪክ በብሔራዊ ቴአትር ለጥበብ አፍቃሪያን ለዕይታ ይቀርባሉ፡፡




ፎቶ- ከገፀ ድር

በከተማችን ከተዘጋጁ ኪነ ጥበባዊ መሰናዶዎች በከፊል

# የቁጥር ጨዋታ

## የባለፈው ሳምንት ጥያቄ መልስ

ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባቢዎቻችን ባለፈው ሳምንት የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችሁ ነበር፡፡ የጥያቄው ትክክለኛ አሰራርና መልስ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ መልሱን ለማግኘት የምንጠቀመው ስሌት የመጀመሪያና ሁለተኛ ረድፍ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ የተደረደሩትን ቁጥሮች ደምረን የምናገኘው ውጤት የመጨረሻው ረድፍ ላይ ያለው ቁጥር መምጣት አለበት፡፡ በዚህ መሰረት 275986 + 342758 = 618744 ይሆናል፡፡ ከዚህ አንጻር የጥያቄው ትክክለኛ መልስ አራት (4) ነው፡፡

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 2 | 7 | 5 | 9 | 8 | 6 |
| 3 | 4 | 2 | 7 | 5 | 8 |
| 6 | 1 | 8 | 7 | 4 | 4 |

## የዛሬው የቁጥር ጨዋታ

ውድ አንባቢዎቻችን ከታች በምስሉ ላይ የቁጥር ጨዋታ አቅርበንላችኋል። በጥያቄ ምልክቱ ቦታ ላይ መግባት ያለበት ትክክለኛው ቁጥር ስንት ነው? በጥያቄው ራስዎን እየፈተኑ ይዝናኑ፡፡ የጥያቄውን መልስ በቀጣይ ሳምንት ዕትማችን ይዘን እንቀርባለን፡፡



# የመስቀል ዘገባ ትውስታዎች በውጭ መገናኛ ብዙኃን


ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
የውጭ ሀገራት ዜጎችን ጭምር ቀልብ የሚስበው የመስቀል ደመራ በዓል

በአብርሃም ገብሬ

ኢትዮጵያ የህብራዊ ባህሎችና ሃይማኖቶች ሀገር ነች፡፡ ከዚህ ህብራዊነት የመነጩ በርካታ እሴቶች አሏት፡፡ እነዚህ እሴቶች ኢትዮጵያውያንን በህብረት ያስተሳሰሩ፣ የእርስ በእርስ መተማመንን ማሳደግ የቻሉና ኢትዮጵያ ነጻነቷን አስጠብቃ እንድትቆይ ጉልህ ሚና የተጫወቱ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያውያንን አንድነት ካበጃጁ ነባር እሴቶች መካከል አንዱ መስቀል ነው፡፡

በኢትዮጵያውያን ዘንድ በደማቅ ሁኔታ ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ መስቀል ነው፡፡ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ የመስቀል በዓል መልከ ብዙ ገጽታዎች ተሰጥቶት ይከበራል፡፡ በዚህ በዓል የተራራቁ ቤተሰቦች በዓሉን አስታክከው ይጠያየቃሉ፡፡ ቅራኔ ውስጥ የነበሩ ሰዎች እርቀ ሰላም ያወርዳሉ፡፡ እንዲሁም ልጄን ለልጅህ የሚባባሉበት በዓልም ነው፤ የመስቀል በዓል፡፡ ይህም መስቀል ከሃይማኖታዊ ዳራው ባሻገር ከማህበረሰቡ ትውፊቶች ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው አመላካች ነው፡፡ በዚህ ዓምድም በተለይ የውጭ መገናኛ ብዙሃን ስለ ኢትዮጵያ የመስቀል በዓል አከባበር ከዚህ ቀደም ምን ዘገቡ የሚለውን በጨረፍታ ልናስቃኛችሁ ወድደናል፡፡

## የመስቀል ሌላኛው ገጽ

የመስቀል በዓል ታሪካዊ ዳራው ሃይማኖታዊ ቢሆንም፤ ኢትዮጵያውያን ግን እንደየአካባቢያቸው ወግና ልማድ ያከብሩታል፡፡ መስቀል ከኃይማኖታዊው በዓል ባለፈ በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ በባሕላዊ ይዘቱ ይከበራል፡፡ ይህ ኃይማኖታዊ እና ባሕላዊ ትውፊት የሚስተዋልበት በዓል የውጭ ሀገር ዜጎችን ቀልብ መግዛት የቻለ ሆኗል። በዚህም ኢትዮጵያ የቱሪስት መዳረሻ እንድትሆን ኹነኛ ሚና እየተጫወተ ይገኛል፡፡

ዩኔስኮ የማይዳሰሱ ባህላዊ ቅርሶች በሚያስተዋውቅበት "ዩኔስኮ አይሲኤች" (UNESCO ICH) ገጸ ድር ላይ ስለ መስቀል በዓልና አከባበር አስመልክቶ ባሰፈረው ጥናታዊ ጽሁፍ፣ "እንደ መስቀል ያሉ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት አብዛኛው ህዝቦቿ በጋራ የሚያከብሯቸውና እርስ በእርስ የሚያስተሳስሯቸው ናቸው፡፡ መስቀልም ሀይማኖታዊ በዓል መሆኑ ቢታወቅም የተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች በየራሳቸው ባህል፣ ትውፊትና እምነት አካሄድ ነው የሚያከብሩት፡፡" ሲል በዓሉ ካለው ሃይማኖታዊ ፋይዳ ባሻገር በርካታ ማህበራዊ ጠቀሜታዎች እንዳሉት አስፍሯል፡፡

በሀገራችን የተለያዩ አካባቢዎች የመስቀል በዓል አከባበር ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት እንደሚከበር ይታወቃል፡፡ የመስቀል በዓል ከሃይማኖታዊ በዓልነቱ ባሻገር የማህበረሰቡ ወግና ልማድ በስፋት የሚንጸባረቅበት በዓል ነው፡፡ ሙሽሮች ሰርጋቸውን በመስቀል በዓል ይፈጽማሉ፡፡ ሩቅ ይኖር የነበረ ወዳጅ ዘመድ ለመስቀል ተገናኝቶ ይጠያየቃል፡፡ ስለዚህ መስቀል የተኳረፉ የሚታረቁበት፣ የተቸገሩ ድጋፍ የሚያገኙበት በዓል ነው። በአጠቃላይ መስቀል በኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ ወግና ልማዱ፤ ትውፊቱና ዕሴቱ ጎልቶ የሚንጸባረቁበት አመታዊ ክብረ በዓል ነው፡፡ ይህንን ታሳቢ በማድረግ የመስቀል በዓል አከባበር ከኢትዮጵያውያን አልፎ የአለም ቅርስ ከሆነ ሰነባብቷል፡፡ መስቀል በተባበሩት መንግስታት የሳይንስ የትምህርትና ባህል ማዕከል (ዩኔስኮ) በዓለም ቅርስነት መዝግቦታል።

በተለይ መስቀልን በድምቀት የሚከበርበት ወርሃ መስከረም ብዙ የውጭ ጎብኚዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡበት ነው፡፡ እንዲሁም እንደ መስቀልና ኢሬቻ ባሉ በዓላት ምክንያት ኢትዮጵያውያን ጭምር ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ የሚንቀሳቀሱበትና ጉብኝት የሚያደርጉበትም ነው፡፡ ከዚህ አንጻር መስቀልን ለማክበር የመጡ የውጭ ዜጎች ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ሌሎች የቱሪስት መዳረሻዎች እግረ መንገዳቸውን የመጎብኘት ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት መስቀል ቱሪስቶችን ኢትዮጵያ እንዲመጡ የሚያደርግ ትልቅ በዓል ነው።

የዝግጅት ክፍላችን የተመለከታቸው የውጭ ሀገር መገናኛ ብዙሃን ዘገባዎች እንደሚያሳዩት፣ ቱሪስቶች የመስቀል በዓልን ለማክበር በሚመጡበት ወቅት ከሚያስገኙት የውጭ ምንዛሬ ባሻገርም ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ስለ ኢትዮጵያ በጎ ምስል ይዘው እንዲመለሱ ያደርጋል። የኢትዮጵያን ጉብኝታቸው ለሌሎችም ስለሚያጋሩ ተጨማሪ ቱሪስቶች እንዲመጡ ዕድሎችን ያመቻቻል፡፡ ከዚህ አንጻር የመስቀል በዓል መልከ-ብዙ ፋይዳ እንዳለው መመልከት ይቻላል፡፡

## መገናኛ ብዙሃን ስለመስቀል በዓል

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የኢትዮጵያውያን ልዩ መገለጫ የሆነው የመስቀል በዓል አከባበር የውጭ ሀገር መገናኛ ብዙሃን ትኩረት ሰጥተው እየዘገቡት ነው፡፡ ዓለም አቀፍ ታዳሚ ያላቸው መገናኛ ብዙሃን መስቀልን ከዜና ሽፋንነት ባሻገር በፎቶ ዘገባ ጭምር ሽፋን በመስጠት ላይ ናቸው፡። በተለያዩ የሀገራችን አካባቢዎች የመስቀል በዓል እንዴት እንደተከበረም በፎቶ ዘገባ ለዓለም ማህበረሰብ አድርሰዋል። ውድ የአዲስ ልሳን ጋዜጣ አንባብያን ከታች የተጠቀሱት የጊዜ አቆጣጠሮች በሙሉ በአውሮፓውያን የጊዜ አቆጣጠር መሆናቸው ከወዲሁ ለመግለጽ እንወድዳለን፡፡

የካናዳው የቴሌቪዥን ጣቢያ "ሲቢሲ ኒውስ" (CBC News) በመስከረም 27 ቀን 2007 "Meskel festival lights up Ethiopia" በሚል ርዕስ ስለመስቀል አከባበር ዘግቧል፡፡ "በድምቀት የሚከበረውን የመስቀል በዓልን ለማክበር በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እና የውጭ ሀገር ጎብኝዎች በመዲናዋ አዲስ አበባ በሚገኘው መስቀል አደባባይ ተሰባስበዋል፡፡ ከኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የተውጣጡ ካህናት፣ መነኮሳትና ምእመናን በዝማሬና በእልልታ በመዘመር ትዕይንቱን ይበልጥ ደማቅ አድርገውታል፡፡ የመስቀል በዓል የሚከበረው የኢትዮጵያ የዘመን መለወጫ በተከበረ ማግስት ነው፡፡ ይህም ማለት ዝናባማው የክረምት ወራት አብቅቶ ብርሃናማው ወራት ጅማሮ ላይ የሚከበር በመሆኑ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ልዩ ስሜት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል። መስቀል አደባባይ እየተከበረ ባለው በዚህ በዓል ላይ፣ በዓሉን ታድሞ ያገኘነው ወጣት ሰለሞን ድጋፌ ለሲቢሲ ኒውስ እንዲህ ብሏል፤ 'ይህ በዓል የኢትዮጵያ ህዝቦች የእርስ በእርስ መፈቃቀራቸውንና መተሳሰራቸውን የሚያሳዩበት አጋጣሚ ነው። ይህ ቀን ለኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ ቀን ነው' ብሏል" በማለት ሲቢሲ ኒውስ በወቅቱ ዘግቧል፡፡

የእንግሊዙ ታዋቂ ጋዜጣ "ዘ ጋርድያን" 'Ethiopia: Fireworks and flowers prevail as capital marks the festival of Meskel' በሚል ርዕስ በጥቅምት 5 ቀን 2010 ባወጣው ዘገባ፣ የመስቀል በዓል አከባበር "እጅግ አስደናቂና ውብ ትዝታን የሚተው በዓል ነው" በማለት አስነብቧል፡፡ "መስቀልን ለማክበር የበዓሉ አክባሪዎች ነጭ ልብስ ለብሰው በየጎዳናው ሲንቀሳቀሱ፣ ሲዘምሩና ሲጫወቱ በዓሉን ለመታደም የመጣ የውጭ ዜጋ ሳይቀር የበዓሉ ድባብ ይጋባበታል፡፡ ... በታክሲ ጓደኛዬ ወደ ሚገኝበት ሀያት አካባቢ እየተጓዝኩ የመስቀል በዓል ምን ያህል ትልቅ በዓል እንደሆነ ማስተዋል ችያለሁ። የፒራሚድ ቅርጽ የሚመስሉ ደመራዎችን በየመንገዱ ተሰርተው አይቻለሁ፡፡ ኋላም ላይ እነዚህን ደመራዎች የበዓሉ አክባሪዎች ተሰባስበው ሲያቃጥሉ (ሲያበሩ) ተመልክቻለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ በበዓሉ አክባሪዎች ፊት ትልቅ ደስታ ይታያል፡፡ ልጆችም በችቦው ዙሪያ ይጫወታሉ፡፡ ይሄ የበዓሉ ትዕይንትም ለታዳሚያን መቼም የማይዘነጋ ትዝታን ትቶ የሚያልፍ ኩነት ነው" ሲል ጋዜጣው አትቷል፡፡

ሌላው ስለ መስቀል በስፋት ያስነበበው ሮይተርስ ነው፡፡ "Ethiopians mark festival of finding Jesus' cross" በሚል ርዕስ በመስከረም 27 ቀን 2016 ሮይተርስ በሰራው ዘገባ፣ "የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች በኢትዮጵያ የክርስትና ባህል ውስጥ ካሉት ቅዱሳን በዓላት አንዱ የሆነው የመስቀል በዓል ለዓመታት ሲያከብሩ ቆይተዋል፡፡ የመስቀል በዓልን ለማክበር በመቶዎች የሚቆጠሩ ካህናትና ዘማሪዎች ነጭ ካባ ለብሰው በመዲናይቱ አዲስ አበባ መስቀል አደባባይ ይገኛሉ። በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብም በዓሉን ለማክበር ከቤቱ ይወጣል፡፡ በደማቅ አልባሳት የተዋቡ የበዓሉ አክባሪዎች ፊት ላይ ደስታ ጎልቶ ይነበባል" በማለት፤ ሮይተርስ ስለመስቀል አስነብቧል፡፡

ቢቢሲ በመስከረም 27 ቀን 2018 "Ethiopia's Meskel festival: Bonfires, robes and crosses" በሚል ርዕስ ረዥም ሃተታ ስለ መስቀል በዓል አከባበር አስነብቧል፡፡ እንዲህ በማለት ሃተታው ይጀምራል፤ "የኢትዮጵያውያን የአዲስ ዓመት የመጀመሪያው ትልቅ በዓል መስቀል ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ክርስትና እምነት አስተምህሮ ተከትሎ የሚከበረው የመስቀል በዓል፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል ከተደበቀበት ለመፈለግ ከተደረገው ሃሰሳ ጋር የተያያዘ ነው" በማለት የመስቀልን ታሪካዊ ዳራ ያብራራል፡፡

ቢቢሲ ከላይ በተጠቀሰው ዘገባው "በተለይ ደመራ በመባል የሚታወቀውን የበዓሉ ዋዜማ በዋና ከተማዋ አዲስ አበባ መሃል በሚገኘው መስቀል አደባባይ በመገኘት በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ያከብሩታል፡፡ ኢትዮጵያውያን እጅግ ያማረ አልባሳት ለብሰው በዚህ የመስቀል አደባባይ ይሰባሰባሉ፡፡ የተለያዩ ዝማሬዎችን በመዘመር እጅግ ያማረ ድባብ በታዳሚው ላይ ይፈጥራሉ" በማለት የመስቀልን ሕብረ-ባህላዊ ገጽታውን ዳስሷል፡፡

የመስቀል በዓል አከባበርን በሚመለከት ሰፊ ሃተታ ያስነበበው ሌላኛው ሚዲያ ደግሞ "WordPress.com" ነው። በፈረንጆቹ መስከረም 13 ቀን 2020 "Meskel Celebration in Ethiopia" በሚል ርዕስ ባስነበበው ሰፊ ሃተታ፣ ንግሥት እሌኒ "ሕዝቦቿ እውነተኛው መስቀል የተቀበረበትን ጢስ ያመለከተ ትልቅ እሳት እንዲያቃጥሉ አዘዘቻቸው። እነሱም እንደተባሉት አደረጉ፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ከተደበቀበት ለመፈለግ ነው ደመራ ደምረው ያቀጣጠሉት፡፡ ኢትዮጵያውያንም ይህንን ትውፊት መነሻ በማድረግ ነው በመስቀል ዋዜማ ደመራ ደምረው የሚያቀጣጥሉት፡፡ መስቀልን በደመቀ መልኩ የሚያከብሩትም ለዚህ ነው" በማለት፤ ስለ መስቀልና ኢትዮጵያውያን መስቀልን ለምን እንደሚያከብሩት ጽፏል፡፡

"What is Ethiopian Orthodox Meskel celebration?" በሚል ርዕስ "TRT Africa" በፈረንጆቹ መስከረም 28 ቀን 2023 በሰራው ዘገባ ደግሞ፣ በኢትዮጵያውያን የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ከሚከበሩት በዓላት መካከል አንዱ መስቀል መሆኑን ያብራራል፡፡ የመስቀል በዓል የሚከበርበት ታሪካዊ ዳራው በማብራራት የሚጀምረው ዘገባው፣ "በመስቀል በዓል ዋዜማ ምእመናን በየመንገዱና በየቤተ ክርስቲያኑ አደባባዮች ላይ ደመራ ደምረው ያቀጣጥላሉ፡፡ ደመራውን ከበው መንፈሳዊ ዝማሬዎችን የሚዘምሩ እንዳሉ ሁሉ፤ መስቀልን እንደየ ባህላቸው የሚያከብሩ ማህበረሰቦችም አሉ" በማለት ስለ መስቀል ያትታል፡፡

እነዚህ ከብዙ በጥቂቱ የዳሰስናቸው ናቸው።ይህ የአደባባይ በዓል የበለጠ ደምቆ እና ፈክቶ እንዲታይ በመዲናዋ እየተከናወነ ያለው የኮሪደር ልማት አበርክቶው ትልቅ ነው፡፡ ባማሩ ጎዳናዎች እና አደባባዮች ማክበር እሴቱ የበለጠ ጎልቶ እንዲወጣ እና ዓለም ሀብቱን በሚፈለገው ልክ እንዲረዳው የሚያደርግ ነው፡፡ አዲስ አበባን የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ ከተሰሩ ስራዎች መካከል ኮሪደር አንዱ ስለመሆኑ ስራው ህያው ምስክር ነው፤ መልካም በዓል!

# የምሽት ንግድ በ4 ኪሎ

• በአራዳ ክፍለ ከተማ በመንገድ ዳር ከሚገኙ የንግድ ተቋማት 873 የሚሆኑት በምሽትም እንደሚነግዱ ተገልጿል

በሸዋርካብሽ ቦጋለ

በሰለጠነው ዓለም በማታው ክፍለ ጊዜ የጦፈ የንግድ እንቅስቃሴ እንደሚደረግ መረጃዎች ያመላክታሉ። ኤ.ቢ.ሲ ኒውስ በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2024 (24 ሃወርስ ትራዲንግ ሲቲስ) በሚል ርዕስ ባወጣው መረጃ በተለይ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በእስያ እና በአንዳንድ የአረቡ ዓለም ሀገራት የምሽት ንግዶች ይዘወተራሉ። በዚህም በዓመት ውስጥ ከ200 ቢሊዮን ዶላር በላይ የሚገመት ሀብት ይንቀሳቀሳል።

እንዲህ ያለው ባህል በኢትዮጵያም መዘውተር ጀምሯል። በተለይ የኮሪደር ልማት ስራን ተከትሎ በዚህ ረገድ መልካም የሚባል አዝማሚያ ተፈጥሯል። የአዲስ አበባ ከተማ ደግሞ ድርጊቱን በህግ ማዕቀፍም ጭምር አስደግፋ ወደማስተግበር ከገባች ሰነባብታለች። ለመሆኑ በአራዳ ክፍለ ከተማ የዚህ ደንብ ትግበራ በምን ደረጃ ላይ ይገኛል? ምን ያህሎችስ እየተጠቀሙበት ነው? የሚል ፍተሻ አድርገናል።

የኮሪደር ልማት በተከናወነባቸው የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ዋና መንገዶች ዳር የሚገኙ የንግድ ተቋማት እስከ ምሽት ሶስት ሰዓት ተኩል ድረስ እንዲሰሩ የሚያደርግ የምሽት ንግድ ተቋማትና ትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 185/2017 የካቲት 29 ቀን 2017 ዓ.ም ጸድቆ ወደ ትግበራ መግባቱ ይታወሳል፡፡ ተቋማቱ እስከ ምሽት ቆይተው ህዝቡን እንዲያገለግሉ መደረጉ ለነጋዴዎች ተጨማሪ ገቢ የሚፈጥር ከመሆኑም በላይ በተለያዩ ምክንያቶች በቀኑ ክፍለ ጊዜ መሸመት የማይችለውን ማህበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርግ እንደሆነ ይታመናል፡፡



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
በ4 ኪሎ ፕላዛ እና አካባቢው የምሽት ንግድ በጥቂቱ

የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል የምሽት የንግድ እንቅስቃሴ ያለበትን ደረጃ ለመታዘብ በከተማዋ የተለያዩ አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ ቅኝት አድርጓል፡፡ አራት ኪሎ አካባቢ አንዱ የቅኝታችን አካል ሲሆን፣ አደባባዩን ተከትሎ መሬት ውስጥ በተሰራው መተላለፊያ ዙሪያ ያሉ በርካታ ሱቆች በምሽት የሞቀ የንግድ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉ ማወቅ ችለናል፡፡

በአራት ኪሎ አደባባይ ዙሪያ በንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ወጣቶች የምሽት ንግዱ ተጨማሪ ገቢ የማግኘት ዕድል እንደፈጠረላቸው ነግረውናል፡፡ በአራዳ ክፍለ ከተማ አራት ኪሎ ፕላዛ ስር በኮስሞቲክስ ንግድ ስራ የተሰማራችው ወጣት ሴና ገብሬ፣ የምሽት ንግድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሞቀ መምጣቱንና መልካም የሚባል ገቢ እንደሚገኝበት ነው የተናገረችው፡፡

አካባቢው የ24 ሰዓት ጥበቃ ያለው በመሆኑ አምሽቶ ለመስራት ከፀጥታ አንፃር ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ የምትጠቅሰው ወጣቷ፣ አልፎ አልፎ የትራንስፖርት ችግር ከማጋጠሙ በስተቀር ስራው ምቹና አትራፊ መሆኑን ገልፃለች፡፡

## ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ በስላሴ ወደ ቀበና፣ ከአራት ኪሎ ወደ እንጦጦ ባሉ መስመሮች የተካሄደውን የኮሪደር ልማት ተከትሎ የምሽት የንግድ እንቅስቃሴው ደምቋል

በአዲስ ፋና ጠቅላላ ሸቀጣሸቀጥና ሆቴሎች ንግድ አክሲዮን ማህበር የሽያጭ ሰራተኛ የሆኑት ወይዘሮ ፍሬህይወት ደበበ የተባሉ አስተያየት ሰጪም በኮሪደር ልማት በለሙ አካባቢዎች ያሉ የንግድ ተቋማት እስከ ምሽቱ 3፡30 አገልግሎት መስጠታቸው ለከተማዋም ሆነ በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ተጨማሪ ገቢ የሚፈጥር እንደሆነ ገልፀው፣ ሆኖም ግን የህብረተሰቡ የምሽት ግብይት ልማድ አናሳ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በምሽት የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ አሽከርካሪዎች ከታሪፍ በላይ ማስከፈል፣ በቂ የትራንስፖርት አገልግሎት አለመኖር፣ የመብራት መቆራረጥ እና መሰል ችግሮች በስራው ላይ የተወሰነ ክፍተት እየፈጠሩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በአራዳ ክፍለ ከተማ በተለምዶ 'ቱሪስት ሆቴል' ተብሎ በሚጠራ አካባቢ አትክልትና ፍራፍሬ (ጁስ) ቤት ከፍተው እየሰሩ ያሉት ነጋዴ አቶ ሃብተሚካኤል ወልዱም የንግድ ተቋማት እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ከሰላሳ አገልግሎት እንዲሰጡ በከተማ አስተዳደሩ ከተወሰነ ጀምሮ የምሽት ንግድ ስራ እየሰሩ እንደሆነ አስታውሰው፣ ይህም ነጋዴዎችን ተጠቃሚ የሚያደርግና ለከተማዋ እድገትም አጋዥ መሆኑን ነው ያስረዱት።

በአራዳ ክፍለ ከተማ ንግድ ፅህፈት ቤት የንግድ ኢንስፔክሽንና ሬጉላቶሪ ቡድን መሪ አቶ ገለታው ለገሰ፣ በክፍለ ከተማው ካሉ 8 ወረዳዎች በ6ቱ የኮሪደር ልማት ስራዎች መሰራታቸውን ጠቅሰው፣ የኮሪደር ልማት በተካሄደባቸው አካባቢዎች በመንገድ ዳር ካሉ የንግድ ተቋማት 873 የሚሆኑ ተቋማት የምሽት ንግድ እየሰሩ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

እነዚህ ድርጅቶች የስራ ባህላቸውን እንዲያሻሽሉ በተደጋጋሚ የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራዎች ሲሰሩ ከመቆየታቸውም ሌላ የከተማ አስተዳደሩም እስከ ምሽቱ ሶስት ሰዓት ከሠላሳ ድረስ እንዲሰሩ ደንብ ማውጣቱን ያስታወሱት አቶ ገለታው፣ ይህን ለማስፈፀምም የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት መዘርጋቱን አንስተዋል፡፡

በአብዛኛው ነጋዴ ዘንድ የምሽት ስራ የተለመደ ባለመሆኑ አንዳንዶቹ መደበኛ ስራቸውን ቀን ሰርተው በማታው ክፍለ ጊዜ እንደሚዘጉ ገልፀው፣ ለእነዚህም በር ለበር በመዞር ግንዛቤ መስጠቱን አስታውቀዋል፡፡

በክፍለ ከተማ ደረጃ በጉዳዩ ላይ ሰፊ ግንዛቤ የተፈጠረ ቢሆንም አንድ ቀን አምሽተው ሰርተው በሌላው ጊዜ ደግሞ የማይሰሩ እንደሚያጋጥሙ ገልፀው፣ ለዚህም የመኖሪያ አካባቢያቸው ከአዲስ አበባ ውጪ እና አዲስ አበባም ሆኖ ዳር ወይም ራቅ ያለ አካባቢ መሆኑን በምክንያትነት ይጠቅሳሉ ብለዋል፡፡

የትራንስፖርት አለመኖርና ከፀጥታ ጋር ተያይዞም እንደ ችግር እንደሚያነሱ የጠቀሱት አቶ ገለታው፣ ጉዳዩን በሚመለከት የወጣው ደንብ ቁጥር 185/2017 የንግድ ስራውንና የትራንስፖርት አገልግሎቱን ሊያሳልጥ የሚችል እንደሆነም አስረድተዋል። የትራንስፖርትና መሰል ችግሮችን ለማቃለል ከሚመለከታቸው መንግስታዊ ተቋማት ጋር እየተሰራ ሲሆን፣ ለችግሩ እልባት ለመስጠት ጥረት እየተደረገ ነውም ብለዋል፡፡

በምሽት ንግድ ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች፣ ሰራተኞችና ባለቤቶች መኖሪያ ቤት ከስራ ቦታቸው ሩቅ ቢሆንም እንኳ ለችግር እንዳይጋለጡ የፀጥታ መዋቅሩ እንደ አዲስ አበባ በየቦታው በትኩረት እየሰራ መሆኑን አውስተው፣ ከተማ አቀፍ ስራ በቅንጅት እየተሰራ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ገለታው ገለፃ፣ የንግድ ተቋማት በምሽት የስራ እንቅስቃሴያቸው ላይ እንደሚያጋጥማቸው ከሚያነሱት የፀጥታና ትራንስፖርት ችግር፣ የፓርኪንግ አገልግሎት እጥረት በተለይ በኮሪደር የለሙ መንገዶች ዳር ተሽከርካሪ ማቆም አለመቻል ደንበኞች በቀላሉ መጥተው መገበያየት እዳይችሉ አድርጓል፡፡

ታድያ የምሽት ንግድ በሚሰራባቸው አካባቢዎች ተሽከርካሪ በጊዜያዊነት አቁሞ መግዛት የሚቻልበትን አግባብ በማመቻቸት ችግሩን ለመፍታት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በስራ ቦታ እና መኖሪያ አካባቢም የፀጥታ ችግር እንዳያጋጥማቸው በየክፍለ ከተማው ያሉ የሰላም ሰራዊት አባላት፣ የፖሊስ አካላትና ደንብ አስከባሪዎች በቅንጅት እየሰሩ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

የአዲስ ልሳን ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል በአራዳ ክፍለ ከተማ ተዘዋውሮ ባደረገው ቅኝት ከፒያሳ ወደ አራት ኪሎ፣ ከአራት ኪሎ በስላሴ ወደ ቀበና፣ ከአራት ኪሎ ወደ እንጦጦ ባሉ መስመሮች የተካሄደውን የኮሪደር ልማት ተከትሎ የምሽት የንግድ እንቅስቃሴው የሞቀ መሆኑን ታዝቧል፡፡ በተለይም 4 ኪሎ ፕላዛ እና 4 ኪሎ የገበያ ማዕከል እና የመኪና ማቆያ ለአካባቢው ልዩ ድምቀት ፈጥረዋል፡፡

4 ኪሎ የገበያ ማዕከል እና የመኪና ማቆሚያ ከመሬት በታች የተገነቡ ዘመናዊ 102 የስጦታና የአልባሳት መደብሮች፣ ካፍቴሪያዎች፣ ማንበቢያ ስፍራዎች፣ ሱፐር ማርኬቶችን ያካተተ ነው፡፡ በተጨማሪም ከ100 በላይ ተሽከርካሪዎችን በአንድ ጊዜ ማቆሚያና በአንድ ጊዜ እስከ 5 ሺህ ሰዎችን መሰብሰብ የሚያስችል የፕላዛ፣ የአምፊ ቴአትርና የተለያዩ የጥበብ ስራዎችን ማቅረቢያ ስፍራዎችን ይዟል። በተመሳሳይ 4 ኪሎ ፕላዛም በውስጡ የሀገር ውስጥ አልባሳት፣ መዋቢያዎች፣ ወርቅና ብር መሸጫ ቤቶች፣ የስልክ መሸጫዎች፣ የፈጣን ምግብ አገልግሎት እና መሰል የንግድ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ እነዚህ ስፍራዎች ለምሽት ንግድ ስራ ተጨማሪ አቅምና ድምቀት ፈጥረዋል፡፡

AMN CONSTRUCTION PLC

P.BOX. 9176
0115226999 / 0115227359
0945408348 / 0919912526
amnconstructionplcamn@gmail.com
nchibssa@gmail.com

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

ኤኤምኤን አስመጪና ላኪ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ማንኛውንም የኮንስትራክሽን እና የግብርና እቃዎች ከተለያዩ ሀገራት አስመጥተን ባሉበት ቦታ እናቀርባለን!

**የምንሰጣቸው አገልግሎቶች**

- ✓ የቀላል እና ከባድ ተሽከርካሪዎች ሽያጭ፣
- ✓ ጄኔሬተሮች እና ኮምፕረሰሮች ከነ መለዋወጫቸው፣
- ✓ የጉድጓድ ቁፋሮ እቃዎች እና መለዋወጫዎች፤
- ✓ የማንኛውም ተሽከርካሪ ጎማዎች፣ ባትሪዎች፣ ፊልተሮች እና ወ.ዘ.ተ የመረጡትን እቃ ለማዘዝ በ 0945408348 ወይም 0919912526 ይደውሉ!
- ✓ የእርሻ እና ግንባታ ማሽኖች፣
- ✓ የግንባታ እቃዎች፣ የትራክተር እና የማሽነሪዎች ጎማ

ከድርጅታችን ጋር አብሮ ለመስራት ከፈለጉ በማንኛው ጊዜና ሰዓት ወደ ቢሮአችን በመምጣት አልያም በመደወል ማናገር የሚችሉ መሆኑን ስንገልጽ በደስታ ነው፡፡ እኛ ዘንድ ከመጡ ኪሳራ ብሎ ነገር አይታሰብም፡፡

ይህንን ዓላማችሁን ለማሳካት ወደ ኤ.ኤም.ኤን ኮንስትራክሽን ኃላ/የተ/የግ/ማህበር ይደውሉ፤ ያሉበት ቦታ ድረስ መጥተን ፍላጎታችሁን እናሟላለን፡፡

**A.M.N Construction PLC**

Car spare parts

1. Tractor spare parts
2. Excavator and it's spare parts
3. Different Machineries Lubricants
4. Generators spare parts
5. All kinds of Battery.......

+971508589125 +8615626207446
P.BOX. 9176
amnconstructionplcamn@gmail.com
nchibssa@gmail.com
http://www.amnplc.com
https://t.me/AMNGeneralspare
https://t.me/AMNimportexport
Telegram (https://t.me/AMNGeneralspare)

**ለበለጠመረጃ:-**

0115582353 / 0115227359 0945408348 / 0919912526
+971508589125 P.BOX. 9176



City Government of Addis Ababa, Office of the Auditor General

## ለአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎችና ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ በሙሉ፤ እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በከተማ አስተዳደሩ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 77/2014 ተጠሪነቱ ለከተማው ምክር ቤት ሆኖ እንደገና የተቋቋመ ሲሆን በከተማ አስተዳደሩ ስር ባሉ በመንግሥት ተቋማት እና ልማት ድርጅቶች አምስት የኦዲት ዓይነቶች ማለትም የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት፣ የገቢ ኦዲት፣ የአካባቢ ኦዲት እና ልዩ/የማጭበርበር ኦዲት እያከናወነ ይገኛል፡፡

ከመስሪያ ቤታችን ዓላማ አንዱ በከተማ አስተዳደሩ ሥር በሚገኙ የመንግስት ተቋማት ውስጥ ለተለያዩ የልማት ሥራዎች የተመደበው በጀት ግልጽነት እና ተጠያቂነት ባለው ሁኔታ ለህዝብ ጥቅም መዋሉን በማረጋገጥ ስለ ሁኔታው ለከተማ አስተዳደሩ ምክር ቤት መረጃ መስጠት በመሆኑ ስለ ከተማ አስተዳደሩ ዕቅዶች አፈጻጸም እና በጀት አጠቃቀም ውጤታማነት አስተማማኝ መረጃ አግኝቶ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር ምክር ቤቱን የሚያግዝ ጠንካራ የኦዲት ሥርዓት በመዘርጋት፣ አገልግሎቱን አስፍቶ መንግስት የያዘው ዘላቂ የልማትና የመልካም አስተዳደር ዓላማዎች እንዲሳኩ አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

ለወደፊቱም የተሰጡንን ህዝባዊ ኃላፊነቶች በአግባቡ በመወጣት የህዝብ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ በትጋት የምንሰራ መሆናችንን እየገለፅኩ መላው የከተማችን ነዋሪዎች ውስን የሆነውን የመንግስትና የህዝብ ሀብት ከብክነት ለመከላከል ለምናደርገው ጥረት ከጎናችን እንዲሆን ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡
ብርሃነ መስቀሉ የሰላም፣ የፍቅር እና የመቻቻል ዘመን እንዲሆን እንመኛለን!

**መልካም በዓል!**

**የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ኦዲተር መ/ቤት**



ባህል እና ኪነ ጥበብ ቢሮ
አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ!

ለመላው የከተማችን ነዋሪዎች በሙሉ የአዲስ አበባ ባህል እና ኪነ-ጥበብ ቢሮ እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ እያለ መልካም ምኞቱን ሲገልጽ በታላቅ ደስታ ነው! ቢሮአችን አዲስ አበባ ከተማ የብዝኃ ባህል ማዕከል እንደመሆኗ የመቻቻልና የአብሮነት ከተማ እንድትሆን፣ የሀገራችን መልካም ባህላዊ እሴቶች እና ቅርሶች ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ እንዲቻል እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የሀገራችን እና የመዲናችን መልካም ገጽታ ከፍ በሚያደርግ መልኩ በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ-ጥበብ ቢሮ ዘርፉን ከማሳደግና ከማስተዋወቅ አንጻር ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየሰራ የሚገኝ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ በከተማችን የሚገኙ አማተር የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎችን በማቋቋም፣ በማደራጀት፣ በማሰልጠንና በማብቃት እንዲሁም የኪነ-ጥበብ ማህበረሰቡ ከተማችንን የሚመጥን ስራዎችን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ ረገድ አበረታች ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መዲናችን አዲስ አበባ የዕደ-ጥበብ ስራዎች ማዕከል እንድትሆን እና ዘርፉ ተመራጭ እንዲሆን የማጠናከርና የመደገፍ ስራ እየሰራ ይገኛል፡፡ በዚሁ አጋጣሚ ሁሉም በከተማችን የሚገኙ የሀይማኖት ተቋማት፣ የኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች፣ የዘርፉ ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ነዋሪዎች ከጎናችን በመሆን ለከተማችን የባህል እና የኪነ-ጥበብ ዘርፍ መጠናከር የድርሻችሁን እንድትወጡ ጥሪያችንን እያስተላለፍን መላው የከተማችን ነዋሪዎች እንዲሁም ኢትዮጵያውያን በሙሉ ዓመቱ የሰላም፣ የመደጋገፍ እና የአብሮነት እንዲሆን እንመኛለን!





## መልካም የመስቀል በዓል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል እና ኪነ ጥበብ ቢሮ

በመጀመሪያው የኢትዮ ሪል እስቴት አዋርድ ላይ ተሸላሚ የሆነው

Temer PROPERTIES

# ቴምር ፕሮፐርቲስ

በ2008 ዓ.ም በሁለት ባለ ራዕዮች ሀሳብ ትልቁን ጉዞ የጠነሰሰ፣ ከ500 በላይ ከፍተኛ ጥራት ያላቸውን የመኖሪያ አፓርታማዎችንና የንግድ ሱቆችን ለደንበኞቹ በጥራት እና በተመጣጣኝ ዋጋ አጠናቅቆ ያስረከበ ቴምር ፕሮፐርቲስ ትልቅ ጉዞን የጠነሰሰ በእድገት አጎልብቷል፡፡

ቤትን እንደ ዳቦ ለብዙሃን ለማድረስ ተልሞ የተነሳው ቴምር፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በተዘጋጀው የኢትዮ ሪል ስቴት አዋርድ ላይ፣ በተመጣጣኝ ዋጋ የመኖሪያ ቤት እና የንግድ ሱቆችን ገንብቶ በማቅረብ ዘርፍ ብቸኛ አሸናፊ የሆነው ቴምር ፕሮፐርቲስ፣ አሁን ላይ በተደራጀ መዋቅር ከ 800 በላይ ሰራተኞችን ከእህት ኩባንኛዎቹ ጋር በመተባበር በጥራት እና በፍጥነት ገንብቶ በማስረከብ ግንባር ቀደም ሆኗል፡፡

በትልቅ ራዕይ የጀመረው ቴምር ፕሮፐርቲስ፣ የሪል ስቴት ዘርፉን ሽያጭን በአዲስ ዘርፉን ሽያche አቅጣጫ በማስቀየር እንዲሁም የተለያዩ ቴክኖሎጂ እና ፕላትፎርምዎችን በመጠቀም ለነባርም ሆነ ለአዲስ ደንበኞቹ ምቹ የሆነ የሰራር ሂደት መዘርጋታችን ተመራጭ ያደርገናል፡፡



በከተማችን በተለያዩ ቦታዎች ላይ ጥራት ምቾት ዋጋን አገናዝቦ በተቀመጠላቸው ጊዜ የሚደርሱ የመኖሪያ ቤት እና የንግድ ሱቆችን ለማቅረብ ሙሉ ዝግጅቱን ጨርሶ ደንበኞቹን በመጠባበቅ ላይ ይገኛል፡፡

ተጨማሪ ማብራሪያዎችን እና መረጃዎችን ለማግኘት የነፃ ስልክ መስመራችን **6033** ወይም በስልክ ቁጥር **+251 975 666 699** እንዲሁም **www.temerproperties.com** ይጎብኙን

# የአዲስ ህይወት በር

- የለነገዋ የሴቶች የተሀድሶ እና የክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል 1 ሺህ 692 ሴቶችን በተለያየ ሙያ በማሰልጠን ወደ ስራ እንዲሰማሩ አድርጓል



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ለነገዋ የሴቶች የተሀድሶ እና የክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል አዲስ የህይወት ምዕራፍ እንድትጀምር ያደረጋት ወጣት ሃሴት ሀብታሙ

በፋንታነሽ ተፈራ

እሴቶቻችን የአብሮነታችን እና የአንድነታችን ስንቆች መሆናቸው የመስቀል በዓል አንድ ማሳያ ነው:: የእምነቱ አስተምህሮ እንደሚናገረው፣ ንግስት ኢሌኒ መስቀሉን ለማግኘት ወጥታለች ወርዳለች፤ ፈተናዎችንም ተጋፍጣለች፤ በመጨረሻ ግን የልቧን መሻት እውን ማድረግ ችላለች:: ሰዎችም ህልማቸውን መኖር የሚችሉት የሚያጋጥማቸውን ፈተና በጽናት መሻገር ሲችሉ ነው:: በሂደቱ የሚያጋጥሙ እድሎችንም ሳያባክኑ መጠቀም የግድ ይላል::

በዚህ ጽሁፍ በብርቱ ከተፈተኑ እና በ"ለነገዋ የሴቶች የተሀድሶ እና የክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል" ነጋቸው ላይ ተስፋ እና ብርሃን ከፈነጠቀላቸው መካከል የወጣት ሃሴት ሀብታሙን (ለዚህ ጽሁፍ ስሟ የተቀየረ) የሕይወት መንገድ ለማስቃኘት ወደድን::

ሃሴት የተወለደችው በድሬዳዋ ከተማ ሲሆን በወጣትነት ዕድሜዋ ያላለፈችበት አስከፊ የህይወት ገፅ የለም:: የህፃንነት እድሜዋን ሳታጣጥመው፣ የእናት ፍቅርን ሳትጠግበው፤ በቅጡ ሳትስቅ እና ሳትጫወት፣ የደስታዋንም ጊዜ ሳታውቅ በ1999 ዓ.ም ስምንት ዓመት ሳይሞላት ወደ አዲስ አበባ መጣች::

"እናትና አባቴ በዝቅተኛ ኑሮ የሚኖሩ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው:: እናቴ ሰው ቤት እንጀራ እየጋገረች ታኖረን ነበር:: በዚሁ ሁኔታ ላይ አባቴ አረፈ። በቤታችን አብሮን የሚኖር አንድ የስጋ ዘመዴ ሊደፍረኝ ሞከረ:: እናቴም 'አንቺ ስትደፈሪ አይኔ ከሚያይ ወደ አዲስ አበባ ሂጂ' ብላ በመኪና አሳፍራ ላከችኝ" ስትል ከእናቷ የተለየችበትንና ወደ አዲስ አበባ የመጣችበትን አጋጣሚ ታስታውሳለች::

ዘመድም ሆነ የምታውቀው ሰው የሌላት ሃሴት፤ ከድሬዳዋ ያመጣት መኪና አውቶቡስ ተራ አወረዳት:: ከዚያም "በእግሬ ወደ አብነት እየተጓዝኩ አለቅስ እንደነበር አስታውሳለሁ፤ ይህንን የተመለከቱ ሜክሲኮ የሚኖሩ የጎዳና ልጆች 'እኛም እዚሁ ነው ያደግነው' ብለው ተቀበሉኝ፤ ጠንካራ እንድሆን መከሩኝ" ትላለች::

ህይወቷ ጎዳና ላይ ቀጠለ፤ ነገር ግን ምቾት አልባና የመከራ ኑሮ ነበር። ከአስከፊው ሁኔታ ለመውጣት መኖሪያ ቤት በቤት ሰራተኛነት መስራት እንደምትፈልግ ለጓደኞቿ ነገረቻቸው:: ስራ አፈላልገውላት ህፃን ልጅ እየተንከባከበች፤ ትምህርት እየተማረች ያለ ደመወዝ ለመስራት ተስማምታ መኖሪያ ቤት ገባች:: ይሁን እንጂ እየሰራች ለመማር አሰሪዎቿ አልፈቀዱላትም:: ከአቅሟ በላይ በምትሰራው ስራ ደከማት፤ ወገቧንም ታመመች፤ ይህ አልበቃ ብሎም ከእለታት አንድ ቀን በአሰሪዎቿ ተደበደበች:: ይህን ግን መታገስ ስላልቻለች ድጋሚ የጎዳና ኑሮ ጀመረች::

"በፊት ከማውቃቸው ጓደኞቼ ጋር ተቀላቀልኩ:: ተስፋም ቆረጥሁ። ጓደኞቼ ሲጋራ አጭሰው የጣሉትን በማጨስ፣ ጫት ሲቅሙ እየቃምኩ፤ ቀስ በቀስ ሁሉንም ነገሮች ለመድኳቸው" ስትል ወደ ሱስ ህይወት እንዴት እንደገባች ትናገራለች::

ተምራ ጥሩ ደረጃ ላይ ለመድረስ ተስፋን የሰነቀችው ሃሴት ሽራ ወጥረው በሚኖሩበት አካባቢ ለሚኖሩ ነዋሪዎች መማር እንደምትፈልግ ነገረቻቸው። ሸመልስ ሃብቴ ትምህርት ቤት 1ኛ ክፍል አስገቧት:: ነዋሪዎቹም በየተራ ምሳ እያመጡላት መማር ቀጠለች። መምህሮቿም ያበረታቷት እንደነበር አልሸሸገችም::

የጎዳና ህይወት በተለይ ለሴቶች ምን ያህል ፈታኝ እንደሆነ መገመት አያዳግትም:: ከእለታት በአንዱ ቀን ሀሴት፣ እንደ እናትና አባት የሚጠብቋት ጓደኞቿን በመኪና አደጋ እና በእስር ምክንያት ከአጠገቧ አጣቻቸው። በዚህም የ6ኛ ክፍል ተማሪ እያለች የአስገድዶ መደፈር ጥቃት ተፈፀመባት:: "ተረበሽኩ፣ ራሴን እንድጠላ ሆንኩ፤ ሁሉ ነገር አስጠላኝ" የምትለው ሃሴት በምትኖርበት ሽራ ውስጥ መጥተው የሚያበረታቷት መምህሮቿ ጉልበት ሆነዋት እስከ 9ኛ ክፍል እንደተማረች ትናገራለች::

10ኛ ክፍል ለመማር እየተዘጋጀች እያለ ወጣትነት አሸነፋት፤ እኩያ ጓደኛዋን አፈቀረች:: ትምህርትም አስጠላት፤ መማር ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸው የሚያሳድጓቸው ጓደኞቿ የሚለብሱትን ልብስ መልበስ እና የሚይዙትን ስልክ ማየት ጀመረች:: ትምህርቷን አቋርጣ፤ መጨረሻ ላይ ከፍቅሯም ከትምህርቷም ሳትሆን ቀረች::

ለሃሴት ትልቁ ፈተና ለፍቅር አለመታደሏ ሳይሆን ቀድሞ ይወድዳት በነበረው የፍቅረኛዋ ጓደኛ በድጋሜ መደፈሯ ነበር:: በዚህ አላበቃም፤ ላልተፈለገ እርግዝና ተዳረገች:: እሷም ልጇን በሆዷ ተሸክማ የጎዳና ኑሮዋን ቀጠለች:: በዚህ ህይወት ልጅ ወልዶ ማሳደግ ከባድ ሆኖ ተሰማት። የአራት ወር ነፍሰጡር ሆና ከጓደኞቿም ከነዋሪውም ብር ለምና በማጠራቀም እናቷ ጋር ልትወልድ ወደ ትውልድ አካባቢዋ ድሬዳዋ ሄደች::

እናቷ ጋር ለመውለድና በእናት ለመታረስ ብዙ ኪሎ ሜትሮችን አቆራርጣ ወደ ትውልድ ቀዬዋ የደረሰችው ሃሴት ያጋጠማት ግን እንዳሰበችው አልነበረም። "እናቴ ዲቃላ ይዘሽብኝ መጣሽ በማለት አላስገባ አለችኝ" ትላለች:: የሆነው ነገር ልቧን ቢሰብረውም ተስፋ ሳትቆርጥ በተወለደችበት አካባቢ በሚገኝ ቤተ ክርስቲያን ደጀሰላም ተጠግታ ቆየች:: ከአዲስ አበባ ይዛው በሄደችው ገንዘብ ቤት ተከራይታ ጫት በሚሸጥበት ቦታ ላይ ኦቾሎኒ በመሸጥ ኑሮዋን ትመራ እንደነበር ትናገራለች::

ዘጠኝ ወር በማህፀኗ የያዘችው ልጇ ይህችን ዓለም ሊቀላቀል ምጥ መጣ። ወደ ጤና ጣቢያም ሆነ ሆስፒታል የሚወስዳትና አይዞሽ የሚላት ማንም ከጎኗ እንደሌላት ስለምታውቅ፣ ቤተሰብ መምሪያ አምቡላንስ ጋር ደውላ እንዲወስዷት አደረገች:: ከ10 ደቂቃ በኋላ የአብራኳን ክፋይ ልጇን እንዳቀፈች ገልጻልናለች::

ከአጠገቧ የሚደግፋት ምንም ዓይነት ሰው የሌላት ሃሴት፤ ከሆስፒታል ልጇን አቅፋ ደሟ እየፈሰሰ የሚበላና የሚጠጣ ወደሌለበት ባዶ ቤት አመራች:: ከዚህ በኋላም "ደከመኝ፣ አመመኝ፣ ሰውነቴ ተንቀጠቀጠ፣ ሰርቶ መብላትም አልቻልኩም:: ተኛሁ፤ ረሃቤም ጠና" ስትል ሰው ኖሮት እንደሌለው በመሆኗ በጣም ተከፍታ እንደነበር ትናገራለች::

ወጣት ሃሴት፤ "በወለድኩ በ11ኛ ቀኔ ብር ጨረስኩ፤ የሚቀመስ ነገር ከቤቴ ጠፋ፤ አሁንም ተስፋ አልቆረጥኩም፤ እናቴ ጋር ደወልኩ:: ቤት እንደሌለች ነገረችኝ፤ ሲብስብኝ ሰው ግቢ ውስጥ ሄጄ ፀሐይ ላይ የተሰጣ ደረቅ እንጀራ ሰርቄ በላሁ" ስትልም የአራስ ቤት ረሃብ እስከ መስረቅ እንዳደረሳት ትገልፃለች::

ቤተ ክርስቲያን ምግብ አስመጥታ እየበላች 40 ቀን ሲሞላት ክርስትና እንዳስነሳች የምትናገረው ወጣቷ፤ እጇን ለልመና ላለመዘርጋት ልጇን አዝላ ጫማ የማሳመር ስራ ጀመረች:: ለሶስት ወርም ሰራች:: ይህ ግን አልቀጠለም:: ልጇ የሳንባ ምች ታመመባት:: ግራ ገባት፤ ቀኑ ጨለመባት፤ ብዙ የሆነችለትን ልጇን ይዛ ወደምታውቀው ከተማ አዲስ አበባ ተመለሰች::

ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ ስትመጣ በፊት የነበሩትን ጓደኞቿን አላገኘቻቸውም ነበር:: ለዕለት ጉርስና የታመመውን ልጇን ለማሳከም እጇን ለልመና ዘረጋች:: ባገኘችውም ብር ልጇን አሳከመችው፤ ዳነላትም:: መንገድ ዳር ሽራ ወጥራ እየኖረች መኖሪያ ቤት እየተመላለሰች ልብስ ማጠብ ጀመረች። ለትንሽ ጊዜ እንደ ሰራችም ሌላ ችግር ተደቀነባት። ታክሞ የዳነው ልጇ በድጋሜ የልብ ቱቦ መጥበብ ታመመባት:: ልጇን ለማሳከም ገንዘብ የሌላት ሃሴት ሃይማኖቷ በሚፈቅደው መሰረት በፀበልና እምነት ልጇ እንደዳነላት ትናገራለች::

ያጋጠማትን ፈተና እየተጋፈጠች በአስከፊ ሁኔታ ኑሮውን ስትመራ የቆየችው፣ ከሱስ መውጣት እንዳለባት የምታምነውና ነገን ተስፋ የምታደርገው ሃሴት፤ ከነበረችበት የጭንቅና መከራ ህይወት የሚያወጣት አጋጣሚ ተፈጠረላት:: ይኸውም ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከልን የመቀላቀል ዕድል ነው:: በሚያዝያ ወር 2017 ዓ.ም ወደ ማዕከሉ ገባች::

"እንደ ልጆች ስቄ፣ ቦርቄ ተጫውቼ፣ ለብሼ፣ ትምህርት ቤት ስሄድ ምሳ እቃ ይዤ አላውቅም፤ ቤተሰብ ያላቸው ሲጫወቱና ከቤተሰብ ጋር ሲያሳልፉ እኔ ጫት ስቅምና ሳጨስ ነበር:: በማዕከሉ ስገባ ግን የሌለኝን ቤተሰብ አገኘሁ። ተደሰትኩ፤ ታክሜም ከህመሜ ተፈወስኩ፤ በላሁ፣ ጠጣሁ፣ ለበስኩ፣ ሁሉም ተደረገልኝ" ስትል አዲስ ህይወት እንደጀመረች ትገልፃለች::

ወደ ገጽ 37 ዞሯል

ወጣት ሀሴት ለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል ገብታ ስልጠና መውሰዷ የትናንት ማንነቷን እንዳታስታውስ፣ ወደ ፊት እንድትራመድ፣ አላማ እንዲኖራትና ትልቅ ነገር እንድትመኝ አድርጓታል



# እንኳን ለ2018 ዓ.ም
## የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!



ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ2018 የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን እያልን፤ በዓሉ የሠላም፣ የፍቅር፣ የመተሳሰብ፣ የብልፅግና እንዲሁም እጅ ለእጅ ተያይዘን ከተማችን አዲስ አበባን የምናበለጽግበትና የምናዘምንበት እንዲሆንልን እመኛለሁ፡፡

ውድ የከተማችን ነዋሪዎች ተቋማችን የአዲስ አበባ ከተማ ግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የነዋሪውን ፍላጎት ማዕከል ያደረጉ አገልግሎቶች በከተማችን ለሚሠሩ ግንባታዎች ፈቃድ መስጠት፣ የኮንስትራክሽን ኩባንያዎችና ባለሙያዎች ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት መስጠት፣ በከተማው መዋቅራዊ ፕላን መሠረት በሚገነቡ ግንባታዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣ ሕንፃዎች ለተፈቀደላቸው ዓላማ አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ የመጠቀሚያ ፈቃድ መስጠት፣ በከተማችን የሚሠሩ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች የግንባታ ቅንጅት፣ ፈቃድና ክትትል ዙርያ የሚሠሩ ሥራዎች እንዲሁም የውጭ ማስታወቂያ ፈቃድና ቁጥጥር አገልግሎት አሠጣጥ ሥራዎችን በማዕከልና በየደረጃው በሁሉም ክፍለ ከተሞች በሚሰጠው የአገልግሎት እርከን መሠረት ለውድ ደንበኞቻችን እንደከዚህ ቀደሙ ሁሉ በቀጣይም አገልግሎቱን ይበልጥ አጠናክረን የምናገለግላችሁ መሆኑን እየገለጽን በድጋሚ በዓሉ የሠላም፣ የፍቅርና የደስታ እንዲሆንላችሁ ከልብ እመኛለሁ፡፡

**ኢንጂነር ህይወት ሳሙኤል**
**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የግንባታ ፍቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር**



## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል አደረሳችሁ!

ግራንድ አፍሪካ የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት በሀገራችን በአምራችነትም ሆነ በአገልግሎት ሰጪነት የሰሩ ተቋማት ለሀገር እና ለህዝብ ለሰሩት ስራ ምስጋና፣ ሽልማትና እውቅና በመስጠት የላቀ ስራ በመስራት እንዲዘልቁ ለማድረግ የተቋቋመ ብቸኛ የሽልማት ድርጅት ነው።

አቢሲኒያ የኢንደስትሪ ሽልማት ድርጅት የአቢሲኒያ የከፍተኛ ክብር ሎሬቶች ሽልማት ድርጅት እህት ኩባንያ በመሆኑ ተደራቢ ስም ላለመጠቀምና ኢትዮጵያ የአፍሪካ ዋና መቀመጫ በመሆኗ ራዕያችንም የአፍሪካን ተቋማት እንዲያቅፍ በመደረጉ ስሙ ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት በሚል ተቀይሯል።

የ2017 ዓ.ም ተሸላሚዎች የሚሸለሙበት ቀን ጥቅምት 2 ቀን 2018 ዓ.ም እና ጥቅምት 9 ቀን 2018 ዓ.ም ሲሆን የሽልማቱ ስፍራ በአድዋ ድል መታሰቢያ ፓን አፍሪካ አዳራሽ ነው።

**ግራንድ አፍሪካን የተቋማትና የአመራር ሽልማት ድርጅት**

**ትጉኃንን እንሸልማለን!**
**መልካም በዓል!**

**ለተጨማሪ መረጃ ስልክ 0911 - 510783 / 0930 – 329134 ይደውሉ።**

የጠዋት ፀሀይ

# የአደባባይ በዓላት በልጆች አንደበት

**በለይላ መሀመድ**

ልጆች በአደባባይ ስለሚከበሩ በዓላት ምን ያህል ታውቃላችሁ? ስለምታውቋቸው ነገሮች እርስ በእርስ ሀሳብ እንደተለዋወጣችሁ አምናለሁ። ጎበዞች! ልጆችዬ፤ የአደባባይ በዓላት በርካታ ህዝብ በተለያየ አልባሳት ተውቦና አሸብርቆ ወደ አደባባይ በመውጣትና በመሰባሰብ፤ እንደበዓሉ ሁኔታ በተለያዩ ስነ ስርዓቶች፣ በምስጋና እና በደስታ የሚያከብሯቸው ናቸው፡፡ የአደባባይ በዓላት ከሆኑት መካከል መስቀል ደመራ እና ኢሬቻ ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ በዓላት በድምቀት ከሚከበሩባቸው የአገራችን አካባቢዎች ደግሞ አዲስ አበባ አንዷ ነች።

እናም ልጆች በዓላቱን ከቤተሰቦቻችሁ፣ ከጓደኞቻችሁ፣ ከጎረቤቶቻችሁ፣ ከዘመድ አዝማዶቻችሁ ጋር አብራችሁ ማክበር ይገባችኋል፡፡ እኛም በዛሬው እትማችን በዓላቱን እንዴት እንደሚያከብሩ የነገሩንን ልጆች ለእናንተ በሚከተለው መልኩ አቅርበነዋል፡፡

ተማሪ ምህረት አድማሱ እባላለሁ፡፡ የምማረው በመሀል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው፡፡ ተወልጄ ያደግኩት ስድስት ኪሎ ልዩ ስሙ ቸሬ ሰፈር ነው፡፡ መስቀልንም ኢሬቻንም አከብራለሁ፡፡ በመስቀል በዓል ዋዜማ ላይ ችቦ በማብራት ነው ማክበር የምንጀምረው፡፡ በሚቀጥለው ቀን የሀበሻ ቀሚሴን ለብሼ ከቤተሰቦቸ ጋር በመሆን በተለያዩ የመዝናኛ ስፍራዎች ውስጥ እዝናናለሁ፡፡ ከዚያ ስንመለስ ድግሞ ቡና በማፍላት ቤቱን ሞቅ ሞቅ እናደርገዋለን፡፡ ዘፈን ይከፈትና ሁላችንም እንጨፍራለን፡፡

ኢሬቻን የማከብረው ለበዓሉ ተብሎ የተገዛልኝን ልብስ ለብሼ፣ ከእናቴ፣ ወንድምና እህቶቼ ጋር በዓሉ ወደሚከበርበት ቦታ በመሄድ ነው። በተጨማሪም፤ አክስት እና አጎታችን ቤት ሄደን እንጠይቃለን፡፡ በቤት ውስጥም ቡና ይፈላል፤ የኢሬቻ ዘፈን ተከፍቶ እንጨፍራለን፡፡ ከአዲስ አበባ ውጪ ወደሌላ አካባቢ ተንቀሳቅሼ ዘመድ ስለምጠይቅ በዓሉ በተለየ ሁኔታ ያስደስተኛል፤ እወደዋለሁ፡፡

የምማረው በመሀል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ስሜ ተማሪ ሳምራዊት ሽፈራው ይባላል፡፡ እድሜዬ 12 ነው፡፡ ተወልጄ ያደግኩት ሽሮ ሜዳ ነው፡፡ የመስቀል በዓልን የማከብረው ከዋዜማው ጀምሮ ነው፡፡ በመጀመሪያ አቅራቢያችን ወደሚገኘው ቤተ ክርስቲያን እሄዳለሁ። በዚያም የሚከናወነውን የደመራ ስነ ስርዓት ከቤተሰቦቼ እና ከጓደኞቼ ጋር እንከታተላለን፡፡ በቤተ ክርስቲያን ደመራ ይበራል፡፡ በደመራ ብርሃን ውስጥ ሆኖ የሚዘመሩ መዝሙሮች፣ እልልታ እና ጭብጨባው በጣም ያስደስተኛል፡፡ በዚያ ያለው መርሃ ግብር እንደተጠናቀቀም ወደቤቴ እመጣለሁ፡፡

በመቀጠልም ሰፈራችን ላይ ከቅርብ ጎረቤቶቻችን ጋር በመሆን እንደገና የደመራ በዓልን እናከብራለን፡፡ የምናከብረውም ቀኑን ሙሉ ሲደመር የዋለውን ደመራ በማብራትና እዮሃ አበባዬ መስከረም ጠባዬ... በማለት ነው፡፡ በሚቀጥለው ቀንም በዓሉ ሞቅ ደመቅ ባለ መልኩ መከበሩን ይቀጥላል፡፡

የመስቀል በዓል ሲከበር የተለየ ደስታና ስሜት ይሰማኛል፡፡ የደመራውን ስነ ስርዓት፣ የሰዎችን የበዓል አለባበስ ሳይ ያስደስተኛል፡፡ እኔ የምኖርበት ሽሮ ሜዳ አካባቢ የተለያዩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ስለሚገኙ የየራሳቸውን የበዓል አልባሳትን አያለሁ፤ ይህም ውስጤን ደስተኛ ያደርገዋል፡፡

ስሜ ሳሙኤል ሙላቱ ይባላል። 12 ዓመቴ ነው፡፡ የመሀል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪ ስሆን በአምስት ኪሎ አካባቢ ነው ተወልጄ ያደግኩት፡፡ ኢሬቻን የማከብረው፤ ከቤተሰቦቼ ጋር በዓሉ ወደሚከበርበት ስፍራ በመሄድ ነው። ከሄድን በኋላም አባገዳዎችና ሌሎች የበዓሉ ተሳታፊዎች ስርአቱን ሲያከናውኑ እከታተላለሁ።



ፎቶ በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ተማሪ ሳምራዊት ሽፈራው



ፎቶ- በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ተማሪ ሳሙኤል ሙላቱ



ፎቶ- በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል

ተማሪ ምህረት አድማሱ

በበዓሉ ላይ የሚታየው ሁሉ ደስ ይላል። በተለይ የወጣቶቹን ውዝዋዜ ማየት እና ዝማሬያቸውን መስማት ደስታ ይሰጠኛል፡፡ ወደ በዓሉ ማክበሪያ ቦታ ከየአቅጣጫው የሚገቡትን የበዓሉን ታዳሚዎች እና አልባሳቶቻቸውን ማየት ስለሚያስደስተኝ ሲገቡ እከታተላለሁ፡፡

ልጆችዬ፤ የአደባባይ በዓላት የሚፈጥሩት ስሜት እና ትዝታ በጣም ውብ እንደሆነ ሃሳባቸውን ካካፈሉን ልጆች ለመገንዘብ ችለናል። እናንተም ይህንን የመሰለ ስሜት እንደሚፈጥርባችሁ እናምናለን። በሉ ልጆች፤ የ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ እና የኢሬቻ በዓላት በመልካም ሁኔታ እንድታሳልፉ እንመኛለን፡፡

## 10 ልዩነቶችን ፈልጉ



## እንቆቅልሽ

### ያለፈው ሳምንት ጥያቄ

**በሶስት እግሩ ቆሞ የሚፈነጥዝ**

**መልስ፡-** መ. ወጥ

## የዚህ ሳምንት ጥያቄ

**እራሱ ሳይቀምስ የቆረሰውን ለሌላ ያጎርስ**

ሀ. እጅ

ለ. እናት

መ. ባል

**ልጆች መልስ ይሆናል የምትሉትን በዌብ ሳይታችን አድርሱን፤ እኛም በተደጋጋሚ የመለሰውን እንሸልማለን፤ ስለዚህ ተሳተፉ፤ ተሸለሙ::**


Siinqee
EMPOWERED. TOGETHER BANK
እንኳን ለ2018 ዓ.ም
የመስቀል በዓል በሠላም አደረሳችሁ!
ሲንቄ ባንክ ለመላው ህዝበ ክርስቲያን እንኳን ለብረሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ እያለ፤
በዓሉ የፍቅር፥ የአብሮነት እና የሰላም እንዲሆንላችሁ ይመኛል!
Siinqee
EMPOWERED. TOGETHER BANK
መልካም በዓል!
ሲንቄ ባንክ በአንድነት ወደ ስኬት!


አዲስ አበባ አመራር አካዳሚ
ADDIS ABABA LEADERSHIP ACADEMY
እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ በ2017 በጀት ዓመት በከተማዋ ስር የሚገኙ ተቋማትን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም በስልጠና፣ በምርምር፣ በማማከርና ማህበረሰብ አገልግሎት በመገንባት በርካታ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል።
በ2018 በጀት ዓመትም የአቅም ግንባታ ስራውን አጠናክሮ ለማስቀጠል አዳዲስ አሰራሮችን በመቀየስ ከውትሮው በተለየ መልኩ ዝግጅቱን አጠናቋል። በመሆኑም በከተማዋ የምትገኙ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆናችሁ ተቋማት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንድትሆኑ ጥሪውን እያቀረበ፤ የመስቀል በዓል የሰላም፣ የጤና የብልፅግና ዓመት እንዲሆን ይመኛል፡፡
መልካም በዓል!
የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ





## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም በጤና አድሳችሁ፣ አደረሰን፤ የሚለው የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በ2017 ዓ.ም ትኩረት ሰጥቶ ከሰራቸው ተግባራት መካከል የአገልግሎት አሰጣጥና መልካም አስተዳደርን ማሻሻል፣ የወጣቶች፣ ሴቶች፣ አርሶ አደሮችና ነዋሪዎች ተጠቃሚነት፣ የልማት ስራዎች፣ የፕሮጀክት አፈጻጸም፣ ሰው ተኮርና የበጎ ፍቃድ ስራዎች፣ ከተማ ግብርና፣ ሌማት ትሩፋት፣ በድህነት ቅነሳና ዘላቂ ልማት፣ ሰላም ግንባታ፣ በሀገራዊና ከተማዊ ተልዕኮዎች እና እንደ ከተማ አስተዳደሩ ትኩረት የተደረገበት የኮሪደር ልማት ስራ በተጨማሪም በራስ አቅም ህብረተሰቡን በማሳተፍ የተሰሩ ስራዎች የክፍለ ከተማውን ገጽታ ከመቀየሩም በተጨማሪ ውበትን ለከተማችን አበርክቷል፡፡

የተከበራቹ የክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች አንዲሁም በየደረጃው ያላችሁ አመራሮችና ባለሙያዎች መጪው በ2018 ዓ.ም እንደ አደይ በመልካም ስራዎቻችን የምንደምቅበት፣ የመልካም አስተዳደር ስራዎቻችን የምንመለስበት፣ በአዲስ አገልግሎት አሰጣጥ የተገልጋዮችን እርካታ የምናሳድግበት እና የልማት ስራዎቻችንን በትጋት ከህብረተሰባችን ጋር የምንከውንበት፤ በአጠቃላይ በሁሉም ተግባሮቻችን በአፈጻጸም ወደ ተሻለ ስራ የምንልቅበት ብሩህ የደስታ፣ የብልጽግና፣ የብርሀን፣ የማንሰራራትና የከፍታ ዓመት የምናሳልፍበት እንዲሆን እያሳሰብኩ፤ ብርሃነ መስቀሉ የሰላም የደስታና የፍቅር እንዲሆን ልባዊ ምኞቴን እገልጻለሁ

**መልካም በዓል!!**

**የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ አድማሱ ደቻሳ**



## ለክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል አደረሳችሁ!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን በ2017 በጀት ዓመት ኅብረተሰቡንና በጎ ልብ ያላቸውን ነዋሪዎች በማስተባበር የበጎ ፈቃድ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ በርካታ ነዋሪዎችን ከማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንዲላቀቁ አድርጓል።

በተጨማሪም የከተማዋን እድገት የሚመጥኑ የአካባቢ ልማት ተግባራትን በማከናወንና ኅብረተሰቡን ያሳተፈ የተቀናጀ ሞዴል ብሎክ ልማት እንዲሁም የነዋሪውን የሠላም ተሳትፎ በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ውጤት አስመዝግቧል። ኮሚሽኑ ላስመዘገበው ሁሉን አቀፍ ውጤት የነዋሪዎቻችን ተሳትፎ የጎላ በመሆኑ ላቅ ያለ ምስጋናውን እያቀረበ በ2018 በጀት ዓመትም የተያዙ ግቦች ስኬታማ እንዲሆኑ ኅብረተሰቡ ተሳትፎውን አጠናክሮ እንዲቀጥል በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች ብርሐነ መስቀሉ የመተሳሰብና የፍቅር እንዲሆን እየተመኘን ህዝበ ክርስቲያኑ በዓሉን ሲያከብር የተቸገሩ ወገኖችን በመጠየቅና አብሮ በማሳለፍ ኢትዮጵያዊ የመተሳሰብ እሴትን በሚያጠናክር መልኩ እንዲሆን ኮሚሽኑ ይጠይቃል፡፡



# መልካም የመስቀል በዓል!

# ሕይወት የዘራበት ግንፍሌ

**• የወንዝ ዳርቻው የተለያዩ አገልግሎቶች ተሟልተውለት የመዝናኛ ስፍራ ሆኗል**

**በስንታየሁ ምትኩ**

በአዲስ አበባ ከተማ የእድገት ጉዞ ወንዞቹ በአዎንታዊና አሉታዊ መልክ ተፅዕኖ አሳርፈዋል፡፡ በከተማዋ ከ76 በላይ ትላልቅና ትናንሽ ወንዞች ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወንዞች የበርካቶች ታሪክና ትዝታ የተከተበባቸው፣ እንደአሁኑ የህዝብ ቁጥር ሳይጨምርና የመኖሪያ አካባቢ ሳይሆኑ የመጠጥ ውሃ፣ የግብርና ስራ እና የተለያዩ አገልግሎቶች ሲሰጡ እንደቆዩ ነዋሪዎቹ ይመሰክራሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል መነሻውን ስድስት ኪሎ አንበሳ ግቢ አካባቢ አድርጎ ኡራኤል አካባቢ የቀበና ወንዝን የሚቀላቀለው የግንፍሌ ወንዝ አንዱ ነው፡፡



ፎቶ -በገነት ወንድሙ

ከአዋሬ ከፍ ብሎ ያለው የግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ ገጽታ በከፊል

አቶ ማሞ መለሰ ትውልድና እድገታቸው አራዳ ክፍለ ከተማ ግንፍሌ እየተባለ በሚጠራው አካባቢ ነው። የ65 ዓመቱ ጎልማሳ እንደሚናገሩት፣ በድሮው ጊዜ የግንፍሌ ወንዝ በክረምት ወቅት የእንጨት ድልድይ ተሰርቶ ነበር የሚሻገሩት፡፡ በወንዙ አካባቢም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር መኖሪያ ቤቶች አልነበሩም፤ በደን የተሸፈነ ነበር። የወንዙ ውሃም ንፁህና ኩልል እያለ ነበር የሚወርደው፡፡ "ወንዙ ውስጥ እየገባን ብይ እና ጠጠር እናወጣ ነበር። ልብስ የምናጥበው፣ የምንዋኘው፣ ሰውነታችንንም የምንታጠበውም ወንዙ ላይ ነበር" ሲሉ ትውስታቸውን ያነሳሉ፡፡

ከጊዜ በኋላ በወንዙ ዳርቻ ሰዎች መኖሪያ ቤቶችን በብዛት እየሰሩ መኖር ሲጀምሩ፣ የሽንት ቤት ፍሳሽን ጨምሮ የተለያዩ ቆሻሻዎች የሚወገዱበት ስፍራ እየሆነና እየተበከለ መምጣቱን አቶ ማሞ ያነሳሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር ቤቶቹ ከወንዙ ዳርቻ ተጠግተው የተገነቡ በመሆናቸው በክረምት ወቅት ወንዙ ሲሞላ በንብረት ላይ የተለያዩ ጉዳቶች ያስከትል እንደነበር ያስታውሳሉ፡፡

አቶ ሲሳይ ወልዴም ትውልድና እድገታቸው ግንፍሌ አካባቢ ነው፡፡ የግንፍሌ ወንዝ የቀደመ ገጽታ በተለያዩ ምክንያቶች እየተቀየረ መምጣቱን የገለጹት፣ "በቤቶች የተከበበና መፈናፈኛ የሌለው፣ በተለያዩ የፕላስቲክና ፍሳሽ ቆሻሻዎች ከመበከሉ የተነሳ ውሃው ተፈጥሯዊ መልኩን ያጣ፣ መጥፎ ጠረን ያለውና ለኑሮ የማይመች አካባቢ" በማለት ነው፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደመሰከሩት፣ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣንና የተለያዩ ተቋማት ጥናቶችም እንደሚያሳዩት፣ የግንፍሌ ወንዝ የቆሻሻ መጣያ ሆኖ በከፍተኛ ደረጃ በመበከሉ ተፈጥሯዊ ወዙን አጥቶ፣ ሰዎች ለማየት የማይመርጡት፣ ቆሻሻ ለመጣል ካልሆነ በስተቀር ለልማት ጀርባቸውን የሰጡት ስፍራ ሆኖ ቆይቷል፡፡

የአዲስ አበባ ወንዞችን ለመታደግ የተጀመረው የወንዝ ዳርቻ ልማት የግንፍሌ ወንዝ ለምንም አገልግሎት ከማይውልበት በማውጣት ዳግም ህይወት እንዲዘራበት አድርጓል፡፡ አሁን ወንዙ ተፈጥሯዊ መልኩን ይዞ ይታያል። ይህንን ለማረጋገጥ ከአራት ኪሎ ወደ መገናኛ በሚወስደው መስመር ጥቂት ኪሎ ሜትሮች እንደተጓዝን ሺህ ሰማንያ እና ከላይኛው ቤተ መንግስት ጀርባ ያለውን አካባቢ ማየት በቂ ነው፡፡ የግንፍሌ ወንዝ የሚፈስበት ይህ አካባቢ በተፈጥሮ ድንቅ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ያለው ሆኖ፣ የወንዙ ዳርቻ በተለያዩ አበቦች፣ አረንጓዴ ሳሮች፣ የፍራፍሬና የተለያዩ ችግኞች የተሸፈነ ነው፡፡ በወንዙ ዳርቻ ሰዎች በእግር እየተጓዙ አሊያም አረፍ ብለው ነፋሻማውን አየር እየማጉ፣ አዕምሯቸውን ዘና የሚያደርጉበት የእግረኛ መንገዶች ተሰርተዋል፤ ማረፊያ ወንበሮችም ተዘጋጅተዋል፡፡ የከተማዋ ነዋሪዎች የክረምት የእረፍት ጊዜያቸውን ብቻቸውንና ከጓደኞቻቸው ጋር ከወንዙ የሚወጣውን የፏፏቴ ድምፅ እያደመጡ፣ የአካባቢውን ውበት እያደነቁ ሲዝናኑ ተመልክተናል፡፡

ወጣት እዮብ እንዳለን ፅዱና ውብ ሆኖ በተሰራው የግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ አረፍ ብሎ ሲዝናና ነበር ያገኘነው። አዋሬ አካባቢ በግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ ከቤተሰቡ ጋር ለአስራ አራት ዓመታት ያህል መኖሩንና ለልማት ሲነሱ አሁን ላይ አራት ኪሎ አካባቢ እየኖረ እንደሆነ ይናገራል። ቀደም ሲል የግንፍሌ ወንዝ በቆሻሻ የተበከለ፣ ለማየት ደስ የማይል፣ መጥፎ ሽታ ያለውና የወንዙ ቀለምም የጠቆረ እንደነበር ያስታውሳል፡፡

አሁን የወንዝ ዳርቻው አረንጓዴ ሆኖ፣ ማረፊያ ወንበሮች፣ የእግረኛ መንገድ፣ ካፌና የተለያዩ አገልግሎቶች ተሟልተውለት ለዓይን የሚስብ የመዝናኛ ስፍራ ሆኗል፡፡ በተግባረ ዕድ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የፋሽን ዲዛይን ተማሪ መሆኑን የሚናገረው ወጣት እዮብ፣ "በክረምት ወቅት መዝናኛ ቦታ እንደልብ ስለማይገኝ ብዙውን ጊዜ የማሳልፈው በቤት ውስጥ ነበር፡፡ አሁን ግን አየር እየወሰድኩ፣ ለብቻዬ በጥሞና የማሳለፍበት ደስ የሚል ስፍራ አግኝቻለሁ" ይላል፡፡

ወጣት ቃልአብ ተስፋዬ ደግሞ ከመካኒሳ አካባቢ መጥቶ ሲዝናና ነው ያገኘነው፡፡ በአንድ አጋጣሚ ከጓደኛው ጋር ሆኖ በአካባቢው ሲያልፍ ድንገት ቀልቡን ስቦት እንደተመለከተውና የእረፍት ጊዜውን ለማሳለፍ ምቹ መሆኑን በመረዳት ለሁለተኛ ጊዜ እንደመጣ ነግሮናል፡፡ የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ መልቀቂያ ፈተናን ወስዶ ውጤት በመጠባበቅ ላይ ያለው ወጣት ቃልአብ፣ ከዚህ በፊት መፅሐፍ ማንበብ የሚወድ ቢሆንም ምቹ ቦታ ማግኘት ስላልቻለ ሰፈር ውስጥ ኳስ በመጫወት ነበር ብዙውን የእረፍት ጊዜውን የሚያሳልፈው፡፡ "መጽሐፍ ማንበብ እወዳለሁ፤ ግጥምም እፅፋለሁ። በአረንጓዴ ዕፅዋትና አትክልቶች የተሸፈነውን፣ ፅዱና ነፋሻማ አየር ያለው ይህ ስፍራ ከራስ ጋር ለማሳለፍ ደስ የሚል ስለሆነ መርጬው ነው የመጣሁት፡፡" ይላል፡፡

"ወንዙ ከመበከሉ የተነሳ ዋና ዋኘቼ ቦርቄ ያደኩበትና የማውቀው አይመስለኝም ነበር፡፡" የሚሉት አቶ ማሞ፣ አሁን ግንፍሌ ፀድቶና ተፈጥሯዊ ውበቱ ተመልሶ በማየታቸው መደሰታቸውን ተናግረዋል፡፡ አቶ ሲሳይም የግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ ገፅታው መቀየሩን ይመሰክራሉ። በአበቦች፣ ለምለም ሳርና የተለያዩ ዕፅዋት ተሸፍኖ፣ ማረፊያ ወንበሮች፣ ካፌ፣ የእግረኛ መንገድ፣ ድልድይ ተሰርቶበት የአይን ማረፊያ ሆኗል፡፡

> **የወንዞች መልማት፣ ወደተፈጥሯዊ መልክና ገፅታቸው መመለስ የአዲስ አበባ ትልቁ ብስራት ነው። የወንዝ ዳርቻ ልማት ወንዞችን ወደ ተፈጥሯዊ ይዘታቸው ለመመለስና ጤናማ የሆነ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስችላል**

## ባለድርሻ አካላት ምን ይላሉ?

የከተማዋን ወንዞች የማልማትና የመጠበቅ ኃላፊነት ከተሰጣቸው ተቋማት መካከል የአዲስ አበባ ከተማ የከተማ ውበትና አረንጓዴ ልማት ቢሮ አንዱ ነው፡፡ የቢሮው ምክትል ኃላፊ ኢንጂኒዬር እንዳሻው ከተማ ለዝግጅት ክፍላችን እንደገለፁት፣ የአዲስ አበባ ወንዝና የወንዝ ዳርቻዎች ሰዎች ተጠጋግተው የሚኖሩባቸው፣ ብዙዎችም በህገ ወጥ መንገድ የሰፈሩባቸው፣ ቆሻሻ የሚጣልባቸውና የተበከሉ በመሆናቸው የከተማዋ ፀጋ ከመሆን ይልቅ ዕዳ ሆነው ነበር፡፡ ወንዞቹ የሚነሱባቸውና የሚጓዝባቸው ቦታዎች ብቻ ሳይሆን መዳረሻ በሆኑትና የግብርና ስራ በሚከናወንባቸው የታችኛው ተፋሰስ አካባቢዎች እንዲሁም አዋሽ ወንዝ ድረስ ጉዳት ነበራቸው፡፡

ወንዞቹ የወንዝነት ተፈጥሯዊ ባህርያቸውን አጥተው የቆሻሻ መጣያ የሆኑ፤ ለጤናማ የማህበረሰብ እድገት የማይመቹ ነበሩ፡፡ ኢንጂኒዬር እንዳሻው እንደገለፁት፣ የግንፍሌ ወንዝ በመሀል አዲስ አበባ የሚገኝ ሆኖ፤ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ተጠጋግተው የሚኖሩበት አካባቢ ነው። ከስድስት ኪሎ አንበሳ ግቢ እየተባለ ከሚጠራው አካባቢ ተነስቶ በአዋሬ

ወደ ገጽ 37 ዞሯል


SIKET BANK
መልካም
የመስቀል በዓል
እንኳን ለ2018
የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!
መልካም በዓል!
ስኬት ባንክ የስኬትዎ መሰረት!
8342
ስኬት ባንክ የስኬትዎ መሰረት!
www.siketbank.com
info@siketbank.com


የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር
ለመላው ኢትዮጵያውያን
እንኳን ለ2018 ዓ.ም
ለመስቀል በዓል በሰላም
አደረሳችሁ!!
የጉለሌ ክፍለ ከተማ አስተዳደር ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮችና የአዲስ አበባ ነዋሪዎች እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በሰላም አደረሳችሁ ሰላምን ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገደለ፤ የመስቀል ደመራ በተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ድርጅት(ዩኔስኮ) እውቅና ተሰጥቶት ዓለም አቀፋዊ ቅርስ ተብሎ የተመዘገበ ሲሆን ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሚያከብረው የአብሮነት በዓል ነው።
ደመረ ማለት፡- ጨመረ፣ አንድ አደረገ፣ ከሚለው የግዕዝ ቃል የተወረሰ ሲሆን መቀላቀልን፣ መገናኘትን፣ መሰብሰብን፣ መጣመርን፣ መዋሀድን፣ አንድነትና ህብረትን ያመላክታል፤ በመሆኑም የመስቀል ደመራ በዓል ለዓለም የአንድነታችን ማሳያና መገለጫ ሲሆን በዓመታዊ ድግግሞሽ መስከረም 17 የሚከበር ነው፤ በዓሉን በወንድማማችነትና እህትማማችነት አንድነታችንን በማጠናከር ሁሉም ሊያከብረው የሚገባ ዓለም አቀፋዊ ቅርስ ነው።
የ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል ሲከበር ለየት የሚያደርገው የህዝብ ቁጭት የሆነው የታላቁ ዓባይ ግድብ ምርቃት ስኬትና የታላላቅ ፕሮጀክቶች መጠናቀቅ ሀገራዊና ከተማዊ የብልጽግና ለውጥ በማምጣት ውስጥ የመንገድና የወንዝ ዳርቻ ስራዎች ከፍተኛ አፈጻጸም ማስመዝገብ መቻሉ ነው።
በአንድነትና በአብሮነት በዓሉን እንድታሳልፉ እየጠየቅሁ በድጋሚ መልካም በዓል እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ!!
መልካም የመስቀል በዓል!!
አቶ ወልዴ ወገሴ የጉለሌ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈጻሚ



ወ/ሮ ካባ መብራቱ
የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ! አደረሰን!

ለመላው የሀገራችን ህዝቦች፣ ለከተማችን እንዲሁም ለክፍለ ከተማችን ነዋሪዎች እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓልና የዘመናት ህልማችን ለሆነው የህዳሴ ግድብ ምርቃት አደረሳችሁ! አደረሰን!

በ2017 ዓ.ም እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ከተማ ትላልቅ ስኬቶችን ያስመዘገብንበት መሆኑ ይታወቃል:: በክፍለ ከተማችን በንፋስ ስልክ ላፍቶም ይህንኑ ፈለግ በመከተል በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚና በማህበራዊ ዘርፎች ትላልቅ ስራዎችን ያሳካንበት የስኬት ዓመት ሆኖ አልፏል::

ከነዚህም መካከል በራስ አቅም የለማው ከላፍቶ አደባባይ፣ አቃቂ ወንዝ ድረስ የሚዘልቀው ኮሪደር፣ ትምህርት ቤቶችና ጤና ጣቢያ ላይ ትኩረት በማድረግ የሰራናቸው የግንባታ ፕሮጀክቶችና በስራ እድል ላይ የተሰሩ ስራዎችን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል::

በከተማና በክፍለ ከተማ ያሳካናቸው የኮሪደር ልማትና ትላልቅ ፕሮጀክቶች ላይ የኢትዮጵያ የማንሰራራት ዘመን ጅማሮ ማብሰሪያ የሆነው የታላቁ ህዳሴ ግድብ ምርቃት ሲጨመር በእውነቱ ልዩ የመነሳሳት ስሜትን ይፈጥራል::

እነዚህን ስኬቶች የቀጣይ እቅዶቻችን መነሳሻና መስፈንጠሪያ አድርገን ለመጠቀም ያለንን ዝግጁነት እየገለፅኩ አዲሱ ዓመት የሰላም፣ የደስታና የብልፅግና ይሁንልን እላለሁ!

# መልካም በዓል!



## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል አደረሳችሁ!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለ2018 ዓ.ም የደመራና የመስቀል በዓል በሰላምና በጤና አደረሳችሁ እያለ፤ መልካም ምኞቱን ይገልጻል!!

የመስቀል ደመራ በዓል በሀገራችን የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ በታላቅ ድምቀት የሚከበር በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የትምህርት፣ የሳይንስና የባሕል ድርጅት (ዩኔስኮ) በማይዳሰሱ ቅርሶች የተመዘገበ ሲሆን በተለይ በመዲናችን አዲስ አበባ በመስቀል አደባባይ በርካታ ቱሪስቶች ጭምር በሚገኙበት በድምቀት የሚከበር በመሆኑ ለሀገራችን ብሎም ለከተማችን ትልቅ ኩራትና ድምቀት ነው፡፡

በዓሉ በሰላም እና በጤና እንዲከበር ቢሮው አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ለሚያጋጥሙ ማንኛውንም የጤና ጉዳይ አገልግሎት የሚሰጡ 2 ጊዜያዊ እና አንድ ተንቀሳቃሽ ክሊኒክ እንዲሁም በቂ የጤና ባለሙያዎችን፣ አምቡላንሶችን፣ አስፈላጊውን የህክምና ግብዓቶችን በማሟላት ለአገልግሎት ዝግጁ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም በከተማዋ የሚገኙ በሁሉም የጤና ተቋሞቻችን የህክምና አገልግሎት ማግኘት የምትችሉ ሲሆን፤ በተለይም በዓሉ በሚከበርበት መስቀል አደባባይ አካባቢ በተዘጋጁ ጊዜያዊ የህክምና መስጫ ቦታዎች፣ በዘዉዲቱ መታሰቢያ ሆስፒታል እና በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አስፈላጊውን የህክምና አገልግሎት ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸዉን ቢሮው ይገልጻል፡፡



## በድጋሚ መልካም የመስቀል በዓል፤
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጤና ቢሮ!



በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ
CLEANSING MANAGMENT AGENCY
— ADDIS ABABA CITY ADMINISTRATION —

**የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ**
እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በፍቅርና በጤና አደረሳችሁ ይላል። ኤጀንሲው አዲስ አበባ ከተማ በ2022 ፅዱና የደረቅ ቆሻሻ ዑደታዊ ምጣኔ ሐብቷን ተግባራዊ ያደረገች የአፍሪካ ሞዴል ከተማ ሆና ማየትን ራዕይ ሰንቆ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

አዲስ አበባ በኮሪደር ልማቱ እያመጣች ያለው ለውጥ ቀጣይነት እንዲኖረው የጽዳት ስራውም ተጠናክሮ እየተሰራ ይገኛል።

የከተማችን ጽዳት ዘላቂነት ሊረጋገጥ የሚችለው በሕብረተሰቡ ተሳትፎ በመሆኑ ሁሉም የከተማዋ ነዋሪ በጽዳት ስራው የድርሻውን እንዲወጣ መልዕክታችንን እናስተላልፋለን።



**መልካም በዓል!**
**አቶ ገዛኸኝ ዴሲሳ**
**የአዲስ አበባ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር**





BTE

**እንኳን ለ2018 ዓ.ም**
**የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!**

ለመላው ህዝበ ክርስቲያን እንኳን ለብረሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ አደረሰን! የሚለው የአዲስ አበባ ንግድ ሥራዎች ድርጅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በደንብ ቁጥር 152/2015 ዓ.ም የተቋቋመ መንግስታዊ የልማት ድርጅት ሲሆን የተለያዩ ምርቶችን በከተማዋ ለሚገኙ የመሠረታዊ ሸማቾች ህብረት ስራ ማህበራት፣ ለአገልግሎት ሰጭ ተቋማት እና ለሸማቹ ህብረተሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ በማሰራጨት ገበያ ማረጋጋትን ተልዕኮው አድርጎ እየሰራ መሆኑን በታላቅ ደስታ ይገልጻል፡፡

ድርጅቱ ለህዳሴ ግድብ ምርቃትም እንኳን ደስ አላችሁ እያለ፤ የሚሰጣቸውን አገልግሎቶች፡- የግብርና እና ኢንዱስትሪ ምርቶችን ማቅረብ፣ የምርት ሽያጭና ስርጭት፣ የንፁህ ጤፍ እንጀራ፣ የእንጀራ ድርቆሽ፣ ንፁህ ጤፍ ዱቄት፣ የዳቦ ምርት፣ የተለያዩ የባልትና ውጤቶችን ማዘጋጀት መሆኑን እየገለፀ በዓሉ የሰላምና የጤና እንዲሆን ልባዊ ምኞቱን ይገልጻል፡፡

**መልካም በዓል!**
**የአዲስ አበባ ንግድ ሥራዎች ድርጅት!**
**አድራሻ፣**
**ዋና መስሪያ ቤት ፒያሳ አሪ በከንቱ፣ ጀሞ 1፣ ለሚ ኩራ ወረዳ 2 እና 4፣**
**ጉለሌ እንጦጦ ፓርክ፣ አቃቂ ቃሊቲ ገበያ ማዕከል**

ከተፈሪ መኮንን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ቅዳሜ በወር አንድ ጊዜ የሚቀርብ

# ኢንተርፕራይዞችን በጥናት የመደገፍ ጥረት

**በለይላ መሀመድ**

የተፈሪ መኮነን ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነት እንዲሁም የምርት ጥራት ለማሳደግ የሚያስችል ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል፡፡ ይህንን ሥራ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ በ2018 በጀት ዓመት የሚተገበር ጥናት አካሂዷል፡፡ የዝግጅት ክፍሉም የጥናቱን ዓላማ፣ ግብ፣ ግኝቶችንና እንዲሁም ተያያዥ ጉዳዮች አስመልክቶ በኮሌጁ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ ምክትል ዲን አቶ ወንድምሲያምረኝ መኮንንን አነጋግሯቸዋል፡፡



ፎቶ- በመባጽዮን ሀ/ገብርኤል
ተፈሪ መኰንን ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ

እንደ ምክትል ዲኑ አቶ ወንድም ሲያምረኝ ገለጻ፤ ኮሌጁ ትኩረት አድርጎ ከሚሰራባቸው ሦስት መሰረታዊ ዘርፎች መካከል ተግባራዊ የጥናትና ምርምር ሥራዎች አንዱ ነው፡፡ በዚህም ረገድ ስልጠናዎች ምቹና ጥራታቸውን የጠበቁና ዘመናዊ እንዲሆኑ የሚቀዱ ቴክኖሎጂዎች እንዲሁም ስልጠናዎች ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ እንዲሆኑ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፡፡

"በ2018 በጀት ዓመት የዝግጅት ምዕራፍ ኮሌጁ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ዳሰሳ ጥናት አድርጓል" ያሉት ምክትል ዲኑ፤ የተደራጁና ወደ ሥራ የገቡ ኢንተርፕራይዞችን ዝርዝር ከክፍለ ከተማ ሥራና ክህሎት ጽህፈት ቤት በማምጣት የኮሌጁን ድጋፍ መፈለግ አለመፈለጋቸው ለማወቅ የሚያስችል ጥናት መደረጉን ጠቁመዋል፡፡ ጥናቱ 1 ሺህ 845 በሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች ላይ የተደረገ ሲሆን፤ 1 ሺህ 68 ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ እንደሚፈልጉ ለማወቅ ተችሏል። ኢንተርፕራይዞቹ ያነሷቸው የድጋፍ አይነቶችም በሥራ ፈጠራ (ኢንተርፕርነርሽፕ)፣ በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ በቴክኒካል ክህሎት፣ በካይዘን እንዲሁም ምርትና ምርታማነታቸውን ሊያሻሽሉ በሚችሉ የቴክኖሎጂና አዲስ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ታውቋል፡፡ እነዚህ ጉዳዮች የኮሌጁ ጥናት ዓላማዎች ተደርገው የተወሰዱ ናቸው፡፡

ኮሌጁ ኢንተርፕራይዞች በኮሌጆች የሚደገፉበትን ማዕቀፍ ባስተዋወቀበት ወቅት፤ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራዞች ግንዛቤ አለመኖር በጥናቱ ላይ ከተለዩ በርካታ ችግሮች መካከል ትልቁ እንደነበር አቶ ወንድምሲያምረኝ አንስተዋል፡፡ እንደሳቸው ማብራሪያ፤ ከፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ ድጋፍ ለመስጠት የሚሄዱ ባለሙያዎች ለኢንተርፕራይዞች የሚሰጣቸው ድጋፍ ክህሎታቸውን በማሳደግ ምርትና ምርታማነታችው እንዲጨምር እንዲሁም ጥራታቸው እንዲሻሻል እገዛ እንደሚያደርግላቸው ቢነገራቸውም ድጋፉን ማመንታትና ያለመቀበል ችግር መስተዋሉ ታውቋል፡፡

በኮሌጁ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽንና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ ምክትል ዲን አቶ ወንድምሲያምረኝ እንዳስረዱት፣ ጥናቱ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ከወረዳ 1 እስከ ወረዳ 8 ድረስ የሚገኙ በመንግስት የተደራጁ 1 ሺህ 845 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ ነው የተካሄደው፡፡

የጥናቱ ግኝት 1 ሺህ 68 የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ የሚፈልጉ መሆናቸውን አሳውቋል። የጥናት ቡድኑ የድጋፍ ፍላጎታቸውን ማወቅ ብቻ ሳይሆን የሚሰጠውን የድጋፍ አይነት ማስተዋወቅ ነው፡፡ እነዚህን የድጋፍ ፍላጎት ያሳዩትን ኢንተርፕራይዞች ዓመቱን ሙሉ በመደገፍ ለውጥ እንዲያመጡ ያግዛል፡፡ የኮሌጁ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፉ ውጤት ኢንተርፕራይዙ በድጋፍ ያፈራው ሀብት ይቀመራል፡፡ በ2018 በጀት ዓመት ኮሌጁ በእቅድ የያዘው ኢንተርፕራይዞች በሚደረግላቸው ድጋፍ ብቻ ከ2 ነጥብ 1 ሚሊየን ብር በላይ ትርፍ ያገኛሉ የሚል ግብ ነው ሲሉም አክለዋል፡፡

ሌላው የኢንተርፕራይዞች ምርትና ምርታማነት እንዲሁም የምርት ጥራታቸውን ያሻሽላሉ የሚል ነው። አብዛኛውን ጊዜ በጋርመንት፣ በቆዳ፣ በእንጨት ስራዎች በተሰማሩ በርካታ ኢንተርፕራይዞች ላይ የጥራት ችግር ይስተዋላል፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ነው ኮሌጁ በጥናት ላይ ተመስርቶ ወደ ሥራ የገባው፡፡ የሙያ ብቃት ምዘና በማካሄድ ማረጋገጥና በተመዘኑበት ሙያ ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ ላይ ትልቅ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ድጋፍ ከሚሰጣቸው ኢንተርፕራይዞች ውስጥ 73 በመቶ የሚሆኑትን በሙያ ብቃት ምዘና ብቁ የማድረግ ግብ ተቀምጧል፡፡ በዓመቱ መጨረሻ ብቁ የሆነ ምርትና ምርታማነቱ የጨመረ ሀብት ያፈራ ኢንተርፕራይዝ ማየት ዋናው ግብ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ኮሌጁ በ2018 በጀት ዓመት ድጋፍ የሚደረግላቸው ኢንተርፕራይዞችን ለመደገፍ በሚያደርገው ሂደት የዝግጅት ምዕራፍ ላይ ይገኛል፡፡ በዝግጅት ምዕራፉ እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ከሰነድ ወደ ተግባር ርክክብ ማድረግና የጥናቱን ግኝት ማቅረብ ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ኮሌጁ ቀደም ሲል ሲደግፋቸው የነበሩትን ነባር ኢንተርፕራይዞች ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ማድረግ ነው፡፡ ወደ ተግባር ምዕራፍ ለመሸጋገር የአሰልጣኝ ምደባ፣ የብቃት ማረጋገጫ (ሲኦሲ) ምዝገባ እንዲሁም ቀደም ሲል የተሰጠውን የኢንተፕርነር (ስራ ፈጣሪነት) ስልጠና የወሰዱ ሰልጣኞች የሲ ኦ ሲ ምዘናም እየተካሄደ ነው፡፡

በኮሌጁ የቀድሞ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ቴክኖሎጂ ሽግግር ዘርፍ አስተባባሪና የአሁኑ የ2018 የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ኢንተርፕራይዞች ፍላጎት ለመለየት የተጠናውን ጥናት ያስተባበሩት አቶ ብርሀኑ ዘገየ በጉዳዩ ላይ ሀሳባቸውን አጋርተዋል፡፡ እንደ አስተባባሪው አቶ ብርሀኑ ገለጻ፤ 1 ሺህ 68 ኢንተርፕራይዞች ለድጋፍ ከተለዩ መካከል፤ በአምራች (በማኑፋክቸሪንግ) ዘርፍ የተሠማሩ በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ በልብስ ስፌት የተሰማሩት ቁጥር 110 በመያዝ ቀዳሚ ናቸው፡፡ በሽመና 7 እና በደረቅ ምግብ ዝግጅት 41 ተገኝተዋል፡፡

አጠቃላይ ከ719 ኢንተርፕራይዞች መካከል 192 የሚሆኑትን መጠይቅ በማስሞላት በምን እና መቼ መደገፍ እንደሚፈልጉ ልየታ ተደርጓል፡፡ ከሚደገፉበት አራት ፓኬጆች ማለትም ለካይዘን፣ ለኢንተርፕርነር፣ ለክህሎትና ለቴክኖሎጂ ውስጥ በየትኛውና መቼ እንደሚደገፉ የመለየት ስራ ተሰርቷል። የድጋፍ ስራው ጥቅምት ወር ላይ የሚጀመር ሲሆን እስከ ታህሳስ የሚቆይ ይሆናል፡፡ ሁለተኛው ዙር ስልጠና የሚሰጥበት ጊዜ ደግሞ ከጥር እስከ መጋቢት ድረስ ነው፡፡ ሶስተኛው የስልጠና ጊዜ ከሚያዝያ እስከ ሰኔ ድረስ ነው፡፡ ስልጠና የሚሰጥበት የጊዜ ድልድል የኢንተርፕራይዞችን ጊዜ በቆጠበ፣ ስራ የማይበዛባቸውንና የሚመቻቸውን ጊዜ ባገናዘበና በተጠና መልኩ ነው ብለዋል፡፡

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ የዜጎችን ህይወት መለወጡን አጠናክሮ እንዲቀጥል፣ ለሀገር ኢኮኖሚ ማደግም ሁነኛ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት በማድረግ ረገድ ከሚመለከታቸው ብዙ እንደሚጠበቅ ያነጋገርናቸው የኮሌጁ አመራሮች መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

## ስለ ካይዘን ምን ያህል ያውቃሉ ?

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የስራ ዕድል ለመፍጠሪያና ወደ ኢንዱስትሪ ለሚደረገው ሽግግር ወሳኝ የሆኑ ተቋማት ናቸው፡፡ እነዚህ ተቋማት ተወዳዳሪና ምርታማ እንዲሆኑ የተለያዩ ዓይነት ድጋፎች ያስፈልጓቸዋል፡፡ ከእነዚህ ድጋፎች መካከል ካይዘን አንዱ ነው፡፡ ካይዘንን መተግበር የኢንተርፕራይዞችን ምርትና ምርታማነት ለማሳደግ ከሚያስችሉ መንገዶች መካከል አንዱ ነው፡፡

**የካይዘን 5ቱ "ማ" ዎች**

- **ማጣራት፡-** በስራ ቦታ የሚገኙ አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በማስወገድ በወቅቱ ለሚከናወኑ ተግባራት አስፈላጊ የሆኑ እቃዎችን ብቻ የማስቀረት ዘዴ ነው፡፡
- **ማስቀመጥ፡-** የምንገለገልባቸውን እቃዎች፣ ግብአት ብሎም ማሽኖች ለስራ ፍሰት አመቺነት እንደተፈላጊነታቸው በቅርብ፣ በግልፅ፣ በቀላሉ ለማግኘት፣ ለመጠቀምና በቦታው ለመመለስ በሚያስችል ሁኔታ የማደራጀት ዘዴ ነው፡፡
- **ማፅዳት፡-** የስራ ቦታችንንና የስራ መገልገያ መሳሪያዎችን ፅዱ ማድረግ ማለት ነው፡፡
- **ማላመድ፡-** በሁሉም የስራ ቦታዎች ላይ ስራን ማዕከል ያደረጉ ህጎች ማውጣትና መከተል ማለት ነው፡፡
- **ማዝለቅ፡-** የ5ቱ "ማ"ዎችን አሰራር እና ደንብ ማዘጋጀት፣ ለደንቡ በመገዛት፣ በሁሉም ሰራተኛ በቀጣይነት በስራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥና ድርጅታዊ የአሰራር ባህል ማድረግ ማለት ነው፡፡

ምንጭ፡- www.invensislearning.com እና በሃረማያ ዩኒቨርሲቲ የተዘጋጀ ጽሑፍ

# “ቤቴ ቀን ወጥቶለት አምሮ እንደ አዲስ ተሞሽሯል”

**ቤታቸው የታደሰላቸው ወ/ሮ ዝናሽ ቸኮል**

- **በክረምቱ መርሃ ግብር 3 ሺህ 154 የሚሆኑ መኖሪያ ቤቶችን ገንብቶ ማጠናቀቅ ተችሏል**

**በሄለን ጥላሁን**

የ75 ዓመቷ አረጋዊት ወ/ሮ ዝናሽ ቸኮል የ2018 አዲስ ዓመትን በታደሰ ቤት ከተቀበሉት መካከል ናቸው፡፡ ታድሶ አዲስ ውበት፣ አዲስ ገፅታ፣ አዲስ መንፈስ በፈጠረባቸው ቤታቸው በገቡበት ወቅት ተገኝተን ደስታቸውን ተጋራን፡፡

እኚህ አረጋዊት በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 በተለምዶ ግንፍሌ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ለሠላሳ ሦስት ዓመታት ኖረዋል፡፡ ከሦስት አስርት ዓመታት በተሻገረ ዕድሜ በኖሩበት በዚህ አካባቢ በርካታ ውጣ ውረዶችን ማስተናገዳቸውን አልሸሸጉም፡፡

“ህይወት መልኳን ያዞረችብኝ ባለቤቴን በሞት ባጣሁበት ሰዓት ነበር። የሞላ እና የሞቀ ትዳር ውስጥ እኖር ነበር፡፡ ይህ አስከፊ አጋጣሚ ከተከሰተ ሃያ አምስት ዓመት አልፎታል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ምንም የተረጋጋ ሕይወት አልነበረኝም፡፡ አራስ ልጄን በአንድ እጄ ይዤ ጡት ሳጠባ፣ በሌላኛው እጄ ደግሞ እንባዬን እያበስኩ ነበር ኑሮዬን ስገፋ የቆየሁት፡፡ ‘በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ’ እንደሚባለው፤ የክረምቱ ዝናብ፣ የበጋው ፀሐይ የተፈራረቀባት ደሳሳዋ ጎጆዬ በላዬ ላይ መፍረስ ጀምራ ነበር፡፡” በማለት ያለፉበትን አስከፊ ጊዜ ይተርካሉ፡፡

ባለቤታቸውን ካጡ በኋላ፣ አራስ ልጃቸውን ብቻቸውን ሰው ቤት ልብስ በማጠብ፣ እንጀራ በመጋገር እንዲሁም ደግሞ አሻሮ በመቁላት ያሳደጉት እኚህ አረጋዊት፤ የደሳሳ ቤት ኑሮአቸውን አስከፊ ያደረገባቸው ዝናብና ሐሩሩ ብቻ አልነበረም፡፡ የተለያዩ ነፍሳት እንዲሁም አይጦች እንዳሻቸው ገብተው የሚወጡበት ቀዳዳ በመብዛቱ፣ እረፍት አልባ ሌሊቶችን እንዲያሳልፉ ምክንያት ሆኗቸዋል፡፡

“የህዳሴ ግድባችን ከዳር ደርሶ መላ ኢትዮጵያውያንን እንዳስደሰተው ሁሉ፤ የእኔም ቤት ቀን ወጥቶለት አምሮ እንደ አዲስ ተሞሽሯል፡፡ በአዲሱ ቤቴ ውስጥ አዲስ ሶፋ፣ ወንበሮች፣ ጠረጴዛ እና አልጋ ተሟልቶልኛል፡፡ ዓመትንም በአዲስ መንፈስ ተቀብያለሁ፡፡ ያለው ለሌለው ሲረዳ ጎዶሏችን ይሸፈናል” ሲሉ የተሰማቸውን ደስታ እንባ በተቀላቀለ ሁኔታ ገልፀዋል፡፡

በክረምቱ ወቅት እንደወይዘሮ ዝናሽ ቸኮል ላሉ በቁጥር 13 ለሚሆኑ የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 7 አስተዳደር አቅመ ደካማና አረጋዊያን ነዋሪዎች ቤታቸው ታድሶላቸዋል፡፡ ይህንን ሥራ አስመልክቶ ማብራሪያ የሰጡት በወረዳው የህብረተሰብ ተሳትፎ እና በጎ ፍቃድ ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ሃላፊ አቶ ገረመው አዝመራው በአስተያየታቸው፤ “በክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት የበርካቶችን የአቅመ ደካሞች ቤት በማደስ፣ የትራፊክ አገልግሎት በመስጠት፣ የሰላም ዘብ በመሆን፣ የደም ልገሳ፣ የማጠናከሪያ ትምህርት በመስጠት እና መሰል አገልግሎቶችን በጎ ፍቃደኞችን በማሳተፍ ሲሠራ ቆይቷል፡፡ የአቅመ ደካሞችን ቤት እድሳት ለማድረግ በወረዳው ውስጥ የከፋ ችግር ያለባቸውን እንደየክብደቱ ቅድሚያ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡” ብለዋል፡፡



ፎቶ- በገነት ወንድሙ

ወ/ሮ ዝናሽ ቸኮል በታደሰላቸው ቤት ውስጥ

ነዋሪነታቸውን በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ወረዳ 5 በተለምዶ አበበ ቢቂላ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ ያደረጉት አቶ አንተነህ ተስፋዬ፤ ባሳለፍነው ጷጉሜን ላይ ነበር አዲስ ቤታቸውን ተረክበው አዲስ ዓመትን የተቀበሉት፡፡ ከስምንት ዓመት በፊት በደረሰባቸው የመኪና አደጋ ህልማቸው ጨልሞ፤ በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆነው ቀናትን፣ ወራትንና ዓመታትን በመቁጠር ላይ ሳሉ ነበር የበጎ ፈቃደኝነት በጎ ተግባር የደረሰላቸው፡፡

ወድቆ መነሳት ያለ መሆኑን በማመን ጎጇቸውን ለማቅናት አቅማቸው የፈቀደውን ስራ ብቻ በመከውን የእለት ጉርሳቸውን ለማሟላት ጥረት ቢያደርጉም፣ ህልማቸውና አኗኗራቸው ሊጣጣም ያልቻለው አቶ አንተነህ፤ ከእርሳቸው አልፎ በቤተሰቦቻቸው ላይ ተፅዕኖ መፈጠሩ አልቀረም፡፡ ሁለቱን ልጆቻቸውን ለማስተማር ችግር ገጥሟቸው እንደነበር ያስታውሳሉ። የኑሮ ውጣ ውረድ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጫናቸው ሲመጣ፤ በእርጅና ምክንያት እየተጎሳቆለ የመጣውን መኖሪያ ቤታቸውን ማደስ አልቻሉም። ጎርፍ ለሚያስገባው መኖሪያቸው መላ ለማበጀት ተቸግረው ባሉበት ወቅት ለመፍትሄ በራቸውን ያንኳኳው የበጎ ፍቃደኞች በጎ እጅ እንደማለዳ ፀሐይ ቀሪ ዘመናቸውን ሊያበራ እንደመጣ ተዓምር ይመስሉታል፡፡

እንደ አቶ አንተነህ ገለፃ፤ በክረምት ወራት የሚዘንበው ዝናብ የቤታቸውን መሰረት ከማዛባት ባሻገር እርጥበቱ የኤሌክትሪክ አደጋ መፈጠር ምክንያት ጭምር ሆኗል፡፡ በተለይ ካለማቋረጥ አምፖሉ ብልጭ ብልጭ ሲል ከአሁን አሁን እኔና ቤተሰቤ አለቅን በማለት የሰቀቃ ህይወትን እንመራ ነበር፡፡ ባለሁለት ክፍል ቤታቸው በተዋበ በርና መስኮት ስርዓቱን በጠበቀ አግባብ ተሰትሮ ሲያዩት በደስታ እንዳነቡ ገልፀዋል፡፡ በተለይ እነዚያ ለመውጣትና ለመግባት አስቸጋሪ የነበሩ በሮች ከማዘንበላቸው ባለፈ ከዛሬ ነገ ይወድቁ ይሆን ብለው ይሰጉ ነበር፡፡ አሁን ግን ቀኑን ቀን፤ ሌሊቱን ሌሊት አስመስሎ ድምቀትን የቸራቸው መኖሪያ ቤታቸው ትልቅ የህይወት ተስፋን እንዲያገኙ አግዟቸዋል፡፡

“በተስፋ መኖር እድሜ እንዲቀጥል ያደርጋል” የሚሉት አቶ አንተነህ፤ “ቀድሞ በነበረው ቤት ውስጥ አይደለም ብሩህ ተስፋን ይቅርና ለደቂቃ እንኳን ቤት ውስጥ ሳሳልፍ ድባቴ እና ጭንቀት ነበር የሚሰማኝ፡፡ አሁን ግር ብሩህና የማያቋርጥ ሰላም ባለበት ቤት ውስጥ በመገኘቴ ቀጣዩ የህይወት ዘመኔ የተሻለ እንዲሆን ያደርገኛል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ሠው ተኮር የልማት መርሃ ግብርን እያከናወነ ያለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር፤ ዘመናዊና ምቹ የመኖሪያ ቤቶችን ለነዋሪዎች የማቅረቡን ሥራ አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ በቅርቡም ከተማ አስተዳደሩ በሺዎች ለሚቆጠሩ ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት አስተላልፏል፡፡ ይህንን በተመለከተ በማህበራዊ የትስስር ገፃቸው ላይ ሃሳባቸውን ያስተላለፉት የአዲስ አበባ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፤ “በክረምት በጎ ፈቃድ አገልግሎት ያስገነባናቸውን 1 ሺህ 671 ያህል ቤቶች ለሀገር ባለውለታዎች፣ ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለከፋ ማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ፣ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ እና በወንዝ ዳርቻዎች ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች አስረክበናል” ብለዋል፡፡ አያይዘውም፤ በዚህ ተግባር ውስጥ ካላቸው ያለ ስስት ሰጥተው ከከተማ አስተዳደሩ ጎን ለነበሩ ባለሀብቶች ምስጋናቸውን አቅርበዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረተሰብ ተሳትፎና በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር ወይዘሮ አስራት ንጉሴ ለዝግጅት ክፍላችን በሰጡት ማብራሪያ፣ የክረምቱ መርሃ ግብር እስከ መስከረም 30 ድረስ ይቀጥላል፡፡ በ15 ዋና ዋና መርሃ ግብሮች እና 19 ንዑሳን መርሃ ግብሮችን በመያዝ ነበር ወደ ተግባር የተገባው፡፡ የቤት እድሳትን በተመለከተ በክረምቱ መርሃ ግብር 2 ሺህ 500 መኖሪያ ቤቶችን ለመገንባት የታቀደ ሲሆን ወደ 3 ሺህ 154 የሚሆኑትን ገንብቶ ማጠናቀቅ ተችሏል፡፡ ቁጥራቸው ከ500 ሺህ በላይ ለሚሆኑት ማዕድ ለማጋራት ታቅዶ ከ600 ሺህ በላይ ለሚሆኑት ማጋራት ስለመቻሉ ገልፀዋል፡፡

ነፃ ህክምናን በተመለከተ እንዲሁ ቁጥራቸው ከ125 ሺህ በላይ ዜጎችን ተደራሽ ለማድረግ ታቅዶ 207 ሺህ በላይ የሚሆኑትን መድረስ ተችሏል፡፡ ይህ ሁሉ ሊሰራ የቻለው የመንግስት ብሎም የግል የህክምና ተቋማትን በማሳተፍ ጭምር ነው፡፡ በደም ልገሳ መርሃ ግብር እንዲሁ 40 ሺህ ዩኒት ደም ለመሰብሰብ ታቅዶ ከ41 ሺህ ዩኒት በላይ ደም ከበጎ ፍቃደኞች እንዲሁም ከከተማዋ ነዋሪዎች ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡ ቁጥራቸው 65 ሺህ የሚሆኑ ተማሪዎችን በክረምት መርሃ ግብር የማጠናከሪያ ትምህርት ለመስጠት ታቅዶ ለ68 ሺህ 107 ለሚሆኑ ተማሪዎች በበጎ ፍቃደኛ መምህራን ትምህርቱ ተሰጥቷል፡፡ ሌሎችም አገልግሎቶች ከእቅድ በላይ ለማሳካት ስለመቻሉ ተናግረዋል፡፡

እንደ ምክትል ኮሚሽነሯ ገለጻ፣ በክረምቱ መርሃ ግብር እስከ መስከረም 6 ቀን 2018 ዓ.ም ድረስ ቁጥራቸው ከ2 ነጥብ 2 ሚሊዮን በላይ በጎ ፍቃደኞች በድግግሞሽ በሁሉም መርሃ ግብሮች ላይ ተሳትፈዋል፡፡ የከተማዋን እድገትና ልማት በማፋጠን የነዋሪውን ኢኮኖሚያዊ እና ማህባራዊ ችግሮች ለመፍታት በሚደረገው ጥረት ውስጥ በጎ ፍቃደኞች የቀኝ እጅ ስለመሆናቸው ወ/ሮ አስራት የገለፁ ሲሆን በተሰራው ስራ 5 ነጥብ 9 ቢሊየን በላይ የመንግስት ወጪን ለማዳን ተችሏል፡፡

በበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሚከወኑ ተግባራት የማህበረሰባችንን የመረዳዳትና የእርስ በእርስ ግንኙነታችንን አጠናክሯል። አቅመ ደካሞች፣ አረጋውያንና አካል ጉዳተኞች ማህበራዊ ተሳትፏቸውና ተጠቃሚነታቸው ማሳደግ፣ በጥሩ ስብዕና የታነፁ ወጣቶችን ማፍራት ተችሏል። በመንግስት ይሸፈን የነበረውን ወጪ በማዳን ወደ ሌሎች ልማታዊ አጀንዳዎች ማስፈጸሚያነት እንዲውል አስቻይ ሁኔታዎች ስለመመቻቸቱ ጭምር ምክትል ኮሚሽነሯ አስረድተዋል፡፡

የዓድዋ ድል መታሰቢያ
ADWA VICTORY MEMORIAL

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል አደረሳችሁ





የዓድዋ ድል መታሰቢያ የፓን አፍሪካኒዝም ህያዉ ምልክት እና የመላው የኢትዮጵያ ህዝቦች ድል የሆነውን የዓድዋ ድል ታሪክን የሚዘክሩ ታሪካዊና ባህላዊ ቅርሶችን በማሰባሰብና በክብር በማኖር ለትውልድ ማሳወቅ እና ማስተላለፍ እንዲሁም ለጎብኝዎች በማሳየት ለሀገር ገፅታ ግንባታ አስተዋፅኦ ማበርከት፤ ጎብኚዎችም የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ታሪካቸውን እንዲያውቁ በማድረግ እውቀትን የሚያጎለብቱበትና መረጃ የሚያገኙበት ማዕከል በማድረግ በታሪኩ የሚኮራ ትውልድ ማፍራት ዋነኛ ዓላማዉ ነዉ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የዓድዋ ድል ታሪካዊ መረጃዎች እና ቅርሶችን በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣ በመንከባከብና በመጠበቅ ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለማገናዘቢያ አገልግሎት ማቅረብ የቱሪስት መዳረሻ ማድረግ እንዲሁም የነገ ሀገር ተረካቢ ትውልድን ለመቅረጽና ለማስተማሪያነት የሚያገለግል የህጻናት ቤተ-መጻሐፍትን በማደራጀት ላይ ያለ ተቋም ነው፡፡

በራሴና በዓድዋ ድል መታሰቢያ ማኔጅመንትና ሠራተኞች ስም ለመላው ኢትዮጵያዉያን በሙሉ መልካም በዓል እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ!

**አቶ ግሩም ግርማ**
**የዓድዋ ድል መታሰቢያ ዋና ዳይሬክተር**



## እንኳን ለመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን እንኳን የአንድነታችን መገለጫ፣ የላብና የደም ጠብታ ውጤት ዳግማዊ አድዋ በሆነው የታላቁ የህዳሴ ግድብ ምርቃት እና በድላችን ማግስት ለሚከበረው የመስቀል ደመራ በዓል አደረሳችሁ አደረሰን እያለ የመስቀል እና ደመራ በዓል በሀገራችን በልዩ ድምቀት ከሚከበሩ በዓላት መካከል አንዱ በመሆኑ በበዓሉ የተራራቁ ቤተሰቦች የሚገናኙበት የአንድነት፣ የፍቅር፣ የይቅርታ፣ የአብሮነት፣ የምስጋና እና የተስፋ እሴቶች የሚገለጹበት በመሆኑ የእንኳን አደረሳችሁ ምኞቱን ይገልፃል:: ባለስልጣኑ አዲስ አበባን እንደ ስሟ አዲስና ውብ ለማድረግ በህብረተሰቡ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎ የደንብ መተላለፎች እና ተያያዥ ህገ-ወጥ ተግባራትን በመከላከልና በመቆጣጠር ከተማችንን ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ማራኪና ሰላማዊ እንድትሆን የማድረግ ስራዎችን አጠናክሮ እየሰራ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ከተማችንን አዲስ አበባን የአፍሪካ ተምሳሌት የማድረግ ራዕይ እውን እንዲሆን እየተሰሩ ያሉ የኮሪደር ልማት ስራዎችን እና የወንዝ ዳርቻ ብክለት የመከላከልና የማልማት ስራዎች ለትውልድ ተሻጋሪ ለማድረግ ሚናውን በመወጣት ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም መስከረም 16 እና 17 ቀን የሚከበረውን የደመራ እና መስቀል በዓል ስናከብር ከተማችንን ከህገ-ወጥ የእንስሳት እርድ በመከላከል እና በመቆጣጠር ህብረተሰቡ ጤንነቱ የተረጋገጠ እርድ እንዲያከናውን እና ህገ-ወጥ እርዶች ሲከናወኑም በነፃ ስልክ ቁጥር 9995 ጥቆማ እንዲሰጥ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

## መልካም በዓል!

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ ማስከበር ባለስልጣን**





እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሠላም አደረሳችሁ የሚለው የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት በዓሉ የሠላም፣ የጤና እና የብልጽግና እንዲሆን ያለውን ልባዊ ምኞት እየገለፀ በአሁኑ ወቅት 111 የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳዎች ውስጥ ተደራጅተው ለህብረተሰቡ በአቅራቢያው የዳኝነት አገልግሎት በመሥጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀጽ 50(5) እና በአዋጅ ቁጥር 31/99 አንቀጽ 5 መሰረት የአዲስ አበባ የወረዳ ማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ግምታቸው ከብር 5,000 (አምስት ሺህ) ያልበለጡ የንብረትና የገንዘብ ክርክሮችን የመዳኘት የፍትሐ-ብሄር ስልጣን ያለው ሲሆን በተጨማሪም በደንብ ቁጥር 150/2015፣ ደንብ ቁጥር 167/2016 እና 180/2017 መሰረት የሚቀርቡለትን የደንብ መተላለፍ ጉዳዮች መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

ነገር ግን ፍርድ ቤቶቹ ያላቸው የፍትሐ-ብሔር የዳኝነት ሥልጣን በጣም ውስን መሆኑ አሁን ካለው የተሻለ አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዳይሰጡ አድርጓቸውል፡፡ ከስልጣን ማነሱ ጋር በተያያዘ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለፍ/ቤቶቹ የሚቀርቡ አቤቱታዎች እየቀነሱ መጥተዋል፡፡ ስለሆነም የማ/ፍ/ቤት ስረ ነገር ስልጣን ኢንዲሻሻል ጉባዔ ጽ/ቤቱ መቋቋሚያ አዋጁን ለማሻሻል አበክሮ እየሠራ ይገኛል፡፡ በዚህ አጋጣሚ ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ህብረተሰቡ በመኖሪያ አካባቢው የዳኝነት አገልግሎት የማግኘት መብቱ እውን እንዲሆን አፋጣኝ መፍትሔ እንዲሰጡን ከአደራ ጋር በአክብሮት እንጠይቃለን፡፡

# መልካም በዓል

**አቶ ገ/እግዚሐብሄር ገ/ማሪያም የአዲስ አበባ ከተማ የማህበራዊ ፍርድ ቤቶች ዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ጽ/ቤት ፕሬዝዳንት**



**የሱፍ ኢብራሂም ሸፋው**
**የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን ዋና ስራ አስኪያጅ**

# በአዲስ አበባ ከተማ የመንግስት ንብረት አስተዳደር ባለስልጣን

ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ። በዓሉ የሰላም፣ የጤና እና የአብሮነት እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቱን ይገልጻል።

ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የመንግስትን ንብረት ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል፤ ከብልሹ አሰራር እና ብክነት በመከላከል ረገድ አይተኬ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል። በመንግስት ተቋማት ያለ አግባብ በትርፍነት የተያዙ ንብረቶችን አገልግሎት ሊሰጡ ወደሚችሉበት የመንግስት ተቋም በማስተላለፍ እና አገልግሎት የማይሰጡትን በማስወገድ፤ በቀላል ጥገና አገልግሎት መስጠት የሚችሉትን በራስ አቅም ጠግኖ ወደ አገልግሎት በማስገባት የከተማ አስተዳደሩን ከተጨማሪ ወጪ እና ኪሳራ የመጠበቅ ተግባር እያከናወነ ይገኛል፡፡

በህንፃው ዘርፍ በኩል በኪራይ አገልግሎት የሚሰጡ የከተማ አስተዳደሩ የመንግስት ተቋማትን ፍትሐዊ የቢሮ ድልድል በመስራት፤ የመንግስት ህንፃ ማስፋፊያዎችን በማከናወን፤ የጥገናና የእድሳት ስራዎችን በመስራት፤ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላትን በማሟላት ለአገልጋይና ተገልጋይ ምቹ የስራ አካባቢን በመፍጠር በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ ለውጥ እንዲመጣ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል።

ለባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ራዕይ እና ተልዕኮ መሳካት የከተማችን ነዋሪዎችና የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ለምታበረክቱት አስተዋፅኦ እያመሰገነን በዓሉ የሰላም፣ የፍቅር እና የአብሮነት እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቱን ይገልፃል።







## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል በዓል በሰላም በጤና አደረሳችሁ! አደረሰን !

እንደ ክፍለ ከተማ የሰራናቸው ስራዎች መስራት የነበረብንን ሳይሆን፤ መስራት የቻልነውን ነበር፤ ይሄ የሆነው በነበረብን የአቅም ውስንነት እንጂ የእኛ መሻት አልነበረም፡፡ የቻልነውን ሰርተን የእኛን ድጋፍ ከሚፈልጉት ከብዙ በጥቂቱ ለመድረስ ሞክረናል፡፡ ከችግሩ ስፋት አንፃር ብዙ ስራዎች ከፊታችን ይጠብቁናል፡፡ ከትላንት ያካበትነውን ልምድ ቀምረን ከሁኔታዎች ጋራ አዋህደን ስራዎችን በፍጥነት ሌት ተቀን ለመስራት ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅብናል፤ ምክንያቱም ዛሬም እንደ ትላንቱ አያሌ ዜጎቻችን የእኛን ድጋፍ የሚሹ በመኖራቸው፡፡

በዓሉ አንድነታችንን በማስጠበቅ የልዩነት መንገዶችን በመዝጋት ከፊታችን የተደቀኑብንን ችግሮች ለመቅረፍ በትጋት መስራት ከሁሉም የክፍለ ከተማው ነዋሪ ይጠበቃል፡፡ በአዲሱ ዓመት ካሳለፍነው በተሻለ በሁሉም ዘርፍ የተሻሉ ውጤቶችን ለማስመዝገብ የክፍለ ከተማው አስተዳደር እንደ ትላንትናው ዛሬም ቁርጠኛ ነው፡፡ የእኛ ቁርጠኝነት ካለ የማህበረሰባችን እገዛ ከዳር እንደሚደርስ በብዙ እንገነዘባለን፡፡ በመሆኑም በክፍለ ከተማችን የሚፈለገው ለውጥ እውን እንዲሆን አጠቃላይ አመራሩ፣ የመንግስት ሰራተኛው እና ነዋሪዎቻችን የተሻለች ነገን ዛሬ እንድንሰራ ከጎናችን እንድትቆሙ ጥሪዬን እያስተላለፍኩ፤ ሁሉም የክፍለ ከተማ እና የከተማችን ነዋሪዎች እንኳን ለ2018 የመስቀል በዓል አደረሳችሁ፡፡ ብርሃነ መስቀሉ የሰላም፣ የደስታ፤ የፍቅር እና በምንሰማራበት የስራ መስክ ሁሉ ውጤታማ የምንሆንበት እንዲሆን መልካም ምኞቴን እገልፃለሁ፡፡

**መልካም በዓል!**

**አቶ ታረቀኝ ወርቅነህ**
**የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ዋና ስራ አስፈፃሚ**



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ
BUREAU OF JUSTICE

## እንኳን ለ2018 ዓ.ም የመስቀል ደመራ በዓል በሰላም፣ በጤና አደረሳችሁ አደረሰን!

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች የህግ ማዕቀፎችን በማዘጋጀትና በማሻሻል፣ የጸደቁትን በተለያየ መንገድ ተደራሽ ማድረግ እንዲሁም በሕግ ጉዳዮች የከተማው አስተዳደር ዋና አማካሪና ተወካይ በመሆን የህዝብና የመንግስት መብትና ጥቅም ማስከበር ነው፡፡

ቢሮው የሕዝብና የመንግስት የጋራ ሀብት ላልተገባ አካል ተላልፎ እንዳይሰጥ፣ መልካም አስተዳደር የተረጋገጠባት፣ ፍትሕ የሰፈነባት እና የሕግ የበላይነት እውን የሆነባት አዲስ አበባ በዘላቂነት ለመገንባት በአዲሱ ዓመትም በፍትህ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽንና በመደበኛ እቅድ በልዩ ተነሳሽነት ርብርብ የሚሰራ ሲሆን ለስኬታማነቱ መላው ነዋሪ ከጎናችን በመሆን የድርሻውን እንዲወጣ በዚህ አጋጣሚ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

**በድጋሚ መልካም የመስቀል ደመራ በዓል እንዲሆን እንመኛለን!**
**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍትህ ቢሮ!**


ሕብረት ባንክ
በሕብረት እንደግ!
እንኳን ለብርሃነ
መስቀሉ
በሰላም አደረሳችሁ
FOLLOW US
hibretbank.com.et


እንኳን ለ2018 ዓ.ም
የመስቀል በዓል አደረሳችሁ!
የአዲስ አበባ ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ በሠላም አደረሳችሁ እያለ፤ ተገልጋዮች የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 88 እና በደንብ ቁጥር 105/2011 አንቀጽ 6 በተደነገገው መሠረት አስፈላጊዉን ቅድመ ሁኔታዎች በማሟላት አቤቱታቸውን ሲያቀርቡ ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ተግቶ የሚሠራ መሆኑን በደስታ ይገልፃል።
መልካም በዓል!
አቶ ታረቀኝ አስፋው የታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ፕሬዝዳንት

## ከህዳሴ ... ከገጽ 12 የዞረ

ይኸንኑ ሀሳብ የሚያጠናክር አስተያየት ሰጥተዋል።

የስነ ልቦና ባለሙያ የሆኑት ልዑልሰገድ በየነ (ዶክተር) እንደገለጹት፤ ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ለምርቃት እስኪበቃ ድረስ ያለፈበት ውጣ ውረድ ሰዎች ለሚኖሩት የዕለት ተዕለት ኑሮ ብዙ የሚሰጠው ትምህርት እንዳለ ያብራራሉ። ማንኛውም ሰው እቅድ አቅዶ ወደ ስራ ሲገባ ሊያሳካው የሚችለው መሆኑን፤ ሊያውቀውና ሊረዳው ይገባል፡ ፡ ይህ ካልሆነ የተፈጠረው ለቁጥር እንጂ ለስኬትና ለልማት አይደለም ወደሚል ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ይገባል፡፡

ህልም እንዲሳካ ከሚያደርጉ መሳሪያዎች ውስጥ የመጀመሪያው አንድ ሰው ሊያሳካ ያሰበውን ነገር ወደ ውስጡ ዘልቆ መግባቱን እና ለራሱ፣ ለቤተሰቡና ለሀገሩ ጠቃሚ መሆኑን ማረጋገጥ፣ እቅዶቹ ችግሮች ቢገጥሙት እንኳን መቋቋም የሚችል ህልም ያለው መሆን እንዲሁም ከጥሪው እና ከጥንካሬው ጋር የሚስማማ ማድረግ እንደሚገባው ይናገራሉ፡፡

ባለሙያው በማብራሪያቸው፣ “እቅዳችንን አቅደን ወደ ህልማችን ለመድረስ ስንነሳ እንዳይሳካ የሚያደርጉ የተለያዩ ውጣ ውረዶችና ተግዳሮቶች ማጋጠሙን ልንወደው ይገባል፡፡ አዋጭ ናቸው። ለእኛ ተግዳሮቶች ቢመስሉንም እንድናሳካ የሚረዱን ሽልማቶች ናቸው። ምክንያቱም ዋጋ ካልከፈልን ሽልማት አናገኝምና” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የሰው ልጅ ማሳካት የማይችለው ነገር እንደሌለ ማሳያ የሆነውንና በብዙ ውጣ ውረድ ያለፈውን ታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ያነሱት የስነ ልቦና ባለሙያው፤ አንዳንድ ኢትዮጵያውያንም ሆኑ የዓለም ሀገራት እንደማይሳካ ተስማምተውበት የነበረ ቢሆንም በኢትዮጵያ መንግስትና ህዝብ ትብብር እውን ሆኖ ተመርቋል፡፡

ለዚህ ዋነኛ ምክንያቱ ያሉትን ምሁሩ ሲያብራሩ፣ “የኢትዮጵያ ህዝብ ወደራሱ ተመልሶ፣ ይሳካል ብሎ ማመኑ እና ለሀገራችን ብሎም ለአፍሪካ ይጠቅማል የሚል ርዕይ መሰነቁ ነው፡፡ ይህም ማንኛውም ልናሳካው የፈለግነው እቅድ ከአቅማችን በታች እንጂ በላይ እንዳልሆነ ያረጋገጥንበት ነው” ብለዋል፡፡

እንደ ባለሙያው ገለጻ፣ የግድብ ግንባታውን ስንጀምር ከርዕይ ጀምረን ተግዳሮቶችን እንደ መወጣጫ መሰላል በመጠቀም “ካላጠናቀቅን አንቆምም” የሚል ቁርጠኛ አቋም የያዝን አመራሮችና ኢትዮጵያውያን ስለነበርን አሳክተን በተግባር አሳይተናል፡፡ በግድቡ የተለያየ የፖለቲካ አቋምና አመለካከት ያላቸው አካላት በአንድነት በመቆም ‘እንኳን ደስ አለን’ እያሉ ደስታቸውን ሲገልፁም ታይተዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ግድቡ ሃይልን ብቻም ሳይሆን መስማማትንም፣ አንድነትን፣ ማሳካት መቻልንም ጭምር ማመንጨት መቻሉን ነው፡፡

ይህን ትልቅ የህዳሴ ግድብ ስኬት ወደ እያንዳንዱ ሰው ህይወት በማምጣት ያለፈበት ውጣ ውረድና ስኬት የግል ህዳሴን መገንባት የሚያስችል መሆኑን የገለፁት ልዑልሰገድ (ዶ/ር)፣. ይህም ሲባል ግብ አስቀምጠን፣ ጠንካራ ጎናችንንና ጥሪያችንን እንደ መሳሪያ በመጠቀም፣ ደካማ ጎናችንን በማወቅ፣ ስልታዊ አብሮ መስራትን መጠቀም ህልምን ማሳካትና ወደፈለጉበት ደረጃ እንዲደርሱ ያደርጋል፡፡

የህዳሴው ግድብ ውጣ ውረዶችን አልፎ ለመመረቅና ጥቅም ላይ ለመዋል እንደበቃው ሁሉ፤ የሰው ልጆችም ለሚኖሩት የግል ህይወት ውጣ ውረዶች ሊያጋጥሙት እንደሚችሉ እና ተግዳሮቶችን እንደ መሰላል በመጠቀም እንደሚያሳኩት ማሳያ መሆኑን ነው የስነ ልቦና ባለሙያው የተናገሩት፡፡

## የአዲስ ... ከገጽ 22 የዞረ

ወደ ማዕከሉ እንደገባችም የጤና ምርመራ ተደርጎላት፣ ለአንድ ወር ያህል የህይወት ክህሎት ስልጠና ወስዳ ከነበረችበት የሱስ ህይወት እንደወጣች የምትገልፀው ሃሴት፤ የምትፈልገውን የምግብ ዝግጅት ሙያ መርጣ ለአራት ወር እንደሰለጠነች ነግራናለች፡፡

ወጣት ሃሴት የህይወት ክህሎት ስልጠና ማግኘቷ ለራሷ ያላት አመለካከት ከፍ እንዲል፣ ትልቅ ሰው እንደሆነች እንድትረዳ እና እንድታውቅ እንዳስቻላትና በደረጃ 1 በሰለጠነችው የምግብ ዝግጅት ሙያም በተመረቀች ማግስት “አኮ ኮፊ” የስራ ዕድል ተፈጥሮላት መቀጠሯን አብራርታለች፡፡

“አዲሱ ዓመት ብዙ ፈተናዎችና ስቃይ ያሳለፍነው የእኔ እና መሰል እህቶቼ ዓመት ነው” የምትለው ሃሴት፤ በዚህ ማዕከል ገብታ ስልጠና መውሰዷ የትናንት ማንነቷን እንዳታስታውስ፣ ወደ ፊት እንድትራመድ፣ አላማ እንዲኖራትና ትልቅ ነገር እንድትመኝ በር እንደከፈተላት ትገልፃለች፡፡

ትልቅ የምግብ ባለሙያ መሆን፣ በስሟ ትልቅ ሆቴል መክፈት እና በለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል የበጎ አድራጎት ስራ እየሰራች መኖር የወደፊት ህልሟ እንደሆነ ገልፃ፤ ማንነቷ እንዲቀየርና ካልተመቻቸ ህይወት ውስጥ እንድትወጣ ያደረጓትን የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤን አመስግናለች፡፡

የለነገዋ የሴቶች ተሃድሶ እና ክህሎት ማበልፀጊያ ማዕከል የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግዳሮቶች የተጋለጡ ሴቶችን ህይወት ለመታደግ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተቋቋመ ሲሆን፣ ከሥነ ልቦና ድጋፍ እና የጤና ክብካቤ ጀምሮ ሙያዊ ስልጠናዎችን ይሰጣል፡፡ እንዲሁም የስራ ዕድል በማመቻቸት እንዲህ አይነት የሕይወት ፈተና እያሳለፉ ያሉ ዜጎች ራሳቸውን እንዲችሉ ከማድረግ ባለፈ ለሀገርና ወገን የሚጠቅሙ እንዲሆን ይደግፋል።

በቅርቡም ማዕከሉ በሶስተኛ ዙር በተለያዩ የሙያ መስኮች ያሰለጠናቸውን 810 ሰልጣኞችን አስመርቋል፡፡ በዕለቱ ንግግር ያደረጉት ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ፣ “ያለ ጥፋታቸው፣ ማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ችግር የተሸከሙ፣ ለብዙ ማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡና በዚህም ምክንያት እንደ ጥፋተኛ የሚወቀሱ ሴት እህቶችን ህይወት ለመቀየርና ለማሻሻል እንደሚሰራ ስራ አስደሳች የለም፡፡ የእነሱን ህይወት መቀየር ከሰራናቸው ፕሮጀክቶች ሁሉ ይበልጥብናል” ሲሉ ተናግረዋል፡፡ ሴቶች ለተለያዩ ማህበራዊ ችግሮች የመጋለጣቸው ዋነኛ ምክንያት ድህነት እንደሆነና ይህንን ችግር ለማቃለል የከተማ አስተዳደሩ ከተለያዩ አካላት ጋር በመቀናጀት በትብብር እየሰራ እንደሚገኝም አክለው ጠቁመዋል፡፡

ማዕከሉ በይፋ ከተከፈተ በኋላ በሶስት ዙሮች 1 ሺህ 692 ለተለያዩ ለማህበራዊ ችግሮች የተጋለጡ ሴቶችን በተለያየ ሙያ በማሰልጠን ወደ ስራ እንዲሰማሩ አድርጓል፡፡

## ሕይወት... ከገጽ 27 የዞረ

አድርጎ አኀዛ ገበያ ላይ ከቀበና ወንዝ ጋር ይገናኛል፡፡ ከሶስት ኪሎ ሜትር በላይ ርዝመትም አለው፡፡

ኢንጂነዬር እንዳሻው እንደሚገልፁት፣ የግንፍሌ ወንዝና ዳርቻ በርካታ ሰዎች የሰፈሩበት፣ መኖሪያ ቤቶች ዙሪያውን የሚገኙበት በመሆኑ የተጨናነቀ፣ ከወንዝነaት ይልቅ የቆሻሻ ማስወገጃ፤ ለመኖሪያነትም ሆነ ለእይታ የማይመችና ደስ የማይል አካባቢ ነበር፡፡ ማህበረሰቡም ክረምት በመጣ ቁጥር ለጎርፍ አደጋ ተጋላጭ የሚሆንበት ሁኔታም ነበር፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ አሰግደው ኃ/ጊዮርጊስ ከላይ የተነሳውን ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡ ግንፍሌ መሀል የከተማዋ እምብርት፤ የላይኛውን ቤተ መንግስት ጭምር ተጎራብቶ የሚገኝ ቢሆንም በወንዙ አካባቢ ለሚኖረውም ሆነ አጠቃላይ ለከተማው ህዝብ ጥቅም ሳይሰጥ ቆይቷል፡፡ ከመኖሪያ ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በሚለቀቅና የሚጣል ቆሻሻም ለከፍተኛ ብክለት በመዳረጉ ስነ ምህዳሩና ብዝሃ ሕይወት ሀብትነቱ ተመናምኗል፡፡ ምቹ የመኖሪያ አካባቢ ከመሆን ይልቅ ሰው ለማየት የሚጠየፈው፣ የቆሻሻ መጣያ፣ የጎርፍና የጤና ስጋት ምንጭ ሆኖ መቆየቱን ያነሳሉ፡፡

በብልፅግና ፓርቲ የአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ፅህፈት ቤት ኃላፊ እና የቀበና ወንዝ ዳርቻ የኮሪደር ልማት አስተባባሪ አቶ ሞገስ ባልቻ ሰሞኑን “ከተፈጥሮ ጋር እርቅ” በሚል ርዕስ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ በተላለፈው ጥናታዊ ፊልም (ዶክመንታሪ) ላይ እንደተናገሩት፣ በግንፍሌ ወንዝ ላይ የወንዝ ዳርቻ ልማት ከመጀመሩ በፊት ወንዙ ከመበከሉ የተነሳ የነበረው መልክ የተቃጠለ ናፍጣ የሚመስል፣ መጥፎ ጠረን ያለውና ለሰዎች ጤናና ለደህንነት ስጋት የሚጭር ነበር፡፡

ይህንን የወንዙን ሁኔታ ለመቀየር እና ምቹ የመኖሪያና የቱሪዝም መዳረሻ እንዲሆን ለማስቻል የከተማዋ አመራር ቁርጠኛ የሆነ አቋም በመያዝ ወደ ወንዝ ዳርቻ ልማት ገብቷል፡፡ የግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ ፅዱ፣ ውብና አረንጓዴ ገፅታን ተላብሶ መሰራቱን ያነሱት አቶ አሰግደው፣ ይህም የአካባቢው ስነ ምህዳር፣ የብዝሃ ህይወት ሀብቶች እንዲጠበቁ፣ የጠፉ ዕፅዋትና እንስሳት እንዲመለሱ ያደርጋል፡፡ ክረምት በመጣ ቁጥር የከተማ አስተዳደሩንና ነዋሪዎችን ይፈትን የነበረውንና በተለያዩ ጊዜያት በሰው ህይወትና ንብረት ላይ አደጋ ሲያስከትል የቆየውን የጎርፍ አደጋ ማስቀረት አስችሏል፡፡ በወንዝ ዳርቻ ልማቱ የጎርፍ መከላከያ የድጋፍ ግንቦች ግንባታና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡

ኢንጂነዬር እንዳሻው በበኩላቸው በግንፍሌም ሆነ በሌሎች የወንዝ ዳርቻ ልማት የተከናወነባቸው አካባቢዎች ከወንዞቹ ጠርዝ ግራና ቀኝ (buffer zone) ያለው 30 ሜትር ርቀት ከማንኛውም ግንባታና ንክኪ ነፃ እንዲሆኑ ተደርገው እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ መሰረተ ልማቶችን በማካተት ተገንብተዋል። የግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ ካፌን፣ ወንዙ ንፁህና ወጥ ሆኖ እንዲፈስ የሚያችስሉ አነስተኛ የውሃ ማቆሪያዎችን፣ መፀዳጃ ቤቶችን፣ ሰዎች በእግር የሚጓዙበት ወይም ስፖርታዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉባቸው የእግረኛ መንገዶችን፣ የልጆች ማቆያንና መጫዎቻዎችን ጨምሮ የተለያዩ ልማቶችን አካትቶ የተገነባ አረንጓዴ ልማት ነው፡፡ በአካባቢው ይኖሩ የነበሩ የህብረተሰብ ክፍሎችንም በአዋሬና በተለያዩ ቦታዎች በተገቢ ሁኔታ እንዲሰፍሩ ተደርጓል፡፡

የውበትና የጥላ ብቻ ሳይሆን ለምግብነት የሚውሉ ችግኞችም ተተክለውበታል፡፡ በዚህም ለእይታ የማይመችና ለጤና ስጋት የነበረው ወንዝ ወደ ፅዱ፣ ውብና የመዝናኛና ቱሪዝም ማዕከልነት መቀየር ተችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅት የግንፍሌ ወንዝ ዳርቻ ልማት ሙሉ በሙሉ ግንባታው መጠናቀቁን ኢንጂነዬር እንዳሻው ገልፀውልናል፡፡

አዲስ አበባ ወንዞችን መነሻ በማድረግ የተመሰረች ከተማ ብትሆንም ወንዞቿ ተፈጥራዊ ገፅታቸውን አጥተው ነበር የቆዩት፡፡ የወንዞች መልማት፣ ወደተፈጥሯዊ መልክና ገፅታቸው መመለስ የአዲስ አበባ ትልቁ ብስራት ነው፡፡ የወንዝ ዳርቻ ልማት ወንዞችን ወደ ተፈጥሯዊ ይዘታቸው ለመመለስና ጤናማ የሆነ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስችላል፡፡ የከተማዋ አረንጓዴ ሽፋንም እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ አዲስ አበባ የቱሪስቶች መተላለፊያ ሳትሆን ማረፊያ እንድትሆን እንዲሁም ዜጎች ፅዱና አረንጓዴ አካባቢ የመኖር መብታቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ በተጨማሪም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረገውን ጥረት በማገዝ ከፍ ያለ ጠቀሜታ እንደሚኖራቸው ምክትል ቢሮ ኃላፊው ኢንጂነዬር እንዳሻው አስረድተዋል፡፡

በ2017 በጀት ዓመት የወንዝ ዳርቻ ልማትን በሰፊው ከመተግበር ባሻገር ወንዞች ንጽህናቸው ተጠብቆ እንዲቀጥል ለማድረግ የወንዝ ዳርቻ ልማትና ብክለትን ለመቆጣጠር የሚያስችል ደንብ ቁጥር 180/2016 ወደ ስራ መገባቱ ትልቅ እርምጃ ነው። የወንዝ ዳርቻ ልማቱ የከተማዋን ገፅታ የሚቀይር፣ በርካታ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳዎች ያሉት፣ የአሁኑን ብቻ ሳይሆን የመጪውን ትውልድ ታሳቢ ያደረገ ልማት እንደሆነ አቶ አሰግደው አስረድተዋል፡፡

የቀበና ወንዝ ዳርቻ የኮሪደር ልማት አስተባባሪ አቶ ሞገስ እንደተናገሩት፣ የወንዝ ዳርቻ ልማት በአጭር ጊዜ የአዲስ አበባን ገጽታ በትልቁ የቀየረ ስራ ነው። የከተማ አስተዳደሩ አዲስ አበባን የብልጽግና ተምሳሌት፣ የአፍሪካ ከተሞች ኩራት፣ ለኑሮ ምቹ ለማድረግ የገባውን ቃል በተጨባጭ እየተገበረ ስለመሆኑ ህያው ምስክር የሆነ ስራ ነው፡፡


ethio telecom
ኢትዮ ቴሌኮም
ቴሌብር
telebirr
እንኳን ለብርሃነ መስቀሉ
በሠላም አደረሳችሁ!


አዲስ አበባ
Addis Ababa
The Vibrant Hub of Africa
የአዲስ አበባ ቱሪዝም ኮሚሽን
ADDIS ABABA TOURISM COMMISSION
ለከተማችን ነዋሪዎች እንዲሁም ለመላው የክርስትና እምነት ተከታዮች በሙሉ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቱሪዝም ኮሚሽን እንኳን ለ2018 ዓ.ም ለብርሃነ መስቀሉ በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን እያለ መልካም ምኞቱን ይገልፃል፡፡
የአዲስ አበባ ቱሪዝም ኮሚሽን ከተማችንን የሚመጥን ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችል የመዳረሻ ልማትን እና የኮንፈረንስ ማዕከላትን በማልማትና በማስፋፋት የሀገር ውስጥና የዓለም አቀፍ ቱሪስቶች መናህርያ እንድትሆን፤ የከተማችን ነዋሪ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ በትኩረት ይሰራል፡፡
መዲናችን አዲስ አበባ የኮንፈረንስና የቢዝነስ ቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን፣ ከጊዜው ጋር የሚሄድ አገልግሎት የመስጠት፣ በቴክኖሎጅ የታገዘ የግብይትና ፕሮሞሽን ስራ በመስራት የቱሪስት ቁጥርና ገቢ እንዲጨምር ኮሚሽናችን በትኩረት እየሰራ ይገኛል፡፡
ለሁሉም የክርስትና እምነት ተከታዮች እንኳን ለመስቀል በዓል በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን እያልን መልካም ምኞታችንን እንገልፃለን፡፡
መልካም የመስቀል በዓል!
የአዲስ አበባ ከተማ ቱሪዝም ኮሚሽን

ወ/ሮ ሣራ በቀለ እና እታፈራሁ በቀለ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር ¬¬አዲስ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/106/14991/01 ተመዝግቦ የተሰጣቸዉ በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 04 በ ሰፋ በርሄ ብረታ ብረት የኮንስትራክሽን እቃዎች ስራ ድርጅት የተመዘገበ ቤት - በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 ክልል ውስጥ በይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000070407308 በሴሪ ቁጥር 0148930 የተመዘገበው የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

በአቶ ሰማን ጀማል ሙሳ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 07 የይዞታ ልዩ መለያ ቁጥር AA000090707168 ሴሪ ቁጥር L 012274 የጠፋባቸው መሆኑን በ 13/01/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያሳወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ 90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ:- ካርታ መጥፋን ስለመግለፅ**

ወ/ሮ ታቦቱ ፀጋዬ በርሔ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ቦሌ12/27/2/8/ሲ/ዕ/146/192/43285/01 ሴሪ ቁጥር 082911 ተመዝግቦ የነበረው ኦርጂናል/ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ለይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች አስናቁ ድንቁ ሀብቴ ህጋዊ ተወካይ አቶ ሲሳይ ዘርጋው በቀን 28/11/2017 ዓ.ም ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የካርታ ቁጥር የካ/10780/12 ባቀረቡት አቤቱታ መሰረት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የጠፋብኝ ስለሆነ በምትኩ እንዲሰጠኝ በማለት አስናቁ ድንቁ ሀብቴ ስም የተመዘገበ የሆነው መጥፋቱ ተገልጾ ለፖሊስ ጣቢያ እና ለአዲስ ሚዲያ ኔትወርክ እንዲጻፍልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

በመሆኑም ማህደራቸው ወጦልን በማንዋል ባጣራነው መሰረት በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ወረዳ 11 የሆነው ኮንደሚኒየም አስናቁ ድንቁ ሀብቴ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ የካርታ ቁጥር የካ/10780/12 ሴሪ ቁጥር 1499259 የሆነ ኮንደሚኒየም ቤት ስፋት 110 ካ.ሜ የቤቱ አገልግሎት ለመኖሪያ የሆነ ቤት ማረጋገጫ ካርታቸው የጠፋ ስለሆነ ቤቱን በዕዳ አስገዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት ጥሪ የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገ በኋላ ማህደሩን የማናደራጅ እና ሀላፊነቱን የማንወስድ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**ጉዳዩ፡- የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ**

ከላይ በርእሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባ መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወረዳ 12 በ ወ/ሮ ፀሐይ አበበ እሸቱ ስም የተመዘገበ የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር B-46/20 የቤት ባለቤትነት የይዞታ ማረጋገጫ የካርታ ቁጥር የካ/12/17970/08 የተሰጠበት ቀን 02/02/2008 ዓ/ም የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት እንደጠፋባቸው በቀን 09/01/2018 ዓ/ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ ታውጀ በ90 ቀናት ውስጥ በይዞታው ላይ ሙብት አለኝ የሚል እና ካርታውን ያገኘ ካለ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዲያመጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው የተደረገ ሲሆን ይህ ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ እየገለጽን ይህ ባይህን ለአመልካቹ ምትክ ካርታ ተዘጋጅቶ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 07 በ ሳሚ መሃመድ ይስሃቅ የተመዘገበ ቤት __ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ በወረዳ 07 ክልል ውስጥ በይዞታ ልይ መለያ ቁጥር AA000070706705 በሴሪ ቁጥር 0126729 የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ ሙብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

---

አቶ/ወ/ሮ/ወ/ሪት አልታዬ ይድነቃቸው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 12 ካርታ ቁጥር ሲዝ/ዕጣ/520/91_ሴሪ ቁጥር 2487 ተመዝግቦ የነበረው ኦሪጅናል/ዋናው የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋባቸው በተለያየ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባለው 20 ቀናት ውስጥ በቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ለይዞታ አገልግሎትና ማስተካከል ዳይሬክቶሬት ካልቀረበ በምትኩ ሌላ አዲስ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የቦሌ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

**የጠፋ ካርታ በጋዜጣ እንዲወጣ ስለማሳወቅ**

ከላይ በርዕሱ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በየካ ክ/ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ወረዳ 07 ሬንቦ ፕላስቲክና ፎም ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር ስም የተመዘገበው የመሬት ይዞታ የቤት ቁጥር __ ባለቤትነት የይዞታ ካርታ ቁጥር የካ176045/04 የተሰጠበት ቀን 18/11/04 ዓ/ም የሴሪ ቁጥር 027118 የሆነ የሙብት ማረጋገጫ ሰርተፍኬት እንደጠፋባቸው በቀን 12/01/2018 ዓ.ም አመልክተው ይህንኑ ይዞታ በጋዜጣ 30 ቀን ውስጥ በይዞታው ሙብት አለኝ የሚል እና ይህ ካርታ የጠፋ ስለሆነ ያገኘ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲወጣልኝ ሲሉ ያመለከቱ ስለሆነ የይዞታ ካርታው መጥፋቱን በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣላቸው ሲሆን ካርታ መጥፋቱን የሚያውቅ ካለ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ይዞታ ምዝገባ እና መረጃ ኤጀንሲ የካ ቅርንጫፍ እንዲያሳውቅ ይህ ባይሆን ለአመልካቹ ካርታ ወጪ ተደርጎ የሚሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የየካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ክልል ውስጥ የሚገኝ በካርታ ቁጥር ቦሌ15/309/141-8943/13-668/01 ሴሪ ቁጥር 148135 በአቶ ካሳ አሳየኸኝ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ቤት እናት ማህደር ከለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት በማህደር ክፍላችን ተፈልጎ ባለመገኘቱ ማህደራቸውን ልናደራጅላቸው ስለሆነ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ30 ቀናት ውስጥ በለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅ/ጽ/ቤት ተቃውሞውን እንዲያቀርቡ እያሳሰብን፣ በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ተቃውሞ የማያቀርቡ ከሆነ በምትኩ በመመሪያው በሚፈቅደው መሠረት ሌላ ካርታ የሚሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአፈወርቅ ግርማ ስም የተመዘገበ ይዞታ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ወረዳ 01 የይዞታ ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/99/20534/00 ሴሪ ቁጥር 007525 የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 12/01/2018 ዓ/ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንደሚሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ90 (ዘጠና) ቀናት ውስጥ ፅ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በአዲሱ አደረጃጀት ወረዳ 13 የቤት ቁጥር 1059 ለሆነው ቤት የካርታ ቁጥር 14/09/1/1147 በእነ አቶ አስቻለው ሙሴ አለሙ ስም የይዞታ/የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ ካርታ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ካርታው በመጥፋቱ ምክንያት የካርታ ኮፒ አገልግሎት የተጠየቀ ሲሆን አገልግሎቱን ለመስጠት የሙብት ፈጠራና የይዞታ አገልግሎት አሰጣጥ ደንብ ቁጥር 163/2016 አንቀጽ 23 መሰረት የባለይዞታው የይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ መጥፋቱ በአዲስ ልሳን ጋዜጣ ማስታወቂያ ወጥቶ በ30 (ሰላሳ ቀን) ቀን ውስጥ ተቃዋሚ ካልቀረበ አገልግሎቱን መስጠት እንደሚቻል ተደንግጎ ይገኛል፡፡ ስለሆነም ካርታውን ይዤዋለሁ የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 (ሰላሳ ቀን) ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይዞ እንዲቀርብ እያሳሰብን ይህ ካልሆነ ግን በመመሪያው መሰረት የጠፋውን ካርታ አምክነን በምትኩ ሌላ የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የምንሰጥ መሆኑነ እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

**የግዢ መለያ ቁጥር 01/2018 ዓ.ም**

የአባይ ምንጭ ቅድመ አንደኛና ልማት ምንጭ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2018 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚውል ከዚህ በታች በሎት በሎት በዝርዝር የተገለፁትን እቃዎች ሎት 1 የፅህፈት መሳሪያዎች፣ ሎት 2 የፅዳት ዕቃዎች፣ ሎት 3 የደንብ ልብስ፣ ሎት 4 አላቂ እና ቋሚ የቢሮ ዕቃዎች፣ ሎት 5 የቢሮ ፈርኒቸር እቃዎች፣ ሎት 6 የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ሎት 7 የህትመት ስራዎች ሎት 8 የደንብ ልብስ ስፌት አገልግሎት በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም

1. የንግድ ምዝገባ ሰርተፍኬት

2. በዘርፉ የተሰማሩበት የታደሰ የንግድ ፍቃድ

3. በአቅራቢነት ዝርዝር የተመዘገቡበት ሰርተፍኬት

4. የቫት ተመዝጋቢ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰርተፍኬት ማቅረብ የምትችሉ ከሎት 1 እስከ ሎት 7 በዝርዝር ለተገለፁት እቃዎች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ናሙና ማቅረብ ወይም ማሳየት የሚችል ናሙና ማቅረብ ለማይችሉት እቃዎች በምስል የተደገፈ /ፎቶ ግራፍ/ በማቅረብ ለጨረታ ማስከበሪያ ለሎት1. 6,000፣ ለሎት2. 6,000፣ ለሎት3. 6,000፣ ለሎት4. 5,000፣ ለሎት5. 2,500፣ ለሎት6. 2,500፣ ለሎት7. 500፣ ለሎት8. 500 በት/ቤቱ ስም በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ማሲያዝ ይኖርባችኋል። ተጫራቾች የጨረታ አሸናፊ ሆነው የተገኙባቸውን እቃዎች ከአጠቃላይ ዋጋ 10% ለውል ማስከበሪያ ማስያዝ የሚችል ማንኛውም ተጫራቾች ከላይ የተዘረዘሩትን ሰነዶች ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን በሁለት ፖስታ በማሸግ ት/ቤቱ ለእዚሁ ጨረታ ባዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ በመሙላት መወዳደር የምትችሉ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 /አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በአባይ ምንጭ ቅድመ አንደኛና ልማት ምንጭ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ግዢ ክፍል ለምንገዛቸው እቃዎች የተዘጋጀ የጨረታ ሰነድ በማይመለስ 200.00 ብር /ሁለት መቶ ብር/ በመግዛት ከላይ በዝርዝር የተገለጸውን ሰነድ ዋናውንና ኮፒውን እንዲሁም ዋጋ የሞላችሁበትን ሰነድ በፖስታ በማሸግ ት/ቤቱ ለእዚህ ጨረታ ባዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ውስጥ በማስገባት እንድትወዳደሩ ተጋብዛችኋል፡፡ ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ በ10 ኛው ቀን 11:30 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በ11ኛው ቀን በ4:00 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል። በተጠቀሰው ቀንና ሰዓት ጨረታው ሲከፈት የማይገኙ ተጫራቾች በሌሉበት ጨረታው እንደሚከፈት እያሳወቅን የተጠቀሰው ቀን ቅዳሜ እና እሁድ እንዲሁም የበዓል ቀን ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተጠቀሰው ሰዓት ይከፈታል፡፡

**ማሳሰቢያ፡- ት/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።**

**አድራሻ፡- በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 1 ጦርሀይሎች በመኮንኖች ክበብ 200 ሜትር ገባ ብሎ**

**ስልክ፡- 0113-20-03-51**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ በልደታ ክፍለ ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የልማት ምንጭ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

## የኦሜድላ መ/ደ/ት/ቤት
## የ2018 ዓ/ም ግልፅ ጨረታ ማስረታወቂያ

የኦሜድላ መ/ደ/ት/ቤት የ2018 ዓ/ም የተለያዩ አገልግሎት የሚሆን ግብዓቶችን በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት ከታች በተዘረዘሩትን መሰረት :-

ሎት 1 የበጀት ኮድ 6211 የደንብ ልብስ ዕቃ-------------3500 ብር እንዲሁም ስፌቱን ብቻ ለሚወዳደሩ -----1500 ብር

ሎት 2 የበጀት ኮድ 6212 አላቂ የቢሮ ዕቃዎች---------------------- 4400 ብር

ሎት 3 የበጀት ኮድ 6213 የህትመት ------------------------------- 1000 ብር

ሎት 4 የበጀት ኮድ 6214 የህክምና ዕቃ------------------------------ 1000 ብር

ሎት 5 የበጀት ኮድ 6215 የትምህርት ዕቃ------------------------------ 2000 ብር

ሎት 6 የበጀት ኮድ 6218 ፅዳት ዕቃ----------------------------------- 2800 ብር

ሎት 7 የበጀት ኮድ 6219 ልዩ ልዩ ዕቃዎች --------------------------- 1300 ብር

ሎት 8 የበጀት ኮድ 6313 የኤሌክትሮኒክስ ዕቃ------------------------- 2000 ብር

ሎት 9 የበጀት ኮድ 6314 ቋሚ ዕቃ------------------------------------- 2500 ብር

ሎት 10 የበጀት ኮድ 6419 ልዩ ልዩ ዕቃዎች --------------------------- 1000 ብር

- በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ
- የግብር ከፋይነት ሰርተፊኬት/ቲን ያለው
- የተጨማሪ እሴት ታክስ ሰርተፊኬት /ቫት/ ተመዝጋቢ ሰርተፍኬት ያለው
- በአቅራቢዎች ዝርዝር የተመዘገቡ
- ጥቃቅን እና አነስተኛ ተጫራቶች በሚያመርቱት የሀገር ውስጥ ምርት ብቻ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን በሌሎች በማያመርቱት ግብዓቶች ላይ አስፈላጊውን የጨረታ ማስከበሪያ በሎቱ ላይ የተገለፀውን ገንዘብ መጠን የማስያዝ ግዴታ አለበት
- ጨረታው 10 የስራ ቀናት የሚቆይ ሲሆን በ10ኛው ቀናት 11:30 ሰዓት ተዘግቶ በ11ኛው ቀን ጠዋት 3:00 ሰዓት ታሽጎ ተጫራቶች እና ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 3:30 ሰዓት ጨረታው የሚከፈት ሲሆን ነገር ግን የጨረታው መክፍቻ 11ኛው ቀን ቅዳሜ እና በዓል ቀን የሚውል ከሆነ የቀጣዩ የስራ ቀን ላይ የሚከፈት ይሆናል
- የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ በኩል የተረጋገጠ ሲፒኦ ማቅረብ አለበት
- ተጫራቶች መ/ቤቱ ባቀረበው የዋጋ ማቅረቢያ ሰነድ ላይ ዋጋ ሞልቶ ማቅረብ አለባቸው
- ተጫራቶች የሚያቀርቡት ዋጋ ጠቅላላ ዋጋ ከነቫቱ መሆን አለበት
- በጨረታው ላይ በቀረቡት ከሎት 1 እስከ ሎት 7 እና ሎት 10 ያሉትን ዕቃዎች ተጫራቹ (ናሙና) ወይም ሳምፕል ማቅረብ ያለበት ሲሆን የደንብ ልብስ ስፌትን በተመለከተ እሱም በሎቱ ላይ የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ማስያዝ ያለበት ሲሆን የስፌት ሳምፕል ማቅረብ አለበት
- ከሎት 8 እስከ ሎት 9 ያሉትን በቀረበው ስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት ነገር ግን ተጫራቹ በከፊል ናሙናዎችን አቅርቦ ከሆነ ባቀረበው ናሙና ብቻ የሚወዳደር ይሆናል
- መ/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉ ወይም በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው
- የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 250.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ብቻ በመክፈል የጨረታ ሰነዱን ከግዥ ክፍል መውሰድ የምትችሉ መሆኑን እና ነገር ግን ጥቃቅን እና አነስተኛ ራሳቸው በሚያመርቱት ብቻ ካደራጃቸው አካላት የድጋፍ ደብዳቤ ካቀረቡ መውሰድ የሚችሉ ይሆናል በሌሎች ዕቃዎች ላይ መወዳደር ከፈለጉ የጨረታ ሰነዱን የመግዛት ግዴታ አለባቸው
- አሸናፊ ተጫራቾች ያሸነፉበትን ዕቃዎች በሙሉ በየሎቱ የተገለፁትን አሸናፊ መሆናቸው ከታወቀበት ቀን ጀምሮ ውል በተገባበት በ15 ቀናት ውስጥ ዕቃዎቹን አስገብቶ ማጠናቀቅ አለበት

**አድራሻ : - አብነት አለሙ ሜዳ 100 ሜትር ከፍ ብለው ያገኙናል**
**ስልክ ቁጥር 011-213-51-89**
**የልደታ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ የኦሜድላ የአንደኛ እና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት**

# ለመጀመሪያ ዙር የወጣ ግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

የአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ ለ2018 በጀት ዓመት ለአካዳሚው አገልግሎት የሚውሉ የተለያዩ ዕቃዎች እና የአገልግሎት ቀጥሎ የቀረበ ስለሆነ ተጫራቾች ቀጥሎ በቀረበው ዝርዝር መሠረት በግልፅ ጨረታ አወዳደሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

| ተ.ቁ | የዕቃዎች/ አቅርቦት ዓይነት | ሎት | ጨረታ ማስከበሪያ | የጨረታ መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የጽህፈት መርጃ መሳሪያዎች እና የኮፒና ፕሪንተር ቀለሞች | ሎት1 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ-0001/2017 |
| 2 | የጽዳት ዕቃዎች ግዥ | ሎት2 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ-0001/2017 |
| 3 | የመኪና ጎማ፣ ጌጣጌጥ እና ተያያዥ እቀዎች | ሎት3 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ-0001/2017 |
| 4 | ለዳይኬር(ለህጻናት ማቆያ) የሚሆኑ እቃዎች | ሎት4 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ-0001/2017 |
| 5 | የኮምፒዉተር፣ የፕሪንር እና ፎቶ ኮፒ ማሽኖች ጥገና | ሎት5 | 5,000 | አ/አ/አ/አካ/ግ/ጨ-0001/2017 |

ስለሆነም ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዝርዝር መስፈርቶች የምታሟሉ ተጫራቾች በጨረታው እንድትሳተፉ ተጋብዛችኋል፡-

1. በዘመኑ እና በዘርፉ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያለው፣ የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ያለው፣ በታክስ ባለስልጣን የተሰጠ የግብር ከፋይ ምዝገባ ሰርተፊኬት ፡ቲን ነምበር ያለው፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ወይም ቫት ተመዝጋቢ የሆነ፣ በመንግሥት ግዥ ለመሳተፍ በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ድረ-ገፅ በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገበ እንዲሁም የሚጠበቅባቸውን የግብር ግዴታ የተወጡና በጨረታ ላይ ለመሳተፍ የሚችሉ መሆኑን የሚገልፅ የድጋፍ ደብዳቤ ከገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው፡፡
2. ተጫራቾች ለእያንዳንዱ ጨረታ የማይመለስ ብር 200 (ሁለት መቶ) በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጨረታ ሰነዱን ከአራት ኪሎ አደባባይ ወደ ፒያሳ በሚስደዉ መንገድ በሚገኘው ዳብር ህንፃ ሶስተኛ ፎቅ ላይ ከሚገኘዉ የአድስ አበባ አመራር አካዳሚ የግዥ ዳይሬክተር 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር- 306 በሚገኘው ዘዉተር የስራ ሰዓት በመቅርብ መግዛት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች ከላይ በሰንጠረዡ ላይ በቀረበው የብር መጠን መሠረት የጨረታ ማስከበሪያ "ለአዲስ አበባ አመራር አካዳሚ" በሚል አድራሻ በባንክ የክፍያ ትዕዛዝ (C.P.O) ወይም ቅድመ ሁኔታ ባላስቀመጠ የባንክ ዋስትና ወይም በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁ ከሆነ ካደራጃቸው መ/ቤት የዋስትና ደብዳቤ ማማቅረብ አለባቸው፡፡
4. ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ሰነድ በሁለት በታሸገ ኤንቬሎፕ (ፖስታ) ማለትም ቴክኒካል እና ፋይናንሻል በሚል የሚያቀርቡ ሲሆን በአንደኛው ቴክኒካል ኤንቬሎፕ (ፖስታ) ላይ ንግድ ፍቃድ፣ ንግድ ምዝገባ፣ ቲን ነበር፣ ቫት፣ የአቅራቢነት ምዝገባ፣ ክሊራንስ እና C.P.O) በአንድ ላይ በሁለተኛው ፋይናንሻል ኤንቬሎፕ (ፖስታ) የመወዳደሪያ ዋጋችሁን ብቻ በመሙላት እና የሁለቱንም ኦርጅናል ሰነዶች አንድ አንድ ኮፒ ማቅረብ ያኖርባቹዋል፡፡ ተጫራቹ ከአካዳሚዉ የወሰዱትን የጨረታ ሰነድ የተጠየቁትን ሞልተዉ እያንዳንዱ ግጽ ላይ ማህተም በመምታት ፖስታዉን አሽጋችሁ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ተጫራቾች በፖስታቸው ላይ የድርጅታቸውን ስም በመፃፍና የሚወዳደሩበትን ሎት በመጻፍ ለዚህ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ የጨረታ ሰነዳቸውን ማስገባት አለባቸው፡፡
5. ከሎት 1-5 ለቀረቡት የጨረታ መክፈቻ ቀን ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ10 (አስር) የስራ ቀናት በአየር ላይ የሚቆይ ሲሆን በ11ኛው የስራ ቀን ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ታሽጎ በዚሁ ዕለት 4፡15 ሰዓት ላይ ተጫራች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
6. ጨረታ ሰነድ የመክፈቻ ቀን ላይ ህዝባዊ ባአል(ካላንደር የሚዘጋ) ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን የሚከፈት ይሆናል፡፡
7. አካዳሚው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ይሁን በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

**ስለ ጨረታው ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ከፈለጉ ቀጥሎ ባለው የስልክ ቁጥር ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡**

**0116- 67-33-90**

**አዲስ አበባ አመራር አካዳሚ**

## ጉዳዩ፡- የደረሰኝ መጥፋት ማሳወቅ

በአዲስ አበባ ክልል የካ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 1007 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0000042105 የሚታወቀው ታደሰ ባልቻና ቤተሰቦቻቸው ሴንተራል ሸዋ ሆቴል በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ያልተሰራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር ከ16964 እስከ 16965 ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው ምስራቅ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡- ታደሰ ባልቻና ቤተሰቦቻቸው ሴንተራል ሸዋ ሆቴል**

## ጉዳዩ፡- የደረሰኝ መጥፋት ማሳወቅ

በአዲስ አበባ ክልል የአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 የቤት ቁጥር 393/396 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0093847792 የሚታወቀው ሰልዋ አብዱልባስጥ አብደላ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ___ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ያልተሰራበት የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ ከቁጥር ከ1 እስከ 50 ስለጠፋብን በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራበት እና የጠፋ መሆኑ የሶስተኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ይሁንና ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው ___ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ወይም በአቅራቢያ የሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም፡- ሰልዋ አብዱልባስጥ አብደላ**

በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት ተደራጅቶ የሚገኘው ናሽናል ሞተርስ ኮርፖሬሽን ሰራተኞች ኃላ/የተ/ገንዘብ ቁጠባና ብድር ህብረት ስራ ማህበር በቀን 08/09/17 ዓ.ም በአደረገው ጠቅላላ ጉባኤ ማህበሩ እንዲፈርስ በሙሉ ድምፅ የተወሰነ በመሆኑ ይህን የማህበሩን መፈረስ የሚቃወም ወይም ይገባኛል የሚል አካል ካለ በአንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 92 መሰረት ጋዜጣው አየር ላይ ከዋለ ጀምሮ በ2 ወራት ውስጥ ተቃውሞውን በአካል በመቅረብ ለአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ህብረት ስራ ጽ/ቤት ቢሮ ቁጥር 505 እዲያቀርብ እየገለጽን በዚህ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ንብረት የመጠየቅ መብት የሌለው መሆኑን በመግለጽ ጥሪ እናስተላልፋለን፡፡

**በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ አስተዳደር ህብረት ሥራ ጽ/ቤት**

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ አስተዳደር በወረዳ 09 ክልል ውስጥ በወ/ሮ መታፈሪያሽ ውብሸት ክብረት ስም በካታ ቁጥር 035511 ሴሪ ቁጥር 135229 በሆነ የተመዘገበው የጋራ መኖሪያ ቤት፤ የቤት ባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት /ካርታ ስለጠፋባቸው በማንኛውም መልኩ በእጄ ይገኛል የሚል አካል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው መቅረብ የሚችሉ መሆኑን እያሳወቅን ይህ ካልሆነ በምትኩ ሌላ የመሬት ይዞታ መብት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

**የግዥ መለያ ቁጥር 01/2018 ዓ.ም**

በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የመቅደላ ቅደመ አንደኛ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ለ2018 በጀት ዓመት አገልግሎት የሚዉሉ ከዚህ በታች በሎት በዝርዝር የተገለፁትን እቃዎች ሎት(01) የደንብ ልብስ፣ ሎት(02) አላቂ የፅህፈት መሳሪያ፣ ሎት(03) የጥገና እቃዎች፣ ሎት(04) የህክምና እቃዎች፣ ሎት(05 የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች፣ ሎት(06) የተላያዩ የቢሮ ፈርኒቸር መገልገያ እቃዎች ሎት(7)አላቂ ትምህርት እቃዎች፣ ሎት(08) የጽዳት እቃዎች፣ ሎት(09) ልዩ ልዩ የህትመት ስራዎች ሎት(10) የመስተንግዶ ዉሀ እና ቆሎ፣ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል:: በመሆኑም በጨረታዉ ላይ መሳተፍ የምትፈልጉ ማንኛዉም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርት የምታሟሉ ተጫራቾች መሳተፍ የምትችሉ መሆኑን እየገለፅን ጨረታዉን ለመሳተፍ ተጫራቾች:-

1. ሕጋዊ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ያላቸው እና የዘመኑን ግብር የከፈሉ መሆን አለባችዉ
2. ተጫራቾች በአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ የተመዘገቡና በጨረታ ጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወዳደሩ የተፈቀደ የምስክር ወረቀት ኮፒ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘዉ ማቅረብ ይኖርባቸዋል::
3. ተጫራቾች በተጨማሪ እሴት ታክስ VAT ተመዝጋቢ የሆኑና ለዚህም የተመዘገቡበትን ኮፒ አያይዘዉ ማቅረብ ይኖርባቸዋል ::
4. ተጫራቾች ለሚጫረቱበት እቃ ናሙና ማቅረብ ግዴታ ሲሆን በሚቀርበዉ ናሙናዎች ላይ የድርጅቱን ስም ወይም አርማ ሆነ ማህተም ማድረግ የተከለከለ ነዉ::
5. ተጫራቾች ለጨረታ ማስከበሪያ ሲፒዮ ሎት 01 ብር 8000፣ ሎት 02 ብር 5000፣ ሎት 03 ብር 2000፣ ሎት 04 ብር 1000፣ ሎት 05 ብር 3000፣ ሎት 06 ብር 8000፣ ሎት 07 ብር 5000፣ ሎት 08 ብር 8000፣ ሎት 09 ብር 1000 ሎት 10 ብር 1000 በባንክ በተረጋገጠ (CPO ) ከጨረታው ሰነድ ጋር በፖስታ በማሸግ ማቅረብ ይኖርባቸዋል በቼክ ማቅረብ አይቻልም ::
6. ተጫራቾች በወሰዱት የጨረታ ሰነድ ላይ በተዘጋጀዉ የዋጋ ዝርዝር መሙያ ላይ ሞልተው ማቅረብ አለባቸው አማራጭ ዋጋ ግን መሙላት አይቻልም:: ት/ቤቱ ካዘጋጀዉ የዋጋ መሙያ ሰነድ ዉጭ መሙላት አይቻልም::
7. ባቀረቡት ዋጋ ዝርዝር ላይ ቫት (VAT) ማካተት አለባቸዉ::
8. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የሚጫረቱበትን የመወዳደርያ ዋጋ ሞልተዉ በታሸገ ፖስታ ኦርጅናል እና ኮፒ በተለያየ ፖስታ ማቅረብ ግዴታ ነዉ ::
9. የጨረታው አሸናፊ የሚለየው በተሞላው ነጠላ ዋጋ ሊሆን ይችላል ስርዝ ድልዝ ተቀባይነት የለዉም::
10. ተጫራቾ ያሸነፉባቸዉን እቃዎች በራሳቸዉ ትራንስፖርት ግዥ ፈጻሚዉ መስሪያ ቤት ድረስ ማቅረብ አለባቸዉ::
11. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ) ብር ት/ቤቱ የሂሳብ ክፍል በመክፈል መዉሰድ የምትችሉ መሆኑን እንገልፃለን::
12. ጥቃቅንና አነስተኛ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ C.P.O እና የጨረታ ሰነድ በደብዳቤ የምናስተናግደዉ አምርታቹ ለገበያ በምታቀርቡት ምርት ላይ ብቻ መሆኑን እየገለፅን ጨረታዉ አየር ላይ የሚቆየዉ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 (አስር) ተከታታይ የስራ ቀናት ሲሆን ጨረታዉ በ11ኛዉ ቀን ከጠዋቱ 4.00 ሰዓት ታሽጎ 4.30 ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸዉ በተገኙበት የሚከፈት ሲሆን ተጫራቾች ወይም ወኪሎቻቸዉ ባይገኙም ጨረታዉ የሚከፈት መሆኑን እናሳዉቃለን::

**ማሳሰቢያ:-** ትምህርት ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሠረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

**አድራሻ:- ልደታ ክ/ከ ወረዳ 06 የሚገኘው መቅደላ የመጀ/ደ/ት/ቤት ከፍተኛ 23 መሰናዶ እና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ጀርባ I.C.S አጠገብ።**

**ለተጨማሪ መረጃ:- በስልክ ቁጥር:- 011-3-69-09-83 / 011-3-20-30-82 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።**

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ት/ቢሮ ልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 06 የመቅደላ ቅድመ አንደኛ አንደኛና መካ/ደ/ት/ቤት**

## የጨረታ ማስታወቂያ

**ቁጥር 002/2018 ዓ/ም**

በንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስ የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ግዥ ቡድን ለ2018 በጀት አመት ሁለተኛ ዙር ጨረታ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በመደበኛ በጀት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል:: ስለሆነም

| ሎት | አይነት | የጨረታ ማስከበሪያ C.P.O |
|---|---|---|
| ሎት 1 | የካፌ እና የቢሮ መስተንግዶ | 10,000.00 |
| ሎት 2 | የትራንስፖርትና የጭነት መኪና ኪራይ | 5,000.00 |
| ሎት 3 | የከባድ መኪና የጎማ ጥገና | 5,000.00 |
| ሎት 4 | የቢሮ የፍርኒቸር ዕቃዎች ጥገና | 3,000.00 |

ብቃትያላቸውንና በመስኩ የተሰማሩ ተጫራቾችን አወዳድሮ ግዥ መፈጸም ይፈልጋል በዚህም መሰረት:---

1. በጨረታው ለመወዳደር ፍላጎት ያላቸው ተጫራቾች የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያላቸው፤ የዘመኑ ግብር የከፈሉ፤ የቲን ቁጥር እና የቫት ተመዝጋቢ የሆኑ፤ በአቅራቢነት የተመዘገቡና የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ ::
2. ተጫራቾች የጨረታውን ማስከበሪያ በባንክ የተረጋገጠ ሲፒኦ ከላይ በሰንጠረዥ በተቀመጠው ሎት መጠን ማስያዝ ያለባቸው ሲሆን የጨረታ ማስከበሪያ ከጨረታ ሰነዳቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው::
3. ተጫራቾች የጨረታውን ዝርዝር የያዘ ሰነድ የማይመለስ ብር 250.00 (ሁለት መቶ ሃምሳ ብር ብቻ) በመክፈል ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ተከታታይ የስራ ቀናት ኃይሌ ጋርመንት አደባባይ ን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ፐብሊክ ፑል የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት ግዥ ቡድን 6ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 3 መግዛት ይችላሉ::
4. ተጫራቾች የገዙትን የጨረታ ሰነድ በመሙላት እና ከላይ የተገለጹትን ማስረጃዎች በ2 ፖስታ ዋናውን እና ኮፒውን በማሸግ ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት እስከ 10ኛ ቀን 11:30 ሰዓት ድረስ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል::
5. ጨረታው በ11ኛው ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪል በተገኙበት ልክ በ4:00 ሰዓት ይከፈታል::
6. መ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው::
7. በግልፅ የማይታዩ መረጃዎች እና ስርዝ ድልዝ በመስርያ ቤ/ቱ ተቀባይነት አይኖረውም::

**ለተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልግዎት ስልክ 0912885086 ይደውሉ**

**የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ ፐብሊክ ስርቪስ የሰዉ ሃብት ልማት ጽ/ቤት የመንግስት ግዢ ቡድን**

**የንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ጽ/ቤት**

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክ/ከተማ ወረዳ 09 የካርታ ልዩ መለያ ኮድ ቁጥር AA000050902666 ሴሪ ቁጥር R 087406 በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምኩ ሌላ ሰርተፊኬት /ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

በአዲስ አበባ እስልምና ጉዳዮች ከ/ም ቤት ኑርሰባህ መስጂድ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 06 የይዞታ መለያ ቁጥር AA000060604218 የሆነው ይዞታ በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ የቤት ባለቤትነት ምዝገባ ምስክር ወረቀት ስለጠፋባቸው በማናቸውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ /ይገኖዋለሁ/ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 90 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳስባለን::

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ቦሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

## የስራ ቅጥር ማስታወቂያ

በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በወረዳ 6 ስር የሚገኘው የሜይዴይ ቅድመ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ክፍት የስራ መደቦች ሰራተኞችን በኮንትራት ቀጥሮ ለማሰራት ይፈልጋል። በዚህመሰረት አመልካቾች ለምዝገባ ሲመጡ ማቅረብ ያለባቸው ማስረጃዎች ከዚህ በታች በማሳሰቢያው ላይ በተጠቀሰው መሰረት ይሆናል፡፡

| ተ.ቁ | ክፍት የስራ መደቡ መጠሪያ | የስራ መደቡ የሚጠይቀው ተፈላጊ ችሎታ እና የስራ ልምድ | የስራ ደረጃ | ደሞዝ | ብዛት | የቅጥርሁኑታ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የመልዕክት አገልግሎት ሰራተኛ | 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም 9ኛ ክፍል ያተኛቀቀና 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት | II | 4926 | 1 | በኮንትራት | የተለያዩ ጥቅማ ጥቅም አለው |
| 2 | ጥበቃና አትክልተኛ ሰራተኛ | 10ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 2 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም 9ኛ ክፍል ያተኛቀቀና 3 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት ወይም 8ኛ ክፍል ያጠናቀቀና 4 ዓመት የስራ ልምድ ያለው/ያላት | III | 5104 | 2 | በኮንትራት | የተለያዩ ጥቅማ ጥቅም አለው |
| 3 | ረዳት አንባቢ ሰራተኛ 1 | 12ኛ ክፍል መልቀቂያ ወይም 10ኛ ክፍል መልቀቂያ ወስዶ /ወስዳ ያጠናቀቀ/ያጠናቀቀች 4 ዓመት የስራ ልምድ በፀሀፊነት ፣ በመዝገብ ቤት ኢንኮደር እና በመረጃ አያያዝ መሰረታዊ ኮፒውተር እውቀት ያለው /ያላት | VI | 5283 | 1 | በኮንትራት | የተለያዩ ጥቅማ ጥቅም አለው |

**ማሳሰቢያ፡-** አመልካቾች ለምዝገባ ሲመጡ ማሟላት ያለባቸው

- የትምህርት ማስረጃና የስራ ልምድ
- የስራ ልምድ ማስረጃ የግል ድርጅት የሰራ ከሆነ ግብር የተገበረበት ከገቢዎች ስለመገበራቸው ማስረጃ መቅረብ አለባቸው
- ማንነታቸውን የሚገልፅ መታወቂያ
- በአጠቃላይ ለተዘረዘሩት ማስረጃዎች በሙሉ ዋናውንና የማይመለስ ፎቶ ኮፒ ማቅረብ አለባቸው
- በተራ ቁጥር 3 ላይ በተቀመጠው የስራ መደብ በሌቭል ደረጃ የተመረቁ አመልካቾች የሲኦሲ ማስረጃ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ማቅረብ አለበት
- አድራሻ፡- ጎጃም በረንዳ የቀድሞ ፋሲል ፋርማሲ አጠገብ
- የምዝገባ ቦታ፡- ሜይዴይ ቅድመ አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት የሰው ሀይል አስተዳደር
- የምዝገባ ቀን፡- ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን አንስቶ ባሉት 10 የስራ ቀናት ይሆናል
- የምዝገባ ሰዓት፡- ከጥዋቱ 2፡30 እስከ 6፡00 ከሰዓት ከ8፡00 ሰዓት እስከ 11፡00 ሰዓት ድረስ
- ለበለጠ መረጃ፡- 0112310018 ወይም 0911919184
- የፈተና ቀን፡- በት/ቤቱ በውስጥ ማስታወቂያ ወይም በስልክ የምናሳውቅ ይሆናል

**በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ሜይዴይ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**

---

የእነ ብርሀኔ ምስራቅ አውግቸው በአዲስ አአበባ ከተማ አስተዳደር የካ ክ/ከተማ ወረዳ 07 የካርታ ቁጥር የካ/219515/11 ሴሪ ቁጥር 1469505 በጽ/ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው ባለቤትነት ማረጋገጫ ሰርተፊኬት /ካርታ/ ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት /ካርታ የምንሰጣቸው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የካ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አቶ አዱኛ ረጋሳ በጉለሌ ክ/ከተማ ወረዳ 5 የቤት ቁጥር 306 ካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/119/19010/00 ተመዝግቦ የተሰጣቸው በእጃቸው መገኘት የነበረበት ካርታ የጠፋ በመሆኑ ይህንኑ አስመልክቶ የሚቀርብ ማንኛውም መቃወሚያ ካለ ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ በ20 ቀን ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጉለሌ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ማስረጃውን ይዞ ካልቀረበ ካርታው እንደጠፋ ተቆጥሮ በምትኩ አዲስ ካርታ በማዘጋጀት አገልግሎት የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የዳዊት መዝገቡ መንገሻ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 04 የካርታ ቁጥር ለ/ኩ/24/1/26/16298/00 የሆነው ሰርተፊኬት በፅህፈት ቤታችን ተመዝግቦ የሚገኘው በቤት ባለቤትነት ካርታ በሴሪ ቁጥር 1683955 ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት /ካርታ/ተዘጋጅቶ እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

የደብሬ ብርኃኔ ወንድም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለሚ ኩራ ክ/ከተማ ወረዳ 04 የይዞታው ልዩ ቁጥር AA000061007507230908 የሆነው ፋይላቸው በፅህፈት ቤታችን ተደራጅቶ የሚገኘው ፋይላቸው ስለጠፋባቸው በማንኛውም ምክንያት አግኝቼዋለሁ የሚል ግለሰብም ይሁን ሌላ አካል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት እስከ 30 ቀን ድረስ ጽ/ቤታችን ካልቀረበ በምትኩ ሌላ ፋይል አደራጅተን ወይም ተዘጋጅቶ አገልግሎት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ የለሚ ኩራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

አመልካች ካፕቴን ሳምሶን ሁዲስ ተድላ ስም የተመዘገበ ነዋሪነቱ በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ ወረዳ 10 አያት ዞን 2 መንገድ 10 የቤት ቁጥር 2/19/2 ነዋሪ ሲሆን የቤት ካርታ ስለጠፋብኝ ካርታ ቁጥር ቦሌ10/4/8/1/0623/670/02 ማረጋገጫ ካርታ ስለጠፋብኝ ሌላ ካርታ ምትክ እንዲሰጠኝ በማለት ያቀረቡ በመሆኑ ካርታ የጠፋ መሆኑን በማመልከቻ ያሳወቅን ስለሆነ ይዞታ ቤቱን በዕዳ ይዤዋለሁ፤ አስይዤዋለሁ የሚል አካል በ30 ቀናት በጋዜጣ ጥሪ ስለሚደረግ በተጠቀሰው ቀናት ውስጥ ለተቋሙ እንዲያሳውቁን እያልን በዚህ ምክንያት ለ30 ቀናት የሚቆይ በጋዜጣ ጥሪ እንዲደረግ እየጠየቅን ይህ ጋዜጣ ጥሪ ከተደረገበት በኃላ ሀላፊነት የምንወስድ ይሆናል፡፡

**በመሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ የለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ወረዳ 08 የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የካርታ ቁጥር ኮ/ቀ/የማ/ን/መ/348/19116/00 ሴሪ ቁጥር 093004 በአቶ ዘበርጋ ሽኩር እና ወ/ሮ ፋጡማ ከድር ስም የተመዘገበ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት/ካርታ/ የጠፋባቸው መሆኑን በቀን 12/01/2018 ዓ.ም በመግለጽ ምትክ ካርታ እንዲሰጣቸው ያስታወቁን በመሆኑ በማናቸውም ምክንያት ይዤዋለሁ ወይም አግኝቼዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣ ቀን ጀምሮ እስከ በ30 (ሰላሳ) ቀናት ውስጥ በጽ/ቤታችን ይዘው ካልቀረቡ በምትኩ ሌላ ሰርተፊኬት እንደሚሰጣቸው እናሳውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ኮልፌ ቀራንዮ ክ/ከተማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

---

## የቱሪዝሙ... ከገጽ 11 የዞረ

ስለግድቡ ለጎብኚዎች የሚሆን የተደራጀ መረጃ ማዘጋጀት፣ ማሰራጨትና ተደራሽ ማድረግ ሌላኛው ሥራ እንደሆነ የጠቀሱ ሲሆን፤ የግድቡን ንድፍ፣ አወቃቀር፣ አሠራር እና መሰል ጉዳዮች ከሣይንሳዊ እሳቤ አንፃር የተተነተነ መረጃ መዘጋጀት እንደሚገባ ገልፀዋል። የጥናትና ምርምር ማዕከል እንዲሆን መሥራት አለበት፡፡ በሦስተኛነት መሠራት የሚገባው ደግሞ ከግድቡ ጋር ተፈጥሯዊና ባህላዊ ቱሪዝምን የማቆራኘት ተግባር እንደሆነ አንስተዋል። ከግድቡ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኙ የቱሪዝም ሥፍራዎችን፣ ኃይማኖታዊ እና ባህላዊ ሁነቶችን ... አስተሳስሮ መጠቀም አስፈላጊነት ላይ ትኩረት የሚያሻው ስለመሆኑ አልሸሸጉም፡፡

አክለው እንዳብራሩት፤ የኢኮ-ቱሪዝም ዕድገት የሚሳለጥበትን መንገድ መፍጠር በአራተኛነት የሚነሳ ቁልፍ ጉዳይ ነው። በአምስተኛ ደረጃ፤ በአካባቢው ያለው ማህበረሰብ ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ማህበረሰቡ ግድቡን እና የግድቡን አካባቢ በእኔነት ስሜት እንዲንከባከበው እና እንዲጠብቀው በዘላቂነት የሚጠቀምበትን ሁኔታ ማመቻቸት ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በመጨረሻም፤ የታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ከኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭነቱ ባሻገር ለሀገር እና ለሕዝብ የሚጠቅም አዎንታዊ ለውጥ የሚያመጣ ቁልፍ ሀገራዊ ፕሮጀክት መሆኑን በመገንዘብ፤ ይህንን ጥቅም ለመቋደስ ግድቡን በአግባቡ ማስተዳደር እና በሣይንሳዊ መንገድ መጠቀም እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡ የግድቡ ዋነኛ የቱሪዝም መዳረሻነት ሕልም በተግባር እንዲገለፅ ኢትዮጵያዊያን ግንባር ቀደም ተሳታፊ ሊሆኑ እንደሚገባ፣ የሁሉም ኢትዮጵያዊ አሻራ ያረፈበት እና የጋራ ሀብት የሆነውን ይህንን ግድብ መጎብኘት ከማንም በፊት የኢትዮጵያዊያን መሆን እንዳለበት እንዲሁም በዚህ ትልቅ ፕሮጀክት የጉብኝት ልምዳችን ለማሳደግ መጠቀም እንደሚገባ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

# ከአትሌቲክሱ ባለ ድሎች ምን እንማር?

በሳህሉ ብርሃኑ




ፎቶ -ከገፀ ድር

በቶክዮው ሻምፒዮና የወርቅ ሜዳሊያ ያመጣው ታንዛንያዊው አልፎንስ ፌሊክስ




ፎቶ -ከገፀ ድር

በቶክዮ ሻምፒዮና የወርቅ ሚዳሊያ ያጠለቁት ቤትሪስ ቼቤት እና ፊይዝ ኪፕዬጎን




ፎቶ -ከገፀ ድር

በቶክዮው ሻምፒዮና የወርቅ ሚዳሊያ ያስገኘው የቦትስዋና ቡድን

አንድ የዓለም ሪከርድና ዘጠኝ የሻምፒዮናው ሪከርድ የተሻሻለበት፣ ሳሞአ፣ ሴንት ሉሲያ እና ዩራጓይ የተሰኙ ሀገራት በሻምፒዮናው ለመጀመሪያ ጊዜ ሜዳሊያ ውስጥ የገቡበትና ታንዛኒያ በታሪኳ ለመጀመሪያ ጊዜ የወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊ የሆነችበት የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ከቀናት በፊት ተጠናቅቋል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ በርካታ ሀገራት ሜዳልያ ውስጥ የገቡበት ሆኖ በተጠናቀቀው 20ኛው የዓለም ሻምፒዮና ቦትስዋና በ4x400 ሜትር ወንዶች የዱላ ቅብብል ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ በማሸነፍ የመጀመሪያዋ አፍሪካዊ ሀገር በመሆን ታሪክ ሰርታለች።

የዓለም አትሌቲክስ ገፀ ድር መረጃ እንደሚያሳየው 196 ሀገራት የተሳተፉበትና በጃፓን ቶኪዮ ሲካሄድ የቆየው ሻምፒዮናው 53 ሀገራት ሜዳልያ ሰንጠረዥ ውስጥ የገቡበት ሆኖ አልቋል። ከአሁን በፊት 46 ሀገራት ሜዳልያ ሰንጠረዥ ውስጥ የገቡት በ2007 የኦሳካ እና በ2023 የቡዳፔስት ዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ሲሆን፣ የቶኪዮው መድረክ በሰባት ሀገራት ብልጫ ያለው ሆኖ ተጠናቅቋል፡፡

በኦሳካ፣ የበርሊን፣ ዶሀ፣ ሞስኮ፣ በኦሬጎን፣ ቤይጂንግ፣ ለንደን፣ ዶሃ ላይ በሜዳሊያ ብዛት የደመቀችው ኢትዮጵያ ከአዳዲሶቹ የስኬት ታሪኮች ከአንዱም ሳትቋደስ ተሳታፊዎቿ ወደ ሀገር ቤት ተመልሰዋል፡፡ ኢትዮጵያ ከውጤት በራቀችበት በዚህ መድረክ የአፍሪካ ሀገራት ተሳትፎ ምን እንደሚመስልና ምን አይነት ውጤት እንዳመጡ እንዲሁም ስኬታማ የሆኑ ሀገራትስ ምን ስለሰሩ ተሳካላቸው የሚሉትን ጉዳዮች መፈተሽ ደግሞ ተገቢነት ይኖረዋል፡፡

በዓለም አትሌቲክስ ታሪክ ውስጥ አፍሪካ ከሌላው ዓለም የተለየ ቦታ አላት። በተለይ በረጅም ርቀት ሩጫዎች የዓለምን መድረክ የመቆጣጠር አቅሟ ለዘመናት የታየ እውነታ ነው። በቶኪዮ በተካሄደው 20ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና ላይም ይህ እውነታ በድጋሚ ተረጋግጧል። አፍሪካውያን አትሌቶች ከሌሎች ሀገራት አትሌቶች ጋር በነበረው ከፍተኛ ፉክክር፣ በጠንካራ ዝግጅት እና ከፍተኛ ተነሳሽነት የአህጉሪቱን ስም ከፍ አድርገዋል፡፡ ኬኒያ ከአሜሪካ ቀጥላ በሁለተኛ ደረጃ ባጠናቀቀችበት ውድድር አፍሪካ 22 ሜዳልያዎችን መሰብሰቧን የአፍሪካን ነውስ ዘገባ ያሳያል፡፡

የደቡብ አፍሪካዊቷን ሀገር ቦትስዋና ወርቃማውን ትውልድ አስቀድመን ስንመለከት አዲስ የተጻፈ ታሪክ እናገኛለን። ቦትስዋና በቶኪዮ ሻምፒዮና ላይ ትልቅ አሻራ ጥላለች፡፡ ከዓመታት በፊት በ400 ሜትር ርቀት ላይ የነበራትን ብቃት በድጋሚ በማሳየት የአፍሪካን አትሌቲክስ ክብር ከፍ አድርጋለች። በተለይም በወንዶች የ400 ሜትር ሩጫ ኮለን ኬቢናትሺፒ የወርቅ ሜዳሊያ በማምጣት ለሀገሩ ታሪካዊ ድል አስመዝግቧል፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን፣ ቦትስዋና በ4x400 ሜትር ቅብብል ውድድር ከአሜሪካና ከደቡብ አፍሪካ ጋር በነበረው ከፍተኛ ፉክክር አሸንፋ የወርቅ ሜዳሊያ በማምጣት ከተለፉ በአጭር ርቀት ሩጫ ውድድሮችም ውጤታማ መሆን እንደሚቻል ማረጋገጫ ሰጥቶ አልፏል፡፡

ደቡብ አፍሪካ እንደዚሁ በቶኪዮ ሻምፒዮና ላይ ያሳየችው አፈጻጸም እጅግ የሚያስደንቅ ነበር፡፡ በ4x400 ሜትር ቅብብል ውድድር ላይ ጠንካራ ብቃት በማሳየት የነሐስ ሜዳሊያ በማምጣት፣ በዓለም አትሌቲክስ መድረክ ላይ ያላትን ቦታ አጠናክራለች፡፡ አልጄሪያ በበኩሏ በ800 ሜትር ሩጫ ድጃመል ሴጃቲ በወርቅ ሜዳሊያ አሸናፊው ከኬንያው ኢማኑኤል ዋንዮኒ ጋር ባደረገው ከፍተኛ ፉክክር የብር ሜዳሊያ አምጥቷል። ይህ በወንዶች የ800 ሜትር ሩጫ የአፍሪካ አትሌቶች ያላቸውን የበላይነት በድጋሚ ያሳየ ክስተት ሆኗል።

ኬንያ የረጅም ርቀት ሩጫ ንግሥናዋን በድጋሚ አረጋግጣለች፡፡ በቶኪዮ በተካሄደው ሻምፒዮና የሜዳሊያ ሰንጠረዥ ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ከአሜሪካ ቀጥሎ ትልቅ አፈጻጸም አሳይታለች፡፡ ኬንያ በወርቅ፣ በብር እና በነሐስ ሜዳሊያ ብዛት ሁለተኛ ሆና በማጠናቀቅ የአትሌቲክስ ልዕልናዋን አረጋግጣለች፡፡ በተለይም በሴቶች የ5 ሺህ ሜትር ሩጫ ቤትሪስ ቼቤት የወርቅ ሜዳሊያ በማሸነፍ ታላቅ ስኬት አስመዝግባለች፡፡ በወንዶች የ800 ሜትር ሩጫ ኢማኑኤል ዋንዮኒ በሻምፒዮናው ታሪክ እጅግ ፈጣን ሰዓት አንዱን (1:41.86) በማስመዝገብ ለሀገሩ ወርቅ አስገኝቷል ይላል የዴይሊ ኔሽን መረጃ፡፡

ከታላላቆቹ የአፍሪካ አትሌቲክስ ሀገራት ባሻገር፣ ሌሎች ሀገራትም ስኬት አስመዝግበዋል፡፡ ታንዛኒያ በቶኪዮ

> መንግሥታት ለአትሌቲክስ የሚሰጡት ድጋፍ፣ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ማሻሻልና ወጣቶችን ከልጅነታቸው ጀምሮ ማሰልጠን፣ ለወደፊት የአፍሪካ ስፖርት መሻሻል ወሳኝ መሆኑን የቶኪዮው ሻምፒዮና አሳይቷል

የዓለም ሻምፒዮና የመጀመሪያውን የወርቅ ሜዳሊያ ታሪክ አስመዝግባለች። አልፎንስ ፌሊክስ ሲምቡ በማራቶን ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ አሸንፎ ታሪክ ሰርቷል፡፡ ይህ ድል የታንዛኒያን ስም ከፍ ከማድረጉም በተጨማሪ ለአፍሪካ የማራቶን ሩጫ ያለውን ተስፋ አሳይቷል።

በሻምፒዮናው የኬንያ የበላይነት በረጅም ርቀት ሩጫ፣ በአጭርና መካከለኛ ርቀቶች የቦትስዋና መነቃቃት እንዲሁም የታንዛኒያ ታሪካዊ ስኬት አፍሪካ በአትሌቲክስ ዓለም ያላትን ቦታ ከፍ ያደረገ ስለመሆኑ ደግሞ በአፍሪካ አትሌቲክስ ጉዳዮች ፀሐፊው ዴኒስ ፒተር ያስረዳል፡፡ ፀሐፊው እንደሚለው የአፍሪካ አትሌቶች በዓለም መድረክ ላይ ያስመዘገቧቸው ስኬቶች እንዲሁ በአጋጣሚ የመጡ አይደሉም። ይልቁንስ በስተጀርባው የዓመታት ከባድ ስልጠና፣ ጠንካራ ቁርጠኝነት እና የስፖርት ሳይንስን መጠቀም ትልቅ ሚና ተጫውተዋል ይላል።

የዴይሊ ኔሽን ፀሐፊው ጀምስ ሚዋንባ እንደሚለው ከሆነ አብዛኞቹ አፍሪካውያን አትሌቶች ስኬትን ለማግኘት በከፍታ ቦታዎች (High Altitude) ላይ በመሠልጠን የሰውነታቸውን የኦክሲጅን አጠቃቀም አቅም አሳድገዋል፡፡ ይህ የሥልጠና ስልት በተለይም የኬንያ እና የኢትዮጵያ አትሌቶች ለረጅም ጊዜ ሲጠቀሙበት የቆዩ እንደሆነ እሙን ነው።በአፍሪካ አትሌቲክስ ጉዳዮች ፀሐፊው ዴኒስ ፒተርም በዚህ ሀሳብ ይስማማል፡፡ ፀሐፊው እንደሚለው በተለይ እንደ ኬንያውያን ያሉ አትሌቶች አስደናቂ ብቃት ጀርባ ብዙ ምክንያቶች እንዳሉ ጠቅሶ፣ የዚህ ስኬት መሠረታዊ ነገሮች ከዘመናት ከቆየ ባህል፣ ከተፈጥሯዊ ሁኔታዎች እና ከስልጠና ስልቶች ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በተለይም ዘመናዊ የስልጠና አሰራሮችን መዘርጋት፣ የዘርፉ ባለሙያዎች ተሳትፎ ማሳደግ፣ ተተኪ ስፖርተኞች በብዛት ማምረት ለስኬታማነታቸው በምክንያትነት ከሚጠቀሱ ጉዳዮች እንደሆኑ ፀሐፊው ያብራራል፡፡

አብዛኞቹ የኬንያ አትሌቶች በተለይም በረጅም ርቀት የሚወዳደሩት ከባህር ወለል በላይ በከፍተኛ ቦታዎች (ታዋቂው ኢተን ከተማ በማሳያነት ብንወስድ) ላይ ይኖራሉ። አትሌቶች በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲሰለጥኑ ሰውነታቸው ከወትሮው የበለጠ ቀይ የደም ሴሎችን በማምረት ኦክስጅንን በብቃት የመጠቀም አቅሙ ይጨምራል። ይህ ደግሞ በዝቅተኛ ቦታዎች ወደሚደረጉ ውድድሮች ሲሄዱ ትልቅ ጥቅም ይሰጣቸዋል። በሌላ በኩልም በኬንያ ብዙ ወጣቶች አትሌቲክስን እንደ የኑሮ መሠረትና የመታወቂያ መንገድ አድርገው ይወስዱታል። የብዙ ታላላቅ አትሌቶች ስኬት ብዙ ወጣቶችን ስለሚያነሳሳ፣ በየቀኑ ጠንካራና የቡድን ስልጠናዎችን ያደርጋሉ። ይህ ተፎካካሪ የሆነ የሥልጠና ባህል ወጣቶች ጠንካራ እንዲሆኑ ያግዛቸዋል።

የአፍሪካን አትሌቲክስ ወደ አዲስ ምዕራፍ ሊያሸጋግረው ይችላል በማለት ጀምስ ሚዋንባ በቀጣይም በትኩረት ሊሰራበት ይገባል ያለውን ጉዳይ ይገልጻል፡፡ የሀገራት መንግሥታት ለአትሌቲክስ የሚሰጡት ድጋፍ፣ የስፖርት ማዘውተሪያዎችን ማሻሻልና ወጣቶችን ከልጅነታቸው ጀምሮ ማሰልጠን፣ ለወደፊት የአፍሪካ ስፖርት መሻሻል ወሳኝ መሆኑን የቶኪዮው ሻምፒዮና አሳይቷልና ሊሰራበት ይገባል ይላል።

619 ሺህ 288 ተመልካቾች በቶኪዮ ብሔራዊ ስቴዲየም ተገኝተው ውድድሮቹን በታደሙበት 20ኛው የዓለም አትሌቲክስ ሻምፒዮና አሜሪካ በ16 ወርቅ፣ 5 ብር እና 5 የነሐስ ሜዳልያ በበላይነት ስታጠናቅቅ ኬንያ በ7 ወርቅ፣ 2 ብር 2 ነሐስ 2ኛ እንዲሁም ካናዳ በ3 ወርቅ 1 ብር እና 1 ነሐስ 3ኛ ደረጃን ይዛ ጨርሳለች፡፡ ኢትዮጵያም በ2 ብር እና በ2 የነሐስ ሜዳልያ ከዓለም 22ኛ ደረጃን ይዛ ያጠናቀቀችበት መድረክ ሆኖም ስለመጠናቀቁ የዓለም አትሌቲክስ መረጃ ያሳያል፡፡